# የአዲስ
# ኪዳን
# ታሪክ

# መቅደም

የአዲስ ኪዳን ታሪክ የተሰኘው መጽሐፍ የአዲስ ኪዳንን ይዘት ባጭሩ የሚያቀርብ ነው። መጽሐፉ የአዲስ ኪዳንን ታሪክ በሙሉ ለማቅረብ ስለሚፈልግ ለእያንዳንዱ ሁኔታ ማብራሪያ ለመስጠት አይችልም፤ ተማሪ ትምህርቱን ሲከታተል ይህንን ማብራሪያ በሌላ የትምህርት ወቅቶች ያገኘዋል። በመሆኑም መምህር ሲያስተምር ታሪኩን በሙሉ መሸፈን ስለሚያስፈልገው በሚያውቃቸውና በሚወዳቸው ታሪኮች ላይ ብዙ ሰዓቶች እንዳያጠፋ መጠንቀቅ ያሻዋል። ይህ የመጀመሪያ እትም ስለሆነ አንዳንድ የፊደልና የአቀራረብ ጉድለቶች ሊገኙ ይችላሉ፤ ወደ ፊትም ሰፋ ባለ ሁኔታ ታሪኩን ለማጠናቀር ሰላቀድን በሁለተኛው እትም የበለጠ እንደምትደሰቱ እንተማመናለን።

ሦስተኛ ዕትም

መስከረም 1985 ዓ.ም.

# ማውጫ

ገጽ ገጽ

ዞካርያስ ..................... 5
ከተማው ..................... 5
የጥንቱ መንፈስ .......... 5
ዮሐንስ ..................... 5
ኢየሱስ ..................... 6
ግብር ..................... 6
ቤተልሔም ..................... 6
አካባቢው ..................... 7
ልዩ ቦታዎች ..................... 7
ጠቢባን ..................... 7
ግብፅ ..................... 8
ሄሮድስ ..................... 8
ቤተ መቅደስ ..................... 9
ገሊላ ..................... 9
ናዝሬት ..................... 10
ባሕል ..................... 10
አካባቢው ..................... 10
ሕብረትዋ ..................... 11
ለውጥ ..................... 11
ሃይማኖት ..................... 12
ዮሐንስ ..................... 12
ጥምቀት ..................... 13
ሄሮድስ ..................... 14
ፈተናው ..................... 14
አገልግሎቱ ..................... 15
ቤተ መቅደስ ..................... 15
ኒቆዲሞስ ..................... 15
ሳምራዊቱ ..................... 16
ገሊላ ..................... 16
ባሕሩ ..................... 16
ጌንሴሬጥ ..................... 17
ከተሞች ..................... 17
የዓሣ ማጥመድ .......... 18
ማረፊያ ቦታዎች ......... 18
ሐዋርያት ..................... 19
የተራራው ስብከት ............ 19
መግለጫ ..................... 20
ምሳሌዎች ..................... 20
ዘሪው ..................... 20
ኃይቁ ..................... 21
ጢሮስ ..................... 21
መለወጡ ..................... 22
ሰማርያ ..................... 22
የያዕቆብ ምንጭ ............. 23
ሳምራውያን ..................... 24
የወይን ቦታ ..................... 24
ቢታንያ ..................... 24
ፔሪያ ..................... 25
ኢያሪኮ ..................... 25
ቢታንያ ..................... 26
ኢየሩሳሌም ..................... 26
ትዝታና ዝግጅት ............. 26
ደብረ ዘይት ..................... 27
ጌቴሴማኒ ..................... 27
ሥራና ትምህርት ............ 28
ፈተና ..................... 29
ጎልጎታ ..................... 30
ትንሣኤው ..................... 31
ዕርገቱ ..................... 32
ሐዋርያቱ ..................... 32
በዓለ ሐምሳ ..................... 33
አይሁዶች ..................... 33
ምቀኝነት ..................... 34
እስጢፋኖስ ..................... 34
ሰማርያ ..................... 35
ጀንደረባው ..................... 35
የወንጌል ተልዕኮ ............ 36
ጠርሴስ ..................... 36

ኢየሩሳሌም ............ 37
የሳዖል መለወጥ ...... 37
ሦስት ዓመት ......... 38
ሦርያና ቂሣርያ ...... 39
የጴጥሮስ ራዕይ ....... 40
ቆርኔሌዎስ .......... 40
ሰሙጥ .................. 41
ሄሮድስ ................. 41
ቀላውዴዎስ ........... 42
በርናባስ ................ 42
አንጾኪያ ................ 42
ቆጵሮስ ................. 43
ማርቆስ ................. 44
ጢሞቴዎስ ............ 45
ሦርያዊ አንጾኪያ ..... 45
49 ዓ.ም. ............ 45
አንጾኪያ ............... 46
አለመግባባት .......... 46
ሲላስ ................... 47
2ኛው ጉዞ ........... 47
ገላትያ ................. 48
ጢሮአዳ ................ 48
ራዕይ .................. 49
ፊልጵስዩስ ............ 49
ተሰሎንቄ ............. 50
ቤርያ ................... 50
አቴና ................... 50
ጳውሎስ በአቴና ....... 51
በቆሮንቶስ ............ 52
ሲላስ ................... 52
በኤፌሶን............... 53
ሁካታው ............... 54
በጢሮአዳ ............. 54
ኢየሩሳሌም ........... 55
ቂሣርያ ................. 55
ጉዞው .................. 56
አስተዳዳሪዎች ........... 56
የባሕር ጉዞ .............. 57
የጳውሎስ ጠባይ ......... 57
መላጥያ ................... 58
ሮም ....................... 58
አገልግሎት ............... 59
ምርመራው ............... 59
እስጳንያ .................. 59
2ኛው እሥራት .......... 60
የጳውሎስ ሞት .......... 60
ባልደረቦቹ ................ 60
ያዕቆብ .................... 61
ጴጥሮስ ................... 62
ቶማስ ..................... 62
እንድርያስ ............... 63
በርጠሎሜዎስ ............ 63
ፊልጶስ .................... 63
ማቴዎስ ................... 63
ስምዖን .................... 63
ይሁዳ ..................... 64
ማቲያስ ................... 64
ዮሐንስ ................... 64
የእስያ አብያተ ክርስቲያናት .. 65
ኤፌሶስን ................. 65
ሰምርኔስ ................. 65
ጴርጋሞን ................ 65
ትያጥሮን ................. 66
ሰርዴስ ................... 66
ፊልዳልፍያ .............. 66
ሎዶቅያ .................. 67
ፍጥሞ .................... 67
ዮሐንስ .................. 67
ይሁዳ .................... 68
ቲቶ ...................... 68
ሮማውያን ............... 69
የወንጌል ሥርጭት ..... 70
መደምደሚያ ........... 70

# የአዲስ ኪዳን ታሪክ

## ዘካርያስ በኢየሩሳሌም

ንጉሥ ሄሮድስ ፈርሶ የነበረውን የአይሁድ ቤተ መቅደስ አሳደሰ። ከዚያም የጸሎትና የማምለኪያ ስፍራ እንዲሆን መርቆ ሰጠ። ከዚህ በኋላ ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የተባለ ካህን የቤተ መቅደስ አገልጋይ ነበረ። እንደ ጥንቱ የካህናት ሥርዓት መሠረት እያንዳንዱ ካህን በፋንታው የአንዳንድ ሳምንት አገልግሎት ይሰጥ ነበር። በዚህ መሠረት ዘካርያስ በቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል ገብቶ አገልግሎቱን ጀመረ።

## የከተማው መልክ

በዚህን ጊዜ ኢየሩሳሌም ጥንታዊቷን የኢየሩሳሌምን ከተማ አትመስልም ነበር። ከቤተ መቅደሱ በስተ ምዕራብ በኩል በከፍተኛ ስፍራ ላይ የተሠራው የሄሮድስ ቤተ መንግሥት ነበረ።

## የጥንቱ ዘመን መንፈስ አለፈ

ማንኛውም የአይሁድ ባሕል ግማሽ በግማሽ በባዕድ አገር ወግ ተከልሷል። ሌላው ቀርቶ የአገሪትዋ ብሔራዊ ቋንቋ እንኳ ሳይቀር በአብርሃምና በዳዊት ዘመን አይሁዶች ይነጋገሩበት ከነበረው ቋንቋ ፍጹም የተለየ ነበረ። አብዛኛዎቹ አይሁዶች የአራም ቋንቋ በመስለ ዓይነት ቋንቋ ሲነጋገሩ የቀሩት ደግሞ በግሪክ ይነጋገሩ ነበር። ጠንካራው የአይሁድ የጦር ኃይል ክፍል ደግሞ በሮም ሕዝብ ቋንቋ ይነጋገር ነበር። እርግጥ ቤተ መቅደሱ በእብነበረድ ባሸበረቁ ሕንፃዎች ተጋጊጦ ነበር። ያም ሆኖ ይህ ለጸሎት ቤትነት የተሠራው የማምለኪያ ሥፍራ የእርግብ ሻጮችና የገንዘብ ለዋጮች መናኸርያ በመሆኑ አዘነ። ታዲያ የጥንቱ መንፈስ ወዴት ደረሰ? በመጨረሻው ዘመን የሚነሣው መሢህ የት አለ?

## የዮሐንስ ልደት ዜና

በዚህን ጊዜ ዘካርያስ ከካህናት ተግባር ውስጥ እጅግ የከበረውን ክፍል እያከናወነ ነበር። እርሱም ሕዝቡ በውጭ በጸጥታ ሆኖ እየጸለየ ሳለ ወደ ቅድስት ከመግባቱ በፊት የመሥዋዕቱን በግ ሠውቶ ለእግዚአብሔር የማዕዛ ሽታ የሆነውን ዕጣን ያጥን ነበረ። በዚህ ጊዜ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት ለዳንኤል የታየው መልአኩ ገብርኤል በድንገት ተገለጠለት። እርሱም በእርጅና ዘመንዋ ላይ የምትገኘው የዘካርያስ ባለቤት ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ይነግረዋል። ከዚህም በቀር ሕፃኑ ወደ ዓለም ሊመጣ ላለው መሢህ መንገድ የሚያዘጋጅ ነብይ

እንደሚሆን ያስታውቀዋል። በዚህን ጊዜ መልአኩ የነገረውን ዜና ዘካርያስ ባለማመኑ እንደበቱ ተይዞ ድዳ ሆነ፤ ሕፃኑ ተወልዶ በዓይኑ እስካየበት ቀን ድረስ ዘካርያስ ድዳ እንደሆነ ቀየ። ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ከኢየሩሳሌም ወጥቶ በተራራማው አገር ወደምትገኘው ወደ ቀድሞ መኖርያ ሥፍራው ወደ ይሁዳ ከተማ ሄደ።

## የኢየሱስ ልደት ዜና

ከስድስት ወር በኋላ ይኸው ወደ ዘካርያስ ተልኮ የነበረው መልአክ በሰተሰሜን ወደሚገኘው ከተማ ሌላ ዜና ይዞ እንደገና መጣ። በዚያም በናዝሬት ገጠራማ ክፍል ማርያም የምትባል አንዲት ድንግል ትኖር ነበረ። እርስዋም ትውልድዋ ከዳዊት ዘር ሲሆን ከቀሩት የአይሁድ ልጃገረዶች የምትለየው በነበራት ቅንነትና ረጋ ያለ መንፈሳዊ ሕይወት ነበረ። በሌላው አንፃር ደግሞ ማርያምና ወላጆችዋ በጣም ዝቅ ባለ ኑሮ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ቢሆኑም ያሉበትን ሁኔታ በምስጋና ለመቀበል የታደሉ ነበሩ። ገብሬኤልም ወደዚህች ድንግል መጥቶ በአክብሮት ሰላም ለአንቺ ይሁን አላት። እርስዋም በሰላምታ አሰጣጡ ተደንቃ ከዚህ በኋላ ሊነግራት ያለውን ዜና በአንክሮ ታደምጥ ጀመር። መልአኩ የመጣው ወንድ ልጅ እንደምትወልድና ስሙንም ኢየሱስ ብላ እንደምትጠራው ሊነግራት ነው። ኢሳይያስ ድንግል እንደምትወልድና ስሙንም «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው» ለማት አማኑኤል እንደምትለው የተናገረው ትንቢት በዚህ ይፈጸማል።

## የሕዝቡ ግብር መክፈል

ማርያም በዘካርያስ ቤተሰብ ውስጥ የተፈጸመውን ዜና ከሰማች በኋላ አክስቷን ኤልሳቤጥን ለመጐብኘት የረጅም ጉዳና ጉዞዋን ጀመረች። ከዚያም የአክስቷ የኤልሳቤጥ ባለቤት በሆነው በዘካርያስ ቤት ለሦስት ወር ተቀመጠች፤ በኋላም እጮኛዋ ዮሴፍ ወደሚኖርበት ወደ ናዝሬት ተመልሳ መጣች። እጮኛዋ ዮሴፍ ከዳዊት ዘር የሆነ እግዚአብሔርን የሚፈራና ጻድቅ ሰው ነበረ። ከዚያም ብዙ ሳይቆይ የሮም ንጉሥ በየከተማው የሚኖር ሕዝብ ሁሉ አጠቃላይ የሆነ ግብር እንዲከፍል አሳወጀ። ዮሴፍም እጮኛውን ማርያምን ይዞ ለመመዝገብ ወደ አባቶቻቸው ከተማ ወደ ቤተልሔም ሄደ። አንዳንድ አይሁዶችም ቄሳር ያሳወጀውን የግብር አዋጅ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ተቃውሞአቸውን አሰምተው ነበር። በተለይ አንድ ከገሊላ የሆነ ይሁዳ የተባለ ሰው ተነሥቶ እስከ ጌታችን ቀን ድረስ አካራካሪ ሆኖ በቆየው በግብር መክፈልና አለመክፈል ክርክር ጉዳይ ላይ ታላቅ ረብሻ አስነሥቶ ነበር፤ የሐዋ.5፡37 ተመልከቱ። በኋላም ከክርስቶስ ሞት በኋላ አርባ ዓመት ቆይቶ ቲቶና ሠራዊቶቹ በኢየሩሳሌም ላይ የዘመቱት በዚሁ የግብር ክፍያ ተቃውሞ የተነሣ ነው።

## ቤተልሔም

ዮሴፍና ማርያም ምናልባት ከጥቂት ወራት በፊት ማርያም ወደ ደቡብ በተጓዘችበት ተመሳሳይ መንገድ ላይ ሆነው ወደ ቤተልሔም ተጉዘው ይሆናል። ከዚያም ቤተልሔም እንደደረሱ ያረፉበት ሥፍራ ከአሁን ቀደም የከብቶች ማደሪያ እንደሆነ በሚመስል ቤት

ውስጥ፤ ወይም ደግሞ የመኳሳት ታሪክ እንደሚናገረው ከከተማው ራቅ ብለው ከሚገኙ ዋሻዎች መካከል በአንደኛው ውስጥ አርፈው ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ በዋሻው ላይ እጅግ በጣም ያማረ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል። ይህም ቦታ የተቀደሰ ቦታ ሆኖ የተለየው ክርስቶስ ከሞተ ሦስት መቶ ዓመት ቆይቶ ነው። ምንም እንኳ ይህ ቦታ ክርስቶስ የተወለደበት ትክክለኛ ሥፍራ እንደሆነ ቢነገርለትም በግምትና በይሆናል እንጂ ተጨባች ማረጋገጫ የለውም።

## የአካባቢው መልክ

ቤትልሔም የምትገኘው ከኢየሩሳሌም ደቡባዊ ክፍል ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሚገኝ ሥፍራ ላይ ነው። በስተ ሰሜንና በስተ ምስራቅ በኩል ካሉ ከፍተኛ ሥፍራዎች ቁልቁል ሲወርድ አንዳንድ መንገድ ብቻ ያሉዋቸው ትናንሽ ከተማዎች በሩቅ ይታያሉ። ቤቶቻቸውም ተመሳሳይ በሆኑ በነጫጭ ጥርብ ድንጋዮች የተሠሩ ሲሆኑ ረጃጅም በሆኑ የወይራ ዛፎች ሥር ጉልቻ መስለው ይታዩ ነበር። በዙሪያቸው ያሉ ትናንሽ መንደሮች ደግሞ በዚህ ድንጋያማ አገር ውስጥ ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ ድንጋያቸው በዝቶ ነበረ። ሆኖም አልፎ አልፎ በሸለቋማና ገለልተኛ በሆኑ ሥፍራዎች ላይ ምንም ጊዜ አረንጓዴ ልምላሜ ጠፍቶ አያውቅም። በከተማዎቹ አቅራቢያ ያሉት ብዙ የበለስና የወይን አትክልቶች ይገኛሉ፤ በአካባቢያቸው በተሠሩ ትናንሽ ማማዎች ላይ ባሉ ዘበኞች ይጠብቁ ነበር።

## የመታሰቢያ ቦታዎች

በአካባቢው ከሚገኙ ቦታዎች ሁሉ እንደነዚህ ለመታሰቢያ የተለዩ ቦታዎች የከበረ ሥፍራ አልነበረም። ከእነዚህም ሥፍራዎች መካከል አንዱ ያዕቆብ ውድ ባለቤቱ ራሔል በሞተችበት ጊዜ በሐዘን ቆዝሞ የነበረበት ቦታ ነው። በሌላም በኩል ሩት ቃርሚያ ልትቃርም መጥታ የቦኤዝን ልብ የማረከችበት እርሻም የሚገኘው በዚሁ አካባቢ ነበረ። በኋላም ሩት የቦኤዝ ሚስት ሆና የኖረችው እዚሁ ቦታ ነው። ከዚህም በቀር ዳዊት የምስጋና መዝሙሮቹና እያጠና የአባቱን በጎች ያግድበት የነበረው ሜዳ ከቦኤዝ እርሻ ብዙ አይርቅም። የአይሁድ እረኞች ከምሽት መንጎቻቸውን እየጠበቁ መልአኩ የክርስቶስን ልደት ያበሰረላቸው በዚሁ ዳዊት የአባቱን በጎች ያግድ በነበረበት ሜዳ ላይ ነበረ። መልአኩም አትፍሩ፤ እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና አላቸው። የወንጌል መልዕክት በመለኮታዊ ኃይሉ በሕዝቡ ጆሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰማው በዚሁ ሥፍራ ነበረ። «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር ለሰውም በጐ ፈቃድ።»

## የጠቢባኑ ሰዎች ጉብኝት

ማርያም ከቤተልሔም እስከ ኢየሩሳሌም የሚያስኬደውን መንገድ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ከሦስት ሰዓት በላይ አይወስድባትም። ስለዚህ እንደ ሕጉ ይደረግለት ዘንድ ሕፃኑን ኢየሱስን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰደችው። በዚያም ማንኛውም በዝቅተኛ ኑሮ የምኖር ግለሰብ ይጠይቅ

የነበረውን ሁለት ዋልያ ወይም የርግብ ጫጩቶች አቅርባ መሥዋዕት ተደረገላት። ከዚያም ዕለቱኑ ወደ ቤተልሔም ተመለሰች። ከምሥራቅ የመጡት ጠቢባን ቤተልሔም የደረሱት ማርያም ሕፃኑን ቤተ መቅደስ አስገብታው ሐናና ስምዖን ተስፋ የተሰጠው ሕፃን እንደሆነ ኢየሱስን ባስታወሰበት ቀን መሆን አለበት ምናልባት እነዚህ ጠቢባን ከከለዳውያን አገር፥ ከፋርስ ወይም አይሁዶች በምርኮ ዘመን ይኖሩባቸው ከነበሩት ከአንደኛው አገር መጥተው ይሆናል። ጠቢባኑም የአይሁድ ንጉሥ የሚወለድበትን ዘመን ሊያውቁት የቻሉት የነቢያትን ትንቢት በመከታተል እንደሆነ አያጠራጥርም። ከዚህም በቀር ጠቢባኑ የኮከቡን መውጣት ከክርስቶስ ልደት ጋር ያገናዘቡት ምናልባት የመስጴጦምያ ተወላጅ የሆነውን የበለአምን ትንቢት በማስታወስ ይሆናል። «ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል፤ ከእስራኤል በትር ይነሣል፤ የሞዓብንም ማዕዘኖች ይመታል፤ የሴትንም ልጆች ያጠፋል።» ይህ ጠቢባኑን ይመራ የነበረ ኮከብ ሕፃኑ ኢየሱስ በተወለደበት ቤት ላይ ደርሶ እስከቆመ ድረስ ፊት ፊታቸው ይሄድ ነበር። ኮከቡም ሕፃኑ በተወለደበት ቤት በደረስ ጊዜ ሌሎች ብርሃናት በማይቻላቸው ሁኔቴ ጨረሩን ወደ ቤቱ ውስጥ በማስገባት ሳያንጸባርቅ አይቀርም ብለን እንገምታለን።

## ወደ ግብፅ የተደረገው ሽሽት

የአዲሱ ንጉሥ መወለድ ዜና የሄሮድስን ቅናት ቀሰቀሰው። ሄርዶስም ሊቀካህኑንና ጸሐፈትን ጠይቆ የአይሁድ ነጉሥ የሚወለደው በቤተልሔም እንደሆነ ተረዳ። ከዚያም በሕፃናቱ መካከል ኢየሱስን አግኝቼ እገድለውለሁ ብሎ ስላሰበ ሄሮድስ የቤተልሔምን ሕፃናት ሁሉ አሳረደ። ግድያው ከመፈጸሙ ቀደም ሲል ግን የእግዚአብሔር መልአክ ሊመጣ ያለውን አደጋ ለዮሴፍ ሳላሳውቀው ፈጥኖ ከቤትልሔም ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ ሸሸ። የዮሴፍ ቤትሰብም ከቤተልሔም ከወጣ በኋላ በጥገኝነት እንዲኖር ያስተናገደችው አገር ግብፅ ነበረች። ቢሆንም በግብፅ አገር ሳሉ በየትኛው ሥፍራ እንዳረፉ የሚገልፅ ታሪክ የለም።

## የሄሮድስ ሞት

ሄሮድስ የቤተልሔሙን ግድያ ለማራዘም ራሱ በሕይወት ብዙ አልቆየም ነበር። ከጥቂት ወራት በኋላ ሄሮድስ በከፉ ደዌ ተይዞ ሞተ። የሕመሙም ዓይነት እብጠት የበዛበት ሲሆን አልፎ አልፎ ሲፈነዳ ትል የሚያፈራ ቁስል ይሆንበት ነበር። ሄሮድስ ከመሞቱ በፊት አይሁዶች እንደሚጠሉት ስላወቀ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ አጠቃላይ የሆነ ሐዘን እንዲደረግ አዲስ ትዕዛዝ አወጣ። ከዚህም በቀር ሄሮድስ በሚሞትበት ዕለት ጠላቶቹ እንደሆኑ እሁቱ ያነካከሰቻቸውን ሹማምንት በሞላ የሄሮድስ የእህቱ ባለቤት የሆነው ሰው እንዲገድላቸው አሳዘዘው። ሆኖም የሄሮድስ ትዕዛዝ ተፈጻሚነት አለገኘም። ሄሮድስም አይሁዶችን 37 ዓመት ካስተዳደረ በኋላ በ70 ዓመት ዕድሜው ሞተ። ሄሮድስ ከሞተ በኋላ ሥልጣኑ በሦስት ወንዶች ልጆቹ መካከል ተከፋፈለ። ከእነርሱም መካከል አርኬላኦስ የተባለው ልጁ የይሁዳ ገዢ ሲሆን ሄሮድስ በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገዢ ነበረ። ወንድሙ ፊልጶስ ደግሞ በኢጡርያስ በጥራኮኒዶስ አገር የአራተኛው ክፍል ገዢ ሆነው ተሾሙ። ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ከነቤተሰቡ ከተሰደደበት ከግብፅ አገር ተመለሰ ዮሴፍም በጊዜው የይሁዳ ገዢ የነበረውን አርኬላኦስን በተመለከተ ጊዜ በጣም ትዕቢተኛና ክፉ ሰው መሆኑን አወቀ። ይሄም

ሰው እንደ አባቱ በሥልጣን ላይ እንደማይቆይ ተረዳ። ከዚያም ልክ ዮሴፍ እንዳሰበው ከሥልጣኑ ተባሮ ወደ ተወለደበት ወደ ገሊላ ጠረፍ ሄዶ በተራራማው ምድር ሞቶ በዚያው ተቀብሮ ቀረ።

## ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን እንደጐበኘ

በሥጋ ለተወለደው ለእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ ናዝሬት የ30 ዓመት ምድራዊ መኖሪያ ሥፍራ ሆናው ነበር። ኢየሱስም በ12 ዓመት ዕድሜው እንደገና ለአንድ ጊዜ ብቅ ብሎ ታይቷል። በአይሁዶች ሕግ መሠረት አንድ ሰው የፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ሲከበር የበዓሉ ተሳታፊ የሚሆነው 12 ዓመት ሲሞላው ነበር። በበዓሉ ፍጻሜ እናቱና ዮሴፍ ኢየሱስ አብሯቸው ያለ መስሏቸው ትተውት ጉዞአቸውን ወደ ገሊላ ቀጠሉ። በመንገድ ሳሉም ኢየሱስ አብሯቸው እንደሌለ አረጋግጠው ሊፈልጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። በዚያም ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ውስጥ መምህራን የሚናገሩትን እያዳመጠ አንዳንዴም ጥያቄ ይጠይቃቸው ነበር። ዮሴፍና ማርያምም ባገኙት ጊዜ በተለይ እናቱ ሊፈልጉት ተመልሰው እንደመጡ ትነግረዋለች። ኢየሱስም ለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት መሆን አይገባኝምን? አላት። እርሷም አነጋገሩ ጨርሶ ሊረሳት በማይችል ሁኔታ ገባት። ከዚያም ኢየሱስ በቤተ መቅደስ የጀመረውን ትምህርት በመቀጠል በባሕል ስለሚያውቋቸው ነገሮች ከመጽሐፍ እየጠቀሰ እውነተኛነታቸውን ያረጋግጥላቸው ጀመር።

## ገሊላ

ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ እንደ ሕጉ ይደረግለት ዘንድ አንድ ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ ከተወሰደ ወዲህ ለረጅም ጊዜ ቆይቶ አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ከገሊላ ብቅ ማለቱ ነው። የናዝሬት ከተማ የተቆረቆረችው በገጠራማው ሥፍራ ጥንት የዛብሎን ምድር በነበረው ቦታ ላይ ነው። ይህ ሥፍራ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተለየ ስም አልተሰጠውም። እንዲያውም በደፈናው ግን የጥንቱ የጌታችን መኖርያ ሥፍራ በመባል ይታወቅ ነበር። በላይኛው ክፍል የሚገኘው የገሊላ ምድር ጥንት በሦርያ ንጉሥ ተይዞ ስለነበረ በውስጡ የነበረው ሕዝብ ተማርኮ መሬቱ ባዶውን ነበር። ከዚያን ጊዜ በኋላ በሥፍራው የሚኖሩት ሰዎች ድብልቅና የተለያዩ ዜጐች ነበሩ። እነርሱም ፊንቂአውያን፥ አሦራውያን፥ ግሪኮችና አረቦች ናቸው። በኋላም ቆይቶ በአዲስ ኪዳን ዘመን ይህ ሥፍራ «የአሕዛብ ገሊላ» እየተባለ ይጠራ ጀመር፤ ማቴ.4፥15። እነዚህ በአሕዛብ ገሊላ የሚኖሩ የተለዩ ሕዝቦችም ከአይሁዶች ጋር ስለማይዋደዱ አይቀራረቡም ነበር። እነርሱም ይህንን ጥላቻና መጥፎ ባሕሪይ የተማሩት አብረዋቸው ከሚኖሩ ከተለያዩት ዜጋዎች ነበረ። ሆኖም በዚህን ጊዜ የእነዚህ በአሕዛብ ገሊላ የሚኖር ልዩ ወገኖች ትዕቢትና ጥላቻ በሃይማኖት ላይ ምንም ተጽዕኖ አልነበረውም። ስለዚህ ከጥንቶቹ የአይሁድ መምህራን የሃይማኖት ተጽዕኖ እጅግ የተሻለ ነበረ። ከዚህ የተነሣ ለክርስቶስ በግልም ሆነ በማሕበር ያደርገው ለነበረው መንፈሳዊ አገልግሎት በጣም የተመቸ ጊዜ ሆነለት። ይህ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ይገኝ የነበረው የሃይማኖት ተጽዕኖ እስከ ገሊላ ድረስ አልተስፋፋም ነበር። በዚህ ምክንያት ኢየሱስ በገሊላ እጅግ ብዙ ሕዝብ አስከትሎ በሰላም ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ለመዘዋወር ችሎዋል። በሌላ አንጻር ግን አይሁድ በቅንዓት

ኢየሱስን ሊገድሉት ይፈልጉ ስለነበረ ሐዋርያት ዘወትር በሥጋት ይኖሩ ነበር። ኢየሱስ ሐዋርያትን የመረጠው ከዚሁ ከገሊላ አካባቢ ነበረ። ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ያዩት አምስት መቶ ሰዎች ምስክርነታቸውን የሰጡትም እዚሁ ነበር። ከዚያም ሐዋርያት መቶ ሃያ ሰው ሆነው ሲጸልዩ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት በዚሁ ሥፍራ ነበር።

## ናዝሬት

የናዝሬት ከተማ የተቀረቀረችው በተራራ መካከል በምትገኝ ትንሽ ሜዳማ ሥፍራ ላይ ነው። በዙሪያዋ ያሉት 15 ተራራዎችም ከተማዋን እንደ አጥር ከበው ሲታዩ ሆን ተብለው ለዚህ ተግባር የተሠሩ ይመስሉ ነበር። ተራራዎቹም ወደ ላይ ሽጦጥ እንዳሉ ከሩቅ ሲታዩ ከተማዋን ከጠላት ለመጠበቅ በተጠንቀቅ የቆሙ ወታደሮችን ይመስሉ ነበር። በእነዚህ አረንጓዴ ተራራዎች መካከል የሚገኙት የእርሻ ቦታዎች ደግሞ በጣም የለሙና የተለያዩ ቀለማት ባሉዋቸው አበባዎችና ዛፎች ያሸበረቁ ነበሩ። ሜዳቸውም ለከብቶች ግጦሽ በጣም ያመቹ ነበረ። ናዝሬት በዙሪያው ባሉ ሽፋኖች እንደተከበበ ጽጌረዳ ሆና ከተራራው መካከል ትታይ ነበረ። ከተማዋም በድቡባዊ ምዕራብ ክፍል በተራራው አርከን ላይ አቀማመጡ ዘቅዘቅ ባለ ሸለቆማ ሥፍራ ላይ ሆና ትታያለች። በከተማው ውስጥ የሚታይ ሌላው አስደናቂ ሥፍራ ቢኖር ደግሞ ለመለኩሲዎች የማምለኪያ ሥፍራ እንዲሆን ነጭና ቡናማ ቀለም ባሉት ሽፋን የተከለለው ቦታ ነው።

## ሃይማኖታዊ ባሕል

በጊዜው የነበሩት የናዝሬት ከተማ ነዋሪዎች ቁጥር ወደ ስምንት ሺህ ያህል ይደርስ ነበር። ከእነርሱም መካከል አብዛኛውቹ የዚህ ባሕላዊ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው። በተለይ መካከሳቱ የዚህን ባሕላዊ የክርስትና እምነት ትምህርት በተለየላቸው «ቅዱስ ሥፍራ» እየተባለ ይጠራ በነበረበት ቦታ ሆነው ያጥኑ ነበር። ከዚህም በቀር የአምልኮ ሥርዓታቸውን የሚፈጽሙት ገብርኤል ለማርያም የመውለድዋን የምሥራች እንዳበሠረላት በሚያምኑበት ሥፍራ በመሆን ነው። ይህ ቦታ ከአሁን ቀደም እስላሞች ትምህርታቸውን እንዳይበርዙባቸው ለመከላከላ እንደ አጥር የሆነ ትልቅ ቤት ሠርተውበት የነበረ ሥፍራ ነው። ይህ የመከላከያ ቤት ከተሠራበት ሦስት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ደግሞ ናዝራውያን አንድ ቀን ጊዜ ሲያመቻቸው ኢየሱስን ቁልቁል ወርውረው ሊጥሉበት ያዘጋጁት ከፍተኛ ተራራማ ሥፍራ ነበረ። ይህ ተራራም ከፍታው ከ13 እስከ 15 ሜትር የሚሆነው ነበረ። በናዝሬት ከተማ ውስጥ የደናግሎች ምንጭ እየተባለ ይጠራ የነበረውን ሥፍራ ማርያምም ሆነች ሌሎች በሥፍራው የሚኖሩ ልጃገረዶች በየጊዜው ይጐበኙት ነበር። በግሪክ ባሕል መሠረት ይህ የምንጭ ቦታ ገብርኤል ማርያምን ያነጋገረበት ቦታ እንደሆነ ይታመናል።

## የከተማው አካባቢ

ምንም እንኳ የናዝሬት ከተማ ነዋሪዎች ባሕልና ልማድ እርካታ የማይሰጥ ችክ ያለበት ቢሆንም የአካባቢው የተፈጥሮ አቀማመጥ እጅግ ደስ የሚል ነው። ናዝሬትን ከጐበኙት ጐብኚዎች አንዱ ዶክተር ሮቢንሰን ያካባቢዋን ሁናቴ ተመልክተው ከተደነቁባቸው ነገሮች

ብዙዎቹን ገልጠዋል። «አንድ ቀን ብቻዬን ከናዝሬት ከተማ ተጉዢ በሥተ ምዕራብ በኩል ወደሚገኘው ከፍተኛ ተራራ ላይ ወጣሁ እዚያም እንደደረስኩ ዙሪያዬን በዓይኔ እየማተርኩ ስመለከት የናዝሬት አካባቢ በተፈጥሮ ጸጋ የታደለች ከፍተኛ ግርማ ያላት ምድር እንደሆነች አረጋግጫለሁ ብለዋል። በምዕራብ በኩል የኢዝራኤል ሜዳ እስከ ጫፍ ድረስ ለጥ ብሎ ይታያል። በሥተግራ በኩል ደግሞ ከፍ ብሎ የሚታየው የታቦር ተራራ ሲሆን በከፊል የሄርሞንና የጊብዖን ተራራዎች ዝቅ ብለው ጫፎቻቸው በትንሹ ይታያል። በእነዚህ ተራሮች ትይዩ የሰማርያ ተራራዎች እንደ ሰንሰለት ተያይዘው በመራዘም እስከ ቅርሚሎስ ተራራ ይደርሳሉ። ከዚህ በኋላ የቀርሜሎስ ተራራ ራሱ በረጅሙ እስከ ሰሜን ጫፍ ድረስ ተቀጣጥሎ በመሄድ ኤልያስ ይኖርበት የነበረውን ገዳም ጭምር አጠቃሎ ያሳያል። በሥተ ምዕራብ በኩል በጠዋት የፀሐይ ብርሃን እርዳታ የሜዲትራንያን ባሕር በጨረፍታ ሿ ብሎ ተኝቶ ይታያል። የቀርሜሎስ ተራራም በረጅሙ ተቀጣጥሎ በመሄድ በመጨረሻ መሠረቱን ከባሕሩ ጥልቀት ውስጥ ዘርግቶ ይቆማል። በሥተ ሰሜን በኩል ዝቅ ብሎ ኤል ቡታፍ የተሰኘው ውብ የሆነው የሰሜን ፍልስጤማውያን ሜዳ ይታያል። ከዚያም ባሻገር የተራራ ቅጥልጥል ከምሥራቅ እስከ ሰሜን ጫፍ ድረስ ተያይዞ ብመዝለቅ አንዱ በሌላው ላይ እየተደራረበ በመጨረሻ የሳፌድ ተራራ በሁሉም ላይ ይሆናል። በተራራ ላይ የተመሠረተችው ከተማም በሩቅ ጉብ ብላ የምትታየው በዚሁ ሥፍራ ላይ ሆና ነው። በስተቀኝ በኩል በሩቅ በሚታየው ሥፍራ ላይ መሠረታቸውን በባሕር ውስጥ የሰደዱ ብዙ ኮረብታዎችና ተራራዎች ይታያሉ። ከመካከላቸውም ረጃጅም የሆኑት ተራራዎች ከበስተጀርባቸው ያሉትን አጫጭር ኮረብታዎችና ተራራዎችን ይከልሉዋቸዋል። በሰሜናዊ ምስራቅ በኩል ያሉትን ተራራዎች ደግሞ የአመዳይ ዘውድ የደፋው ታላቁ የቄርሜሎስ ተራራ ከልሏቸዋል።

## ሕብረትዋ

የዓለም አዳኝ የሆነው ክርስቶስ የልጅነቱን ዘመን ያሳለፈው ከዚህች የናዝሬት ከተማ ዝቅ ብሎ በሚገኘው መንደር ነበረ። በአካባቢዋ የሚታዩት የተፈጥሮ ውበቶች ዓይኖቻችንን እንደሚስቡ ሁሉ በዚሁ ዓይነት ሁኔታ የጌታንም ዓይኖች ሳይስቡ አልቀሩም። እግሮቹም በቅርብ ባሉት ኮረብታዎች ላይ ደጋግመው ሳይመላለሱ አይቀሩም። እርሱም በዚህ ሥፍራ ሆኖ ዓይኖቹን በረጅሙ በመማተር የአካባቢውን የተፈጥሮ ውበት ሳይመለከት አለመቅረቱ አያጠራጥርም። የሰላም ንጉሥ የሆነው ጌታ በጦርነት ምክንያት ብዙ ዘመን ጨኸት ያስተጋባበት የነበረውን ታላቅ ሜዳ ቁልቁል ሳይመለከት አልቀረም።

## ፖለቲካዊ ለውጥ

ጌታ ኢየሱስ ለወንጌል አገልግሎት ከመውጣቱ ቀደም ሲል በይሁዳ ውስጥ ታላቅ የፖለቲካ ለውጥ ተደርጎ ነበር። ገና ክርስቶስ የመጀምሪያውን የፋሲካ በዓል ሳያሳልፍ በፊት የአይሁድ ሕዝብ በአርኬላኦስ ምክንያት በሮም ላይ ያጉረመርሙ ጀመር። በውጤቱም አርኬላኦስ በይሁዳ ላይ አሥር ዓመት ከገዛ በኋላ ከሥልጣኑ ተሻረ። ከዚህ በኋላ ይሁዳ ቀጥታ በሮም ሕግ እየተመራች በሮማውያን ባለሥልጣኖች ትተዳደር ጀመር። ከዚህ በኋላ ይሁዳ ከሮማውያን ግዛቶች እንደ አንድዋ በመሆን በሮማውያን ሕገ መንግሥት ትተዳደር ጀመር። ከዚያም ከፍተኛው የሮም አስተዳደር መኖርያ ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ወደ ቂሣርያ ተዛወረ።

አውግስጦስ ቄሳር በ14 ዓ.ም. በሞተ ጊዜ የማደጐ ልጁ ጢባርዮስ በምትኩ የሮም ንጉሥ ሆኖ ተሾመ። ጢባርዮስ አውግስጦስ ከመሞቱ በፊት ቀደም ሲል አብሮቶ ሮምን በማስተዳደር የሥልጣኑ ተካፋይ ሆኖ ሥርቷል። ከዚያም በሉቃስ 3 ላይ እንደተጠቀሰው መጥምቁ ዮሐንስ ተልዕኮውን ለመፈጸም አገልግሎቱን በአደባባይ ማከናወን ጀመረ። ይህ የዮሐንስ አግልግሎትም በድንገት የሆነ ነገር ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ታስቦበት የነበረ ጉዳይ ነው። በኢየሩሳሌም የሚኖረው የሮም አገር ገዢ ምንም ዓይነት ዝና ያለማግኘቱ ጉዳይ በእርሱና በሊቀ ካህኑ መካከል ብዙ አለመግባባት እንዲፈጥር አድርጓል። ከዚህ አለመግባባት የተነሣም አገረ ገዢው ሊቀካህኑን ከሥልጣኑ አውርዶ ስለነበር በውጤቱ ብዙ ለውጦች ሊከሰቱ ችለዋል። ከዚያም ጌታችን ኢየሱስ በተሰቀለበት ወቅት ባልታወቀ መንገድ የሊቀካህኑን ሥፍራ ይዘው የሚመሩት ሐናና የልጁ ባል የነበረው አማቹ ቀያፋ ነበሩ፤ ሉቃስ 3፡2። ከዚህ በኋላ ጨካኝና ነፍሰ ገዳይ የነበረው ጲንጤናዊው ጲላጦስ የሮም መንግሥት ወኪል ተደርጐ በንጉሥ ጢባሪዮስ ትዕዛዝ ወደ ኢየሩሳሌም ተላከ። ብዚያን ጊዜ ሄሮድስ በገሊላ አገረ ገዢ ነበረ። ወንድሙ ፊልጶስም በኢጡርያስና በጥልኮደስ አገረ ገዥ ነበረ። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ከሞተ በኋላ በነበረው ዘመን ሁሉ በሥልጣን ላይ ቆይተው ያስተዳድሩ ነበር።

## የሃይማኖት ሁኔታ

በዚህ ሥፍራ በጌታ ዘመን ስለ ነበረው የሃይማኖት ሁኔታ ብዙ ማተት እንብዛም የሚያስፈልግ አይሆንም። በዚያን ዘመን የነ ሳሙኤል፥ ዳዊትና ኤርምያስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸው ሰዎች ታሪክ በየስርቻው ተወሽቆ ቀረ እንጂ ወደ አደባባይ ተገልጦ አልወጣም ነበር። በጊዜው በህዝቡ ዘንድ የሚታየው ሃይማኖት ስርዓታዊ፥ ውጫዊና ባሕላዊ መልክ የያዘ ብቻ ነበር። ሰዎቹም ባለፈው ነገር ላይ በመታመን እጅግ እየተኩራሩ የመንግሥተ ሰማያት ወራሾች እንደሆኑ ይመጻደቃሉ። እነርሱም በጊዜው ይጠባበቁት የነበረው መሢህ የእስራኤልን መንግሥት እንደ ገና የሚያቋቁምና እስራኤልን በዳዊትን በሰለሞን ዘመን ከነበራት ክብር በላቀ ሁናቴ የሚያስከብራት እንደ ሆነ ነው። ስለዚህ አሁንም ቢሆን ይህ ምኞታቸው የሚፈጸመው እግዚአብሔርን በከፍተኛ ሁናቴ በማምለክ፥ ሕጉን አጥብቆ በመፈጸም፥ ስርዓቱን ሁሉ ጠንቅቆ በመጠበቅና የተስፋውን ቃል ኪዳን በትዕግሥት በመጠበቅ እንደሆነ ያምናሉ።

# የዮሐንስ አገልግሎት

ጌታችን በናዝሬት ታላቁን ሥራ ለመጀመር እየተዘጋጀ ሳለ ዮሐንስ ደግሞ በዳር አገር ሆኖ ለተጠራበት ተልዕኮ ብቁ የሚያደርገውን ዕውቀት ለመገብየት በትጋት ይሠራ ነበር። እርሱም ካህን እንደመሆኑ መጠን ስለ ሕግና ነቢያት ማወቅ የነበረበትን ከፍተኛ ዕውቀት ገበየ። ምናልባትም ትምህርቱን ያጠናቀቀው ወደ 30 ዓመት ዕድሜው ገደማ ሳይሆን አይቀርም። እርሱም የአደባባይ አገልግሎቱን እስከጀመረበት ዕለት ድረስ በዚያው በዳር አገር ኖረ። በዚያን ዘመን ይህ ዮሐንስ ያጠናው ኮርስ እንግዳ ነገር አልነበረም። ብዚያ በረሃማ ሥፍራ የሚኖሩት ዮሐንስን ሕግና ነቢያትን ያስጠኑት መመህራን ብቻ ሳይሆኑ የራሳቸው የሆኑ የተለያዩ ፍልስፍና የነብሩዋቸው የተለያዩ መምህራንም ነበሩ። ጆሲፈስ ከእነዚህ መምህራን መካከል አንዳንዶቹ የዘማዊነትና የሌላም እርኩሰት ሀሳብ ያለበትን ትምህርት የሚያስፋፉ

መሆናቸውን ተናግሯል። እነዚህ መምህራን እነሰም በዛ የየራሳቸው ተከያዮች ነበሩዋቸው። ራሱ ጆሲፈስ በዚህ ገዳም በነበረበት ጊዜ በገዳሙ ውስጥ ብዙ ዘመን ኖሮ የነበረውን ባኑስ የተባለውን ሰው ፍልስፍና ለሦስት ዓመት ያህል ተከታትሎ ወደ ከተማ ተመልሷል። ከባኑስ ፍልስፍና መካከልም አንዳንዶቹ ከዛፍ ቅጠል መልበስ፥ ከምድር የተገኘ ማናቸውንም ነገር መብላትና ከበደል ለመንጻት ዘወትር ጠዋትና ማታ በቀዝቃዛ ውኃ መታጠብ ነበሩ። በመጀመሪያ ጊዜ ዮሐንስ በምድረ በዳ በነበረበት ጊዜ በትምህርታቸው ሊያጠምዱት የነበሩት የበረሃ አውሬዎች እነዚህ ነበሩ። እነርሱም ሰፍራው የነበሩት በኬብሮን ምስራቅ በጨው ባሕር አካባቢ ነበረ። ዳዊት ከሳኦል በሸሸ ጊዜ የተሸሸገው በዚሁ በኬብሮን ነበረ። ዳዊት በኬብሮን በነበረበት ጊዜ ስለ መዝሙሮቹ ያሰላሰለው በተለይም ሊመጣ ስላለው ስለ መሢሁ መንግሥት የደረሰው በዚህ ሥፍራ በነበረበት ጊዜ ነው። ዮሐንስ ስብከቱን በጀመረበት ወቅት በተለይም ለማጥመቅ በተነሣ ጊዜ ምድረ በዳውን ለቆ ወደ ዮርዳኖስ አካባቢ መጣ።

## የኢየሱስ መጠመቅ

ዮሐንስ በሕግና በነቢያት ተነግሮ የነበረውን የጥምቀቱን ጉዳይ በተግባር ያሳያል። እርሱም አይሁዶች ለመንፈሳዊ አባቶችና ለተቀበሉት ወግ የነበራቸውን አክብሮት በተመለከተ ጊዜ ከሁሉ የላቀውን እግዚአብሔርን ለማክበርና ትዕዛዙን ለመፈጸም ልቡ ይበልጥ ተነሳሳ። በተለይ በጊዜው ይታይ የነበረው ኃጢአት ፈጥኖ ለሰዎቹ የንስሐ መልዕክት እየሰበከ የጥምቀት አገልግሎቱን እንዲፈጽም አድርጎታል። ከዚህ ቀደም ሲል ግን ዮሐንስ ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንደ ቀላል ነገር መቁጠራቸው እጅግ አሳዘነው፤ የሚያመጣውም መቅሰፍት ደግሞ በጣም አስፈርቶታል። ስለዚህ ግማሽ በሐዘን ግማሽ በፍርሃት መንፈስ በመሆን ወቅሷቸዋል። በኋላም ሁሉም ንስሐ እንዲገቡ ሲጠይቅ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባ እንዳለች በማሳሰብ ነበረ። ከዚያም መልዕክቱን የተቀበሉትንና ንስሐ በመግባት የኃጢአት ሥርየት ለመቀበል የተዘጋጁትን አጠመቃቸው። ዮሐንስ መልዕክቱን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ራሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ደጋግሞ ይመሰክር ነበር። ሆኖም በአንጻሩ ክርስቶስ ከእርሱ በኋላ ሊመጣ ያለው እንደሆነ ተናግሯል። ይህ ከእርሱ በኋላ የሚመጣው ጌታ ዮሐንስ የጫማውን ክር ለመፍታት የማይገባው እስከሆነ ድረስ የተከበረና ታላቅ ነው። ዮሐንስ የሚናገረውንም ለመስማት ብዙ ሠራዊት ይከተለው ነበር። በአጠቃላይ የአካባቢው የመንፈስ አሠራር ከአሁን ቀደም ተከስቶ የማያውቅ አዱብ ድንቅ ነበረ። በዚህ ጊዜ አብዛኛዎቹ ሰዎች የመንፈስ ተመስጦ አድሮባቸው ለዳግመኛ ልደት የሚያበቃቸውን የሕይወት ለውጥ በዳዊት፥ በሰለሞንና በሕዝቅያስ ዘመን በነበረው ሁኔታ በእምነት ተቀበሉ። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ራሱ ምናልባት ከናዝሬት በኢዝራኤል ሜዳ አድርጎ ወደ መጠመቂያው ሥፍራ ከመጣ በኋላ ተጠምቆ ይሆናል። ዮሐንስ ኢየሱስን ለማጥመቅ ብቁ ሰው አለመሆኑን በመገመት አይሆንም በማለት ይግደረደራል። ኢየሱስ ግን የግድ ብሎት ይጠመቃል። ከዚያም ከመቅጽበት ሰማይ ይከፈትና መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል በኢየሱስ ላይ ያርፋል። ወዲያውም «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ። በሌላ ጊዜም ኢየሱስን በማስመልከት ዮሐንስ «እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ» ብሎ መሰከረለት። ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት ተሸክሞ መስዋዕት ሊሆን እንዳለው ዮሐንስ አረጋግጦ ያውቅ እንደነበረ ያስረዳል።

# ሄሮድስ አንቲጳስ - የዮሐንስ ሞት

የዚህ ጨዋ ሰው ድፍረትና አገልግሎት ከ12 ወይም ከ18 ወራት በኋላ የገሊላ ገዢ በነበረው በሄሮድስ አንቲጳስ ተቀጥቶ ተቋረጠ። ዮሐንስ በድፍረትና በታማኝነት መልዕክቱን አስተላልፎለታል። በጥንት ዘመን ነገሥታት በውበታቸው እስከተማረኩ ድረስ የየራሳቸውን ሚስቶች ፈትተው የሌላውን ሰው ሚስት በሥልጣናቸው መንጠቅ የተለመደ ተግባራቸው ነበር። አውግስጦስ ቄሣር ራሱ ይሄን አስነዋሪ ተግባር አዘውትሮ ያደርግ ነበር። ከዚህም በቀር ሌሎቹም ይህንኑ ተግባር እንዲፈጽሙ ያደፋፍራል። ይህ አፈጻጸም ከሄሮድስ ቤተሰብ ልማድ ስለሆነ ሕዝቡ ይሄንኑ ልማድ እንዲከተል ይገደድ ነበር። በዚህ ሁኔታ ሕብረተሰቡ ሞራል ስለጐደለው በብዙ ምስቅልቅልና ጉስቋላ በሆነ ርካሽ ባሕል ውስጥ ሊወድቅ ችሏል። ሄሮድስ የወንድሙን የፊሊጶስን ሚስት በማግባቱ ዮሐንስ በተለመደው ድፍረቱ ያደረከው ነገር ኃጢአት ነው ብሎ ፊት ለፊት ተቃውሞታል። በዚህ ምክንያት ዮሐንስ በውህኒ ቤት ተጥሎ ነበር። ይህ በዚህ እንዳለ ሄሮድስ ባዘጋጀው ትልቅ ግብዣ ላይ የወንድሙ ልጅ በዘፈንዋ ስላስደሰተችው የፈለገችውን ነገር ብትጠይቀው እንደሚያደርግላት ቃል ይገባላታል። በዚህን ጊዜ ምርጫዋን ለማስተካከል እናትዋን ካማከረች በኋላ በግዞት ያለው የዮሐንስ ራስ እንዲሰጣት ትጠይቃለች። ንጉሡ በጥያቄዋ ሀሳቡ ቢታወክም የገባውን ቃል መፈጸም ግዴታው ስለ ነበር የዮሐንስን አንገት አስቀርጦ ሰጥቷታል። ዮሐንስ የታሠረበት ከዮርዳኖስ ምስራቅ መቃሪየስ በሚባልበት ቦታ እንደሆነ ይታመናል። ከዚህ በኋላ ሄሮድስ በአግባብ ያልያዘውን ሥልጣኑን ብዙ አልተጠቀመበትም። ሊመጣበት የነበረው ችግር የተመሠረተው ከሄሮድያዳ ቤተሰብ ጋር የመሠረተው የጋብቻ ግንኙነት ነው። የመጀመሪያ ሚስቱ የአረብ ንጉሥ የነበረው የአርስጦስዮስ ልጅ ነበረች። ሳይግባቡ ቀርተው ስለተጣሉ ሸሽታ ወደ አባትዋ ዘንድ ሄደች። በኋላም አባትዋ ከሄሮድስ ጋር ተዋግቶ ድል ካደረገው በኋላ መንግሥቱን ያዘበት። ከዚያም ሄሮድስ በሮም እያለ ከክብሩ ተዋርዶ ከቆየ በኋላ ወደ እስፓኝ ተሰደደ። በዚያም ከነቤተሰቡ እየኖሩ ሳለ በመጨረሻ በውርደት ተጐሳቁሎ ሞተ።

# የኢየሱስ መፈተን

ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ። በዚያም በሠይጣን ተፈተነ። ሠይጣንም ኢየሱስ የተለየበትን ቅዱስ ተግባር እንዳይፈጽምና በአባቱ ላይ የነበረውን መተማመን ለማደናቀፍ በሦስት ዓይነት ፈተናዎች ፈትኖታል። በመጀመሪያ ድንጋዮቹን ወደ ዳቦ እንዲለውጥ፤ ቀጥሎም ከቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ ራሱን እንዲወረውር፥ ከዚያም ወድቆ እንዲሰግድለት ጠይቆታል። ኢየሱስ ለእነዚህ ሁሉ የፈተና ጥያቄዎች መቋቋሚያ ከእግዚአብሔር ቃል እየጠቀሰ ተገቢውን መልስ ሰጥቶታል። ኢየሱስ በሠይጣን የተፈተነበት ሥፍራ በኢየሩሳሌምና በኢያሪኮ መካከል በሚገኘው በረሃ ውስጥ ነው ይባላል።

## አገልግሎቱን መጀመር

ከፈተናው በኋላ ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ወደሚያጠምቅበት ቦታ ተመልሶ ይመጣል። በዚያም ስምዖን፣ ፊልጶስ፣ ዮሐንስና ናትናኤል ደቀ መዛሙርት ሆነው ይከተሉታል። እነርሱም ኢየሱስን ሊከተሉት የቻሉት የእግዚአብሔር ልጅና የዓለም አዳኝ መሆኑን ስላረጋገጡ ነው። እነሆ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ እውነትንና ጸጋን ተሞልቶ ተገለጠ። ደቀ መዛሙርቱም ጥቂት ወራት ከኢየሱስ ጋር ከቆዩ በኋላ ሐዋርያት ተብለው ተሰየሙ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በቃና ዘገሊላ ተደርጐ በነበረው ሠርግ ላይ አገልግሎቱን ጀመረ። በዚያም ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የመጀመሪያ ተአምራቱን ፈጽሟል። በተለይ ደግሞ ተአምራቱ የተፈጸመው በጋብቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ስለሆነ ኢየሱስ ለሰው ልጅ የጋራ ደስታና ለትዳር ክቡርነት ያለው ቅዱስ አመለካከት ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። በተጨማሪም ተአምራቱን ሲፈጽም ሰዎች እንደሚሉት የማርያም ልጅ ብቻ ሳይሆን የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አረጋግጧል። ሰው በተፈጥሮ ችሎታው ሊፈጽመው የማይችለውን ተአምራት አደረገ። ለዚህ እውነትም ድጋፍ ይሆነው ዘንድም እናቱን «አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ብሏታል። በዚህ ሁኔታ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተቀባው መሲህ መሆኑን በግልጽ አሳውቋል።

## ኢየሱስ በይሁዳ ያደረገው አገልግሎትና የቤተ መቅደስ መንፃት

የመጀመሪያው የጌታችን ዋነኛ አገልግሎት የተፈጸመው በይሁዳ ነበረ። ኢየሱስ ከቃና ዘገሊላ ከተመለሰ በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ ነጋዴዎችን አስወጣ። ይህንንም ያደረገው ለጸሎት ቤትነት የተሠራውን የአባቱን ቤት የንግድ መለዋወጫ ሥፍራ እንዳይሆን ለመጠበቅ ብሎ ነው። በቃና ዘገሊላ የተደረገው ተአምራት የትዳርን ክቡርነት ይበልጥ ከፍ ማድረጉን የሚያሳይ ምልክት ሆነ፤ ቤተ መቅደሱን ከነጋዴዎች ማጥራቱ ደግሞ ለእግዚአብሔር አብ ያለውን ታላቅ አክብሮትና የማምለክን ቁም ነገር እጅግ አልቆ የሚያሳይ ይሆናል።

## ኒቆዲሞስ

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር ስላደረገው ንግግር የሚተርከው ሀሳብ ይቀጥላል። የንግግሩም ዋና ርዕስ ስለ ሰው ልጅ ደኅንነትና የኃጢአት ሥርየትን የሚመለከት ነበረ። እርሱም በንግግሩ ውስጥ «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም» ብሏል። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከጥፋት የሚያድንበት የደኅንነቱ ፀጋ የማይታጠፍ ነው። በምድረ በዳ ውስጥ ለዚህ ድርጊት ምሳሌ እንዲሆን እባብን ሰቅሏል። ይህ ኢየሱስ ለአይሁዶች የሚሰብቅው የወንጌል አገልግሎት እስከ መቼ ድረስ የሚቆይ ነው? ውጤቱስ ምንድር ነው? በዚህ አንጻር የደረሰን መግለጫ የለም።

## ሳምራዊቱ ሴት

ከዚህ ቀጥሎ ኢየሱስ ወደ ገሊላ እንደተጓዘና በዚያም ከአንዲት ሳምራዊት ጋር በያዕቆብ ምንጭ አጠገብ ይነጋገር ጀመር። ንግግሩም ከበደል ስለ ማንጻትና ስለ ደኅንነት አስፈላጊነት ነበረ። በዚሁ ሁኔታ ኢየሱስን እንደ ገና ከሌላ ግለሰብ ጋር ሲነጋገር እናገኘዋለን። ሳምራዊቱን ሴት ግን ያነጋገራት ታሪኳ የተበላሸና በግልጽ አጥፊና በደለኛ ሴት እንደ ሆነች በሚያጋልጥ ሁኔታ ነበር። ያም ሆን ይህ ለሁለቱም የወንጌሉን የምስራች ቃል ሰብኰላቸዋል። ለሴቲቱ ስለ ደኅንነት የሰበከላት ውኃ ለተጠማ ሰው ከሚሰጠው እርካታ ጋር በማያያዝ ሲሆን ስጦታውም ጡፃ እንደ ሆነ በመግለጽ ነበረ። ኢየሱስም፦ «የእግዚአብሔርን ሥጦታና ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑን ብታውቂ አንቺ ትለምኚው ነበርሽ፤ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር» አላት።

## ገሊላ፥ ቅፍርናሆምና ናዝሬትን እንደጐበኘ

የሚቀጥለው ረጅሙ የጌታ አገልግሎት የተከናወነው በገሊላ ነበር። ኢየሱስ ቀድሞ ይኖርበት ከነበረው ከናዝሬት ተነስቶ በገሊላ ባሕር አካባቢ በምትገኘው በቅፍርናሆም ዋና የአገልግሎቱን ሥፍራ መሠረተ። ቅፍርናሆም የተመሰረተበት ትክክለኛ ቦታ በውል አይታወቅም። ሆኖም ከገሊላ ባሕር ሰሜናዊ ምዕራብ በኩል በሚገኘው ሜዳ ላይ መሆኑ አያጠራጥርም። ቅፍርናሆም በውስጡ ከሚከናወኑት አፋጣኝና አጣዳፊ ተግባሮች አንጻር ከናዝሬት በጣም ይለያል። በጥቂቱ ጌታችን አንድ ጊዜ ናዝሬትን ለመጐብኘት ሄዶ በዚያው ነዋሪ ሆኖ እንደቀረ እናነባለን። ኢየሱስም በሰንበት ወደ ምኵራብ ገብቶ ከኢሳይያስ 61 ላይ በማንበብ በመንግሥቱ ስለሚገኘው መንፈሳዊ በረከት ሰብኳል። የናዝሬት ሕዝብ ተአምራትን ከመሻት ሌላ ለመንፈሳዊ ነገር ምንም ዓይነት ፍላጐት አልነበራቸውም። ኢየሱስም የጠየቁትን ተአምራት ባለማድረግ ስላስከፋቸው ይዘውት ከተማው ከተመሰረተበት ከተራራው ጫፍ ቁልቁል ሊጥሉት ሲሉ ከፊታቸው በተአምር ተሰውሮ አመለጠ። ከዚህ በኋላ ቅፍርናሆም በማያወላውል ሁኔታ «የእርሱ ከተማ ሆነች።» የከተማይቱም ወንዝ ከቦታው ወደ ሩቅ ሥፍራ በመፍሰሱ በምሳሌነቱ ኢየሱስም ሌላ ከዚህ የራቀ ቤት እንዳለው ያመለክት ነበር።

## የገሊላ ባሕር የጐብኚዎች አስተያየት

በተለያዩ ጊዜያት የገሊላን ባሕር የጐበኙት ሰዎች ስለ ባሕሩ የሰጡት አስተያየቶች የተለያዩ መሆናቸው የሚደንቅ ነው። በአጠቃላይ አብዛኛዎቹ ተመልካቾች ስለ ባህሩ የሰጡት አስተያየት ትዝታው ከአዕምሮ ሊሰረዝ የማይችል ዓይነት እንደሆነ ይናገራሉ። ዶክተር እስታንሊ ግን ስለ ውበቱ የሰጡት አስተያየት ባይኖርም የተፈጥሮ አቀማመጡ ከቀሩት ባሕሮች ሁሉ ብዙ የተለየ እንደሚያደርገው ጠቅሰዋል። እርሳቸውም መጠኑን ሲገመግሙ ቁመቱ 16 ኪሎ ሜትር ሲሆን ጐኑ ደግሞ 8 ኪሎ ሜትር እንደሚሆን ገምተዋል። ይህን ባሕር ከቀሩት ባሕሮች ልዩ የሚያደርገው እንደ ጨው ባሕር ጥልቀቱ ወሰን የሌለው መሆኑ ነው። በምስራቅ በኩል ተራራዎቹ ለጥ ያሉ ናቸው። በስተ ምዕራብና በስተ ሰሜን ደግሞ አቀማመጡ

ለየት ያለና ደስ የሚል ዓይነት ነው። አቀማመጡም ልክ እንደ አጥር ዙሪያውን በተከበቡ አለቶች መካከል ስለሆነ ጉብኚዎች ሽቅብና ቁልቁል ሲወርዱ በተለይ የቆላ ተክል በሆኑት እንደ ዘንባባ ባሉ አትክልቶች መካከል ይገናኙ ነበር። በጥብርያዶስ አካባቢ የሚገኘው ፍልውኃ ከረጅም ጊዜ በፊት በእሳተገሞራ የተፈጠረውን የአካባቢውን ለውጥ ያሳያል። ፍልውኃም እስከ ዛሬ ድረስ አገልግሎቱን እንደቀጠለ ነው። በባሕሩ ዙሪያ በማዕበል የተገፉት አሸዋዎች ተጠራቅመው መቀነት የመሰለ ከፍተኛ መደብ ሠርተዋል። ተራራውም ሽቅብ የወጣው ከእነዚህ ከአሸዋ ከምሮች ጥቂት እልፍ ብሉ ከሚገኘው ሥፍራ ተንስቶ ነው። ብዙ ጊዜም ከተራራው ጥግ ዘቅዘቅ ሲል ከበቀሉት ሣሮች ራስጌ ከሚገኙ ተክሎች ጥሩ ሽታ እየወጣ አካባቢውን ያውደዋል። በስተ ምዕራብ በኩል የሚገኙት በዛ ያሉ የውኃ ምንጮች በስተ ምስራቅ በኩል ያሉት ቦታዎች ያላገኙትን ልምላሜ ለአካባቢያቸው ሰጥተውታል።

## የጌንሴሬጥ ሜዳ

በሰሜናዊው ምዕራብ በኩል የሚገኘው አንደኛው ክፍል የባሕሩ ዳርቻ ቁመቱ ስድስት ኪሎ ሜትር ጐኑ 3 ኪሎ ሜትር የሆነ ሜዳማ ቦታ አለው። ይህም ሜዳማ ቦታ ለም ስለሆነ ለእርሻ በጣም ምቹ ነበረ። መልካም ፍሬን ይሰጥ ስለነበር ከክርስቶስ ትምህርትና ተግባር ጋር ተመሳሳይነት አለው። በእርሻውም ውስጥ መሬቱን እየዞሩ የሚያጠጡ የአራት ምንጭ መስኖዎች ይፈሱ ነበረ። በሌላ አንጻር ደግሞ ለስፍራው ድምቀትን የሰጡት የበቆሎ ተክሎች የመሬቱን ለምነት ያሳያሉ። ከዚህም በቀር በአካባቢው የሚገኙት ጥቅጥቅ ያሉት እሾሃማ ቁጥቋጦዎች በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ አእዋፋቶች መኖሪያ ለመሆን ታድለው ነበር። በጠቅላላው የጌንሲራጥን ሸለቆ ስንመለከት ምድሪቱ በሉጥ ዘመን የነበራትን ልምላሜ በሌላ አንጻር እንድንመለከት ያደርገናል። «ውኃ የሞላበት በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለው አገር እግዚአብሔር ሰዶምና ጎመራን ከማጥፋቱ አስቀድሞ እስከ ዘዓር ድረስ እንደ እግዚአብሔር ገነት በግብፅ ምድር አምሳል ነበረ።»

## ከተሞች

በጌታችን ዘመን የኃይቁ ሰሜናዊ ምዕራብ ዳርቻዎች በሙሉ በከተማዎችና በመንደሮች ጥቅጥቅ ያሉ ነበሩ። ከእነዚህም መካከል ቅፍርናሆምና ኮራዚ እንዲሁም የቤተ ሳይዳና መጌዶል ይገኙባቸዋል። አንዳንዶቹ ከተማዎች ማን እንደሆኑ እስከማይለዩ ድረስ ችምችም ያሉ ነበሩ። በቅፍርናሆም አካባቢ የሚኖሩት ሰዎች የመሬት ባለይዞታዎች ብቻ ሳይሆኑ በዓሣ አጥማጅነት ሥራም የተጠመዱ ነበሩ። በተለይ በኃይቁ ምስራቅና ምዕራብ ክፍል የሚገኙት ሁለቱ የቤተሳይዳ መንደር ነዋሪዎች ዓሣ በማጥመድ እጅግ የታወቁ በመሆናቸው የዓሣ ቤት የሚል ቅጥያ ስም ተሰይሞላቸዋል። ስለዚህ ከአካባቢው መንደሮች በቀን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዓሣ አጥማጆች ለሥራ ይሠማራሉ። በተለይ በእነዚህ ላይ መርከብ ጠጋኞቹና በውኃው ላይ የሚንሳፈፉት ታንኳዎች ሲደመሩ ኃይቁ ለጤፍ መጣያ ሥፍራ የለውም ነበር። ከኃይቁ ትንሽ ወጣ ብለው ባሉት ሥፍራዎች ላይ ደግሞ የሮማውያንና በአይሁድ ቤተ መንግሥቶች፣ ምኩራቦችና ቤተ መቅደሶች ደምቀው ይታያሉ። በተለይ አረቦችና ጽዮናውያን በታላቅ

ሥልጣኔና መሻሻል በሚገኙበት በአሁኑ ዘመን ሥፍራዎቹ በብዙ ዓይነት ዘመናዊ የሥራ እንቅስቃሴዎች ተይዘው ይታያሉ።

## የዓሣ ማጥመድ

ገሊላ ብዙ ሕዝብ የሚኖርበትና የዓሣ ፋብሪካ የመሰለ ሥራ ባፋጣኝ ተግባሩን የሚያከናውንበት ቦታ ነው። ብዙ ጊዜ መንገደኞችና ነጋዴዎች ወደዚህ ሥፍራ ስለሚመጡ የክርስቶስ ዝና በቀላሉ ፈጥና ራቅ ወዳሉ አገሮች ሁሉ ይወጣ ነበር። በዚያን ዘመን ከብዙ የተለያዩ አገሮች የሚመጡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች አብዝተው የሚተያዩበት ሥፍራ ቢኖር ይሄው የገሊላ ባሕር አካባቢ ነበር። ብዙ የደከሙና ሸክማቸው የከበደ ሰዎች ሸክማቸውን አራግፈው ተንፈስ የሚሉት በዚሁ ነበር። ጸሐፊዎች ብዕራቸውን ይዘው ከተለያዩ አገሮች የሚመጡትን ሰዎች ባህልና ልማድ ለመመዝገብ ከኃይቁ አካባቢ ተቀምጠው ይጠብቃሉ። የሮም ወታደሮችም በባርነት ሥርዓታቸው የሄሮድስን ምኞትና የቤተ መንግሥቱን ደኅንነት ለመጠበቅ ከጥዋት እስከ ማታ በተጠንቀቅ ቆመው ይጠብቃሉ። በዚህ ዓለም ንዋይ ተደልለው ሀብታሞችንና መርከበኞችን ይከተሉ የነበሩ አመንዝራ ሴቶች ሕይወታቸው ተለውጦ ሥነ ምግባር የተሞላበት ጠባይ ይታይባቸዋል። ይህ ዓይነቱ ጠባይ ክርስቶስን ከሚከተሉት ሰዎች የሚጠብቀው ነበር። እርፉ መሳፍርት የሌላቸው ዓሣ አጥማጆች አሁን ፍላጐታቸው በአዲስ ነገር ተለውጦ ይታያል። ስምዖንና እንድርያስ ከውኃው ዳር ከቆሙት ከሁለቱ ታንኳዎቻቸው ዓሣ ለማጥመድ መረባቸውን እየጣሉ ናቸው። ያዕቆብና ዮሐንስ ደግሞ መረባቸውን ወደ ዳር አውጥተው ሲያጥቡና ሲሰፉ ይታያሉ። እነርሱም ሌሊቱን ሁሉ ሲደክሙ አድረው ምንም አላጠመዱም። ከእነርሱ አልፍ ብለው የዓሣ ቤት እየተባለ ከሚጠራው ከቤተ ሳይዳ የሆኑት ፊሊጶስ፥ እንድርያስና ስምዖን መንጠቆአቸውን ወርውረው የመጀመሪያውን ዓሣ ይይዛሉ። ሁለተኛ ጊዜ መረባቸውን በጣሉ ጊዜ ግን መረባቸው ዓሣ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የባሕር ተንቀሳቃሽ ነፍሳቶችን ሁሉ ይዟል። ከዚያም የማይበሉት ተለቅመው ሲጣሉ የቀሩት በዕቃ ውስጥ ተደርገዋል። እነዚህ በመረቡ ውስጥ የተያዙት የተለያዩ ተንቀሳቃሾች በተለያዩ የዓለም ሃይማኖቶች ይመስላሉ። በመጨረሻው ዘመን ኢየሱስ ሲመጣ በክርስቶስ ያልሆኑት ተለቅመው ወደ እሳት ባሕር ሲጠሉ በክርስቶስ ያሉቱ ለዘለዓለም ሕይወት የጠብቃሉ።

## በአካባቢው ተራራ መካከል የሚገኙ የማረፍያ ቦታዎች

ኢየሱስ በምድር አገልግሎቱን ይሰጥ በነበረበት ዘመን በሥራ ብዛት እርፍትና ፋታ አያገኝም ነበር። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ከሚያገለግላቸው ሕዝቦች መካከል ሰውር ብሎ ከእነዚህ የማረፍያ ተራራዎች ወደ አንዱ ይሄድ ነበር። እርግጥ እንደ ቀድሞው በጸጥታ ብቻውን የሚሆንበትን አመቺ ሥፍራ ለማግኘት ከኃይቁ ዳር ተነስቶ ተራራው ጫፍ እስከሚደርስ ወይም ከዚያ አልፎ ተራራውን አቋርጦ በሌላው የኃይቁ ክፍል እስከሚደርስ ድረስ ጥቂት ሲጓዝ ሳይደክመው አይቀርም። እርሱም ከዚያ ማረፍያ ሥፍራ እንደደረሰ ጥቂት ቀናት በጸሎት አሳልፎአል። ከዚያም ከሐይቁ ሌላኛው ክፍል ወደሚገኘው በረሃማ ሥፍራ ተሻግረው ጥቂት እንዲያርፉ ደቀ መዛሙርቱን ይጠራል። ይህ ጸጥታ የሰፈነበት በረሃም ሥፍራ

ሚሜታና ብዙ መራወጥ ከበዛበት ከጥብርያዶስ ባሕር አካባቢ በእግርም ሆነ በታንኳ ከአንድ ሰዓት በላይ አይወስድባቸውም ነበር።

## የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መሾም

ኢየሱስ ወደ አገልግሎቱ እንደገባ ሰዎች እብዝተው ወደ እርሱ የሚመጡበትን አስደናቂ መንገድ ይጠቀም ነበር። በኋላም ምድራዊ አገልግሎቱን ጨርሶ ወደ አብ ባረገ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ይህንኑ አስደናቂ ዘዴ በመጠቀም ሥራውን ቀጥለዋል። ቀደም ሲል ግን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ባዘጋጀው ተቋም ውስጥ አስልጥኗቸው ነበር። በኋላም ኢየሱስ አንድ ሌሊት ሙሉ በጸሎት ካሳለፈ በኋላ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ጠርቶ ሊለያቸው ሥራ ሾሟቸዋል። ደቀ መዛሙርቱ በኑሮ ደረጃቸው በጣም ዝቅ ካለው መደብ ሲሆኑ በትምህርታቸውም መሃይማን ነበሩ። ቢሆንም ኢየሱስ ከፍ ከፍ አድርጐ የእርሱ አገልጋዮች ሊሆኑ ወደሚችሉበት ደረጃ አድርሷቸዋል። ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ መካከልም ሦስቱ በእርሱ ዘንድ ልዩ ሥፍራ ተሰጥቷቸው ነበር። እነርሱም ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብ ነበሩ። እነዚህ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ባገልግሎቱ ዘመን ሁሉ ኢየሱስን በእውነትና በታማኝነት ተከትለውታል። ይህንንም ከእርሱ ጋር በነበራቸው የቅርብ ግንኙነት በተግባር አስመስክረዋል። ሆኖም በአገልግሎታቸው መካከል አንድ ቀን አንድ አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጽሞአል። ይኸውም አስቆሮቱ ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ መስጠቱ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ይሁዳ አስቆሮቱ በሥጋ እንጂ በመንፈስ ስላልነበረ እነርሱ የደረሱበትን ከፍተኛ መንፈሳዊ ደርጃ በቃል እንጂ በሕይወቱ አያውቀውም ነበር።

## የክርስቶስ አገልግሎትና የተራራው ስብከት

ጌታ ኢየሱስ ዋነኛው የአግልግሎቱ ሥፍራ አድርጐ ሲጠቀምበት የቆየው ገሊላን ነበር። ቢሆንም በቀረው የአይሁድ አካባቢ የሚኖር ሕዝብ መጥቶ የበረከቱ ተካፋይ ለመሆን መብቱ የተጠበቀ ነው። ከዚህ የተነሣ ከአካባቢው ሁሉ ብዙ ሰው ወደ እርሱ በመጉረፍ አድማጩ ታላቅ ጉባዔ ሆነ። ከዚህ በቀር በተለያዩ ብዙ ጊዜያት ሰዎች ወደ ኢየሱስ እየመጡ ቃሉን ያዳምጡ ነበር። በተለይ አንድ ጊዜ ኢየሱስ በእጁ አንድ ማስታወሻ ይዞ ከፍታው 20 ሜትር ወደሚሆን ተራራ ላይ ብዙ ሕዝብ አስከትሎ ወጣ። የተራራው አቀማመጥ አራት ማዕዘን ከመሆኑ በላይ ጥቂቱ የተራራ ክፍል እንደ መድረክ ሆኖ ከፍ ያለና የቀረው ደግሞ ደልዳላ ነበር። በተራራው ላይ የነበረው ሕዝብ እጅግ ብዙ ስለነበረ በሩቅ ተራራውን ለተመለከተ ሰው ተራራነቱን መለየት ያስቸግር ነበር። በአጠቃላይ በተራራው ላይ የተሰጠው መልዕክት ቀጥታ የወንጌል ቃል ባይሆንም የሰውን ልብ ለወንጌል ቃል የሚያዘጋጅ ነበር። የመልዕክቱ ዋና ሀሳብ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲሆን በመንግሥቱ ውስጥ ስለሚሆነው አስተዳደር፥ አገልግሎት፥ መንፈስ፥ ፍሬ ወይም ውጤት የሚያጠቃልል ነበረ። ኢየሱስ አንዳንድ ጊዜ በንግግሩ ውስጥ ጣልቃ እያስገባ በረከትን የሚሹና የሚናፍቁ ሰዎች እንደሚረኩ ወደ ፊት ሊሆንላቸው ያለውን በማስመልከት ይናገር ነበር። ከንግግሩ መካከልም አንዱ «በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁአን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና» የሚል ነው። ይህ አነጋገር የእግዚአብሔር በረከት ምን ያህል የከበረና የተትረፈረፈ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። ከዚህ

በቀር ጌታ ኢየሱስ በንግግሩ ውስጥ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ከሙሉ ቸርነቱ ጋር ምን እንደሚመስል አስረድቷል። በቸርነቱ ሳይጠቀም ከሕጉ ዝንፍ ያለውንም ለመቅጣት ጨካኝ እንደሆነ ገልጿል። በተለይ ወደፊት በፍርድ ቀን በስምህ ይህንና ያንን አላደርግንምን እንደሚሉት ጠቅሷል። እርሱ ግን ይህን ቃል እየተናገራቸው ሳለ ለምሕረትና ለደህንነት የተላከላቸው መሢህና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አስረድቷል።

## ሥዕላዊ መግለጫ

ኢየሱስ መልዕክቱን በምሳሌ ለማስረዳት እንዲችል በአካባቢው የሚታዩትን ነገሮች በማስረጃነት ይጠቀም ነበር። ከእነዚህም መካከል አብዛኛዎቹ የሚዳ አበባዎች፣ በሐይቁ ዙሪያ በጥሻው ውስጥ የሰፈሩት ወፎች፣ በአየር ላይ የሚንሳፈፉት አሞራዎች፣ እርሻዎች፣ አለቶችና ምድረበዳዎችን የመሳሰሉት ሁሉ ናቸው። ከምሳሌዎቹም ውስጥ አንዳንዶቹ ይህን ይመስላሉ፦ «አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን?» ከዚህም በቀር ኢየሱስ ስለ ጠባቡና ስለ ሰፊው መንገድ በምሳሌ በሚያስተምርበት ጊዜ በፊቱ የሚታይ ታላቅ አውራ መንገድ ተዘረግቶ ሊሆን ይችላል። በአለት ላይ ቤቱን ስለሠራው ብልህ ሰውና አሸዋ ላይ ቤቱን ስለሠራው ሰነፍ ሰው ሲናገርም በሐይቁ ዳር ባሉ አለቶችና በውኃው ዳር በአሸዋ ላይ የተሠሩትን ቤቶች ተመልክቶ ይሆናል።

## ምሳሌዎች

ኢየሱስ ትምህርቱን ለማስረዳት ከሚጠቀምባቸው ምሳሌአዊ ገለጻዎች መካከል የሰውን ጠባይ በማስመልከት የሚመስሳቸውን ምሳሌዎች የሚያክል የለም። በጠቅላላው ኢየሱስ የተጠቀመባቸው ምሳሌዎች 47 ሲሆኑ ከፊሉ የተሰወረውን እውነት ለመግለጽ ሲረዱ የቀሩት ደግሞ እውነቱን በውስጥ ሸፍነው የሚይዙ ናቸው። ያም ሆነ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር የሚጠቅመው የአድማጩን ሕዝብ ጥያቄ ለመቀስቀስ ወይም ለማነሳሳት ነው። በዚህ ጥያቄ ምክንያትም እውነትን የሚፈልጉ ሰዎች እውነትን ወደማወቅ ይደርሳሉ።

## ዘሪው

በጥብርያዶስ አካባቢ ከሚታየው ተፈጥሮአዊ ድምቀት ይልቅ ስለ ዘሪው የተነገረው ምሳሌያዊ አገላለጽ የበለጠ ለዛና ሞገስ ይታይበታል። በሐይቁ አካባቢ ከተራራው ሥር ተነሥቶ እስከ ጥብርያዶስ ድረስ የሚወርድ ሰፊ የበቆሎ እርሻ ይታያል። በእርሻው መካከልም ሰውም ሆነ እንስሳ የሚመላለስበት መንገድ አለ። እርሻውም አጥር ስላልነበረበት ዘሩ ከግራና ከቀኝ በመንገዱ ላይ ስለሚረግፍ በመንገዱ ላይ የሚመላለሱ ሁሉ ይረግጡታል። ከላይ እንደተወሳው ከተራራው ጥግ ተነሥቶ እስከ ውሃው ዳር በሰፊው የተኛው እርሻ ለም ስለነበረ እጅግ በጣም ብዙ በቆሎ ያፈራ ነበር። አንዳንድ ከተራራው ጥግ የተነሱ አለቶች ሥር በሥር እየሰረጉ በእርሻው መካከልና በማሳ ውስጥ ቁልቁል ወርደዋል። ከዚህም በቀር እልፍ አልፍ እሾሃማ የሆኑ ቁጥቋጦዎች በስንዴው መካከር ውስጥ ጥቅጥቅ ብለው ይታያሉ።

## በጥብርያዶስ ሜዳና በሐይቁ መካከል ያለ ግንኙነት

በዚህ በጥብርያዶስ ሜዳና በጎይቁ አካባቢ የተነገረው የቃሉ ምክር፣ የምህረቱና የፍቅሩ ብዛት፣ እንዲሁም የመንግሥቱ ክብር ምንኛ ታላቅ ነበር! ስለዚህ እኛም ብንሆን የበረከቱ ተካፋይ እንድንሆን ከዚህ መንፈስ መጠጣት አለብን! ይህ መንፈስ ያለማመንን ሀሳብና የመከራን ሸክም ከእኛ ላይ ያስወግዳል! በሠራነው ኃጢአት እየተመቀስን ሸክም በዝቶብናል? እነሆ ኢየሱስ የነበረበት ቤት ጣርያ ተገልጦ ጥቂት እንደ ቆየ «አንተ ልጅ አይዞህ ኃጢአትህ ተሠረየችልህ» የሚል ድምፅ ተሰማ። በውስጣችን ባለ በኃጢአት በሽታ ተሠቃይተናል? ኢየሱስ «ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም! ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» ብሏል። ልዩ ከሆነ ከሠይጣን ፈተና ወይም ከራሳችሁ ልባዊ ድንዳኔ ጋር እየታገላችሁ ነው? ኢየሱስ ቆጵሮስ በሚገኘው ምኩራብ ውስጥ ሆኖ እርኩሱን መንፈስ «ዝም በል ከእርሱም ውጣ» ብሎ ይገሥጸው ነበር። እርሱም እውሮችን ያበራውና ለምጻሞችን ያነፃው በዚሁ ነበር። ሌጊዮን የተባለው በብዙ ሺህ የሚቆጠረው የአጋንንት መንጋ ከሰውየው ወጥቶ በውኃ ዳር ተሰማርተው በነበሩ እሪያዎች ውስጥ የገባው በዚሁ ነበረ። አሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት የልብሱን ጫፍ በእምነት ነክታ በተፈወሰች ጊዜ ኢየሱስ «ልጄ ሆይ እምነትሽ አድኖሻል በሰላም ሂጂ» ያላት እዚሁ ነበር። የሀሳብና የኃጢአት ሸክም ተጭኗችሁ በኀዘን ትንገላወዳላችሁን? ኢየሱስ «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔ አሳርፋችኋለሁ» ብሏል። ለመሆኑ ይህ እምነተቢስ ልባችን አንዳንድ ጊዜ በእምቢተኝነታችን ሊመጥብን ካለ መከራ አስጠንቅቆን ያውቃል? አምስቱ እንጀራና ሁለቱ ዓሣ ለአምስት ሺህ ሰዎች ምሳ የሆነላቸው በበረሃው መጨረሻ ክፍል በሚገኘው ሥፍራ ነበረ። እግዚአብሔር የተወንና የአካባቢያችን ማዕበል ካፈር ሊቀላቅለን የተዳረስ የመሰለን ጊዜ አለ? በዚህ ኃይቅ ውስጥ በታንኳ እየተጓዙ ሳሉ ሐዋርያት በማዕበል ስለተንገላቱ ኢየሱስን ከእንቅልፉ ቀስቅሰው «ጌታ ሆይ ስንጠፋ አይገድህም?» ብለው ጠየቁት። ከዚያም ኢየሱስ ተነሥቶ ማዕበሉን በገሠፀ ጊዜ ታላቅ ፀጥታ ሆነ። አንዳንድ ጊዜ ለጌታ ያለን ፍቅር ቀዝቅዞብን በአገልግሎታችን የደከምንበት ጊዜ አለ? ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ሐዋርያው ጴጥሮስን «ትወደኛለህን?» ብሎ ከጠየቀው በኋላ «ተከተለኝ» ያለው በዚሁ ሐይቅ ዳርቻ ዓሣ እያጠመደ በነበረበት ጊዜ ነው።

## ጢሮስና ሲዶና

የገሊላ ገጠራማው ሀገር በሰው የተሞላ ነበር። እንደ ጆሲፈስ ዘገባ መሠረት ከሆነ በአገሩ ውስጥ ሁለት መቶ አራት የሚሆኑ ከተማዎችና መንደሮች ይገኙበታል። ኢየሱስ በገሊላ አካባቢ ሲያልፍና ሲያገድም፣ በየምኩራቡ ሲያስተምር፣ ሰዎችንም ካለባቸው ማናቸውም ዓይነት ደዌ ሲፈውስ ብዙ ጊዜ ይታይ ነበር። እርሱም በዚህ በቅርብ ቦታ ብቻ ሳይወሰን ራቅ ብሎ እስከ ዳር አገር ድረስ ይሄድ ነበር። ከእነዚህ ጊዚያት መካከል በአንደኛው ቀን ኢየሱስ በባሕር ዳር ወደምትገኘው ራቅ ወዳለ ቦታ በመሄድ ወደ ፊንቂ መጣ። ፊንቂ በብዙ ለውጦች ውስጥ ያለፈች ወደብ ብትሆንም ኃይሏ ሳይቀነስ አሁንም በትጋት እየሠራች በእድገት ላይ ትገኛለች። ምንም እንኳ ምድሪትዋ በከፊል በግሪክ ነጋዴዎች የተከለለች ብትሆንም ጥንት

በነቢያት ዘመን የነበራት ብልጽግና ዛሬም አልተቀነሰባትም። ስለዚህ በዚህ ዓይነት አሥራር ነጋዴዎችዋን በዓለም የታወቁና የከበሩ ሰዎች አድርጋቸዋለች። በወቅቱ የላቀውንና ከፍተኛውን ክብር የያዘው ክርስቶስ መሆኑ ባይካድም የኩራዚንና የቤተ ሳይዳ ክብር በውስጣቸው ከሚፈጸመው እርካሽ ድርጊት የተነሣ ተቃልዋል። እርሱም ኮራዚንና ቤተ ሳይዳን በጥፋታቸው ከወቀሰ በኋላ ከዚህ ጋር አያይዞ ግሩም ምስክርነት ሰጥቷል። «በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጐ ቢሆን ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበር» ብሏል። ኢየሱስ ይህንን ቦታ በጐበኘበት ወቅት ከሁናቴው ጋር ተያይዞ የተፈጸመ ድርጊት ቢኖር የከነዓናዊትዋ ልጅ መፈወስ ነበር። እርሱም መጀመሪያ ከእስራኤል ቤት አለመሆንዋን ስላወቀ እምነትዋን ለመፈተን ተስፋ የሚያስቆርጥ ንግግር ተናገራት። ይኸውም የልጆችን እንጀራ አንስቶ ለውሾች መስጠት አይገባም የሚል ነበር። እርስዋም ስትመልስ ይህ ቸርነት ሊደረግላት የማይገባት ወራዳ ሴት እንደሆነች በመናገር በክርስቶስ ላይ ያላትን ጽኑ እምነት አሳይታለች። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በባርነትና በጥፋት ውስጥ ያሉ ከነዓናውያን እንኳ ቢሆኑ እምነት እስካላቸው ድረስ የበረከቱና የምህረቱ ተካፋዮች መሆን እንደሚችሉ ተናገረ።

## ኢየሱስ የተለወጠበት ተራራ

ምናልባት ኢየሱስ በተራራ ላይ የተለወጠው ፊልጶስ ቂሣርያን ለመጐብኘት በሄደበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። ከሴኬም አንስቶ በሰሜን ድንበር እስከ ቅድስት ምድር ድረስ ያለው አካባቢ ከአዲስም ሆነ ከብሉይ ኪዳን ጋር የተያያዘ ምንም ዓይነት የታሪክ ዝምድና የለውም። የዚህ ተራራ በእስራኤል አገር ከሚገኙት ተራራዎች ሁሉ ትልቅ ከፍተኛ መሆን ከአይሁድ ቤት ለጠፉት በጐች የኢየሱስን ክብር ከፍ አድርጐ እንዳሳየ ሁሉ የኢየሱስ ክብር ከፍተኛነት ደግሞ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ነገር እንዲፈጸም አድርጓል። ያም ሆነ ይህ በዮርዳኖስ ምንጭ አካባቢ ያለው ከፍተኛ ሥፍራ ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን ጨርሶ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ፊቱን እንዳቀና ዘላቂ ምስክር ሆኖ ይኖራል።

## ሰማርያን እንደጐበኘ

ጌታችን በጥብርያዶስ ይኖር በነበረበት ዘመን በየዓመቱ በኢየሩሳሌም በሚከበረው በዓል ላይ ለመገኘት በገሊላ አቋርጦ ያልፍ ነበረ። ከዚህም በቀር አልፎ አልፎ ርቆ ወደ ቂሣርያና ወደ ሲዶና ሲጓዝም በዚሁ ያልፍ ነበረ። ስለዚህ በዮርዳኖስ ሜዳ በኩል በሚወስደው ጐዳና አልፎ ካልሄደ በቀር ወደ ኢየሩሳሌምም ሆነ ወደ ቂሣርያና ወደ ሲዶና ሲሄድ በሰማርያ በኩል ማለፉ የማይቀር ነው። ኢየሱስ በዚህ ጐዳን ሲመላለስ አንድ ጊዜ በሰማርያ ከአንዲት ሳምራዊት ሴት ጋር ያደረገው ንግግር ጨርሶ የማይረሳ ነው። ምክንያቱም ሴቲቱ ደኅንነትዋን የተቀበለችው ከኢየሱስ ጋር ባደረጉት ውይይት ውጤት በመሆኑ ነው። በንግግራቸው ጊዜ ከሁሉ ነገር በላይ ሴቲቱን ያስደነቃት አይሁድና ሳምራውያን የማይዋደዱ ሆነው ሳሉ ኢየሱስ በወንጌል ላይ እንደተጠቀሰው በትህትናና በጽሞና ማናገሩ ነው። እነርሱም አይሁድ በሦራውያን ተይዘው በነበሩበት ዘመን በጋብቻ ከአሕዛብ ጋር ስለተካላሉ ንፁህ አይሁዶች ይጸየፉዋቸውና ያገልሉዋቸው ነበር። ከዚህ የተነሣ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መልሶ

በታደሰበት ዘመን ሳምራውያን ከእነርሱ ጋር በመተባበር ቤተ መቅደሱን ለማደስ በመጡ ጊዜ አልተቀበሉአቸውም። ከዚህ በኋላ በመካከላቸው እስከ መጨረሻ ድረስ መለያየት ሆነ። በተለይ በምናሴ መሪነት በገሪዛን ተራራ ላይ ለውድድር የተሰራው መቅደስ በታነፀ ጊዜ በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረው ጥላቻ ምቀኝነትና ምሬት እየተባባሰ ወደ መጨረሻው ነጥብ ላይ ደረሰ። ስለዚህ ኢየሱስ በዚህ ጥላችና ምሬት ላይ የባላይነት እንደነበረው ለማሳየት ሳምራዊቱን ሴት በፍቅር ቃል ማናገር ብቻ ሳይሆን ታላቁን የደጎንነት ብልጽግና በነፃ ሰጥቷታል። ይህ በዚህ እንዳለ በተጨማሪ ደግሞ ኢየሱስ ጥላቻን፣ መለያየትንና ምቀኝነትን ሁሉ በማውገዙ የሰው ልጆች ሁሉ እርሱ በሚሰጠው ፀጋ ሥር በመሰባሰብ በክርስቲያን ፍቅር እንዲተቃቀፉ ያዛል።

## ኢየሱስ በያዕቆብ ምንጭ አጠገብ

ጌታ በያዕቆብ ምንጭ አጠገብ ተቀምጦ ሳለ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ስለተፈጸሙ ነገሮች በማሰብ ብዙ ትዝታዎችን ሳያሰላስል አልቀረም። ከእነዚህም መካከል አንዱ አብርሃም ከአድባር ዛፍ በታች በሚኖርበት ዘመን እግዚአብሔር ስለ ገባለት ቃል ኪዳን ሊሆን ይችላል። በተለይ በያዕቆብ ዘመን ልጆቹ በታናሽ ወንድማቸው በዮሴፍ ላይ ተመቅኝተው በፈጸሙበት ተንኰል አባታቸው ታላቅ የልብ ሐዘን ደርሶበታል። ያም ሆኖ ይህ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ያቀደውን ዕቅድ ለማዛባት አልቻሉም። በኋላም ዮሴፍ ከዚህ ዓለም ሲለይ አስከሬኑ ወደ አባቶቹ ምድር ተወስዷል። ከዚያም ጥቂት ዘመን ቆይቶ ኢያሱ የአይሁድን ሕዝብ በኤባልና በሞርያ ተራራ ላይ ሰብስቦ የበረከትና የመርገም ቃል በመናገር አሜንና ይሁን እያሉ ይቀባበሉ ነበር። ከዚያም ክፉና ደፋር የነበረው አቤሜሌክ የአባቱን መንግሥት ለራሱ ብቻ ለማስቀረት ሲል በስውር ወንድሞቹን በግፍ አስገደለ። ይህ ከተፈጸመ ከጥቂት ዘመን በኋላ ደግሞ ዮታም በኮረብቶች ራስ ላይ ሆኖ ኢየሱስ አንዳንዴ እየጠቀሰ ያስተምርበት የነበረውን በዛፍ የተመሰለውን ምሳሌያዊ ቃል ይቀኝ ነበር። ከዚያም ከሰለሞን መንግሥት በኋላ ኢዮርብአም ዘውድ ከደፋ በኋላ የማይረባ ምክር ተቀብሎ ለሕዝቡ የከፋት ቃል በመናገሩ በፍርሃትና በድንጋጤ ሸሽቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄድ ችሏል። ስለዚህ ኢየሱስ ይህንን ከረጅም ዘመን በፊት የተፈጸመውን የአይሁድ ታሪክ አንድ በአንድ ወደ አዕምሮው እየጋበዘ ያሰላስል የነበረው በሰማርያ ከተማ ሲካር እየተባለ ይጠራ በነበረበት ቦታ ሆኖ በተመስጦ እያሰበ ሳለ ነው። እርሱም በተመስጦ ውስጥ ሳለ ከዚህ ጋር የከፉዎቹን ነገሥታት ታሪክና ስሟ ያጡትን የነቢያትን ሁሉ ዘመን ያሰላስል ነበረ። በአጠቃላይ ኢየሱስ በወቅቱ አዕምሮውን አስፍቶ ተራ በተራ የነመገማቸው የታሪክ ዘመናች ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ ስለ ስንዴው መከር ምሳሌ እስከተናገረበት ዘመን ድረስ ያለውን በሙሉ ያጠቃልል ነበር። ይህ ሁሉ ዝግጅት ኢየሱስን ወደ ዋናው የሥራ መስክ አድርሶታል። ስለዚህ ኢየሱስ በመጨረሻ ላይ ነፍሳትን ለመሰብሰብ የሚያደርገውን ተግባር የሚያዘገይ ሁኔታ ሊኖር እንደማይገባ በምሳሌ ተናገረው። ምሳሌውም «እናንተ፡- ገና አራት ወር ቀርቷል! መከርም ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ፥ ዓይናችሁን አንሡ እዝመራውም አሁን እንደነጣ እርሻውን ተመልከቱ» ብሏል።

## ለሳምራያውያን የነበረው ስሜት

ኢየሱስ ሳምራውያንን ከቀሩት ከአልተከለሱት አይሁዶች ለይቶ አይመለከታቸውም ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን በሰማርያ ከተማ ይኖሩ የነበሩ ጥቂት ግለሰቦች ጌታንና ደቀ መዛሙርቱን ተቀብለው ሊያስተናግዱዋቸው ፈቃደኛ አልሆኑም ነበር። ስለዚህ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አንዳንዶቹ ተናደው እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው ተመኙ። ኢየሱስ ግን ይህን ሀሳባቸውን በመቃውም ገሰጻቸው። ከዚያም ወደ ምድር የመጣው የጠፉትን ፈልጎ ለማዳን እንጂ ለማጥፋት እንዳልሆነ አስታወቃቸው። በሌላ ጊዜ ደግሞ አሥር ለምጻሞች ወደ ኢየሱስ መጥተው ከለምጻቸው ነጽተው ከሄዱ በኋላ እንደኛው ተመልሶ ኢየሱስን አመሰገነው። ይህ ሰው ሳምራዊ ሰው ነበረ። ስለዚህ ይህ ሰው እስከ ዛሬ ድረስ «መልካሙ ሳምራዊ» እየተባለ ሲጠራ ይኖራል።

## በደቡብ በኩል ስለነበረው የወይን ቦታ

ኢየሱስ በገሊላ ያስተማረው ስዕላዊ አገላለጽ ዋና ሀሳብ የተወሰደው ከዓሣ አጠማመድ፥ ከእርሻ መሬት፥ ከወይን አትክልትና የአትክልት ቦታ ነበር። የኢየሩሳሌም ተወላጆችና የአይሁድ ሰዎች እስካሁን ድረስ ልክ እንደ ኢሳይያስ ዘመን በጣም ፍሬአማ በሆኑ ተራራዎች ላይ ይኖሩ ነበር። እነርሱም «ውርንጫውን በወይን ግንድ ያስራል፤ የአህያይቱንም ግልግልግ በወይን አረግ» እንደተባለለት መሢህ በቀር በለመለመችው ምድር ኖረዋል፥ አይኖሩም ናቸው። ስለዚህም ይህንኑ ምሳሌአዊ ትምህርት ይበልጥ ለማጠናከር በማቴዎስ 21፡28 ውስጥ በወይኑ ቦታ ሄደው እንዲሠሩ አባታቸው ስላዘዛቸው ሁለት ወንዶች ልጆቹ የተነገረ ታሪክ አለ። በሌላ በኩል ደግሞ በማቴ. 21፡33 ላይ ስለዚሁ ወይነን ቦታ ባለቤትና ክፉዎቹ ገበሬዎች ተጠቅሷል። በመጨረሻም ይህ ሁሉ የወይን ቦታና የወይን ሐረግ ታሪክ የተነገረው ምሳሌአዊ ገለፃ ኢየሱስ «እውነተኛው የወይን ግንድ» እንደሆነ ለማሳሰብ ነው፤ ዮሐ.15፡1።

## በኢየሩሳሌም በምትገኘው በቢታንያ

ኢየሱስ ቀደም ሲል በነበረው ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ውይይት የሚታወስ ነው። በዚያም በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ ታሞ ተኝቶ የነበረውን በሽተኛ ሰው ፈወሰ። ከዚያም በሚከተለው ሰንበት ሌላ ተአምራትን ፈጸመ። በዚህም ያለምክንያት የሚጠሉትን ፈሪሳውያን ያስደነገጠ ቢሆንም ሰንበት የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለማምለክ ሊታደሉት ሰዎች የበረከት ዕለት እንደሆነ አስተምሯል። በዝሙት የተያዘችውንም ሴት ከመወገር አድኗት በደልዋንም ይቅር ብሏታል። ቀራጮችንና ኃጢአተኞችን እየተቀበለ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኙ የደህንነትን ቃል ይሰብክላቸው ነበር። ከዚህም በቀር ኢየሱስ በትምህርቱ ውስጥ ስለ ጠፋው በግ፥ ስለ ጠፋው ገንዘብና ስለጠፋው ልጅ ምስሌ ይመስልላቸው ነበር። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በሄደበት ወቅት ፍቅር በተሞላው ውስጣዊ ልብ በሞላ የሰዎችን መራራ ጥላቻ፥ እርግማን፥ ነቀፋና ስድብ በሞላ ተቀብሉ ነበር። ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በጥላቻ ኢየሱስን በሚነቅፉትና በሚያዋርዱት ጊዜ ሁሉ

በትዕግሥትና በጭምትነት የማለፉ ጉዳይ በጥላቻቸው ላይ የበለጠ ጥላቻ እንዲጨመር አድርጓል። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ኢየሱስ ከነአልአዛር ቤተሰብ ጋር የነበረው የተቀራረበ ሰዳጅነት ሊሆን ይችላል። ብዙ ጊዜ ኢየሱስ የከተማ ትርምስ ወደማይሰማበትን ፀጥታ ወደ ሰፈነበት ወደ ቢታንያ እየመጣ ከአለዛር ቤተሰቦች ጋር ጥሩ የምሽት የውይይት ጊዜ ይኖረው ነበር። ከውይይታቸውም መካከል አንዳንዱ በዕለት ኑሮአቸው ውስጥ አልፎ አልፎ ስለሚገጥማቸው ፈተናና መፍትሄውን የሚመለከት ሳይሆን አይቀርም። ይህ በዚህ እንዳለ ከዕለታት አንድ ቀን አልአዛር በድንገት ታሞ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያል። ቤተሰቡም በወንድማቸው ላይ በደረሰው የሞት አደጋ የተደናገጡና ያዘኑ ቢሆንም ኢየሱስ በተአምር ከሞት አስነስቶታል። ኢየሱስ ከዚህ ቤተሰብ ጋር በሚኖረው የሕብረት ጊዜ ማርያም ቃሉን ለመስማት ሁልጊዜ የተዘጋጀች ስትሆን ማርታ ግን በሥራ ብዛት ትባዝን ነበረ። በተለይ አልአዛር ሞቶ ኢየሱስ ከሞት ባስነሳው ጊዜ ኢየሱስን ይጠሉት የነበሩት ሰዎች ቁጣ ይብልጥ ተጋግሎ ሊገድሉት ይመካከሩበት ጀመር።

## ፔሪያ

ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው በኢያሪኮ በኩል አድርጐ ነበር፤ ሉቃስ 18፡31፤35። እርሱም በእነዚህ ሁለት አፈጻጸሞች መካከል ለጥቂት ጊዜ በዮርዳኖስ ፊት ለፊት በሚገኘው በፔርያ ቆይቶ ነበር። ይህ ፔሪያ የተባለው ስፍራ የጉረቤት አገር የሆኑትን ሞአባውያንን ከሚያዋስነው ጨለማ ከሚመስለው ከሞአብ ተራራ ጥግ ላይ ነበረ። ሙሴ ነፍሱን አሳልፎ በመስጠት የሞተው በዚህ ተራራ ላይ ሲሆን ኤልያስም በእሳት ሰረገላ የተወሰደው በዚህ ተራራ አካባቢ ሳለ ነበረ። ኢየሱስ ከጥቂት ቀናት በኋላ በመስቀል ላይ ሊሞት ስላለው ሁኔታ ጋር በውስጡ እየታገለ ሳለ ከእነዚህ ሁለት ነቢያት ጋር በአርሞንኤም ተራራ ላይ በተለወጠበት ዕለት የተወያዩት ነገር ትዝ አለው።

## ዮርዳኖስ - ኢያሪኮ

በመጨረሻም የፋሲካ በዓል እየተቃረበ ስለመጣ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ተነሡ። ይህ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ዮርዳኖስን የተሻገሩበት አካባቢ በብሉይ ኪዳን ዘመን በኢየሱስ የሚመስለው ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝቡ ይዞ ዮርዳኖስን ከተሻገረ በኋላ የዘንባባ ዛፎችና ምንጮች ወደ ነበሩበት ወደ ኢያሪኮ የመጣበት ሥፍራ ነው። ከዚህ በቀር ያ አካባቢ ጥሩ ጠረን ባለው በሽቶ ዛፍ ተሞልቶ ነበር። አንድ ጊዜ እንቶኒ ለልዕልት ክሊኦፓትራ ክብር ከዚህ ዛፍ እቅፍ አበርክቶ ነበር። ከዚህም ሌላ አንቶኒ ንጉሥ ሄሮድስ በሞት ጊዜ የአገሩን መኳንንት በአንድ ሥፍራ ከሰበሰበ በኋላ ለንጉሡ እንዲያለቅሱለት አድርጓቸዋል። በዚያን ዘመን የክርስቶስ ዝና በያለበት ተዳርሶ ስለ ነበረ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ሊያዩት ወደ እርሱ ይጐርፉ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ብዙ ሕዝብ ኢየሱስን ተከትሎ በመንገድ ሲያልፍ ሁለት በመንገድ ዳር ተቀምጠው ይለምኑ የነበሩ ዓይነ ስውሮች ፈውስን ከኢየሱስ ጠይቀው ብርሃናቸውን ሰጥቷቸዋል። እነርሱም ብርሃናቸውን መልሰው ስላገኙ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተፈጥሮን ዓለም በማየት ደስ ይላቸው ጀመር። በእነኚህ ኢየሱስን ይከተሉ ከነበሩ ሕዝቦች መካከል ዘኪዎስም ስለነበረበት ኢየሱስን ለማየት ካለው

ከፍተኛ ፍላጐት የተነካ ምንም የተከበረ ሰው ቢሆንም ክብሩን ከምንም ሳይቆጥር እንደ ልጅ ጭኑ ላይ ወጥቷል። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በገባለት ቃል መሠረት ወደ ቤቱ በመጣ ጊዜ እንደ እንግዳ ወደ ቤቱ ሲቀበለው እንደ አዳኝ ደግሞ ወደ ልቡ ተቀብሎታል።

## ቢታንያ

ኢየሱስ ኢያሪኮን ለቆ ወደ ቢታንያ ሲጓዝ አቀበቱን እየወጣ ሳለ ለተከታዮቹ ስለ መልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ ይነግራቸው ነበር። በኋላም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከእግዚአብሔር ቃል ምሳሌን እየመሰለላቸው ከቢታንያ መንደር ደረሱ። ይህች መንደር በስተ ምሥራቅ በኩል ከደብረዘይት ተራራ ግርጌ ላይ የተመሠረተች ነበረች። ከተማይቱም በተመሠረተችበት ቦታ ሆና ተመልካቾችን ኢየሩሳሌምን ከማየት ስትከልል በውስጥዋ ለሚኖሩት ሰዎች ደግሞ የረጋና ፀጥ ያለ አየር ትመግባቸው ነበር። የአልአዛርና የእህቶቹ መኖሪያ የነበረችው ጐጆም የምትገኘው በዚሁ ሥፍራ ነበር። ኢየሱስም ወደ እነርሱ ቤት እንግድነት ገብቶ ማርታ ካዘጋጀችው ምሳ እየበሉ ሳለ ማርያም ደግሞ ለመቃብሩ ሲሆን ባለው ሽቱ እግሩን ታብሰው ነበር።

## ኢየሩሳሌም

በማግሥቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲያልፍ ኢየሱስ መምጣቱን የሰማ እጅግ ብዙ ሕዝብ ከከተማው ወጥቶ ተቀበለው። እርሱ በአህያ ውርንጫ ሆኖ በሚያልፍበት ጐዳና ሁሉ ላይ የዘንባባ ዝንጣፊ ተነጥፎለት ነበረ። በመጀመሪያ ሽቅብ ወደ ምስራቅ ይወስድ የነበረው ጐዳና በኋላ ወደ ምዕራብ ዞሮ ወደ ኢየሩሳሌም ያመራል። ከዚያም ወደ ፊት በመገስገስ አቀበቱን ሲወጣ ኢየሩሳሌም ከተማ ፊት ለፊት ቁልጭ ብላ ትታያለች። እነሆ የተወደደችውና ጌታ ያለቀሰላት የኢየሩሳሌም ከትማ። ኢየሱስም በሩቅ ተመልክቷት «ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ፣ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሯል» አላት።

## ያለፈው ትዝታና ለሚመጣው ዝግጅት

እያንዳንዱ መንገደኛ ሜዳውን ጨርሶ ደብረ ዘይት ተራራ አፋፍ ላይ ሲደርስ በመጀመሪያ ዓይኖቹ በሩቅ የሚመለከተው የኢየሩሳሌምን ከተማ ነበር። ስለዚህ ንግግሩ ሁሉ ከተማዋን የሚመለከት ነበረ። በአሁኑ ጊዜ ግን ጥንት የሰለሞን ቤተ መቅደስ ተመሥርቶ በነበረበት ቦታ ላይ የኡማር መስጊድ ታንጾበታል። በዚህን ጊዜ ኢየሱስ ያለፈውን ታሪክ ሊመጣ ካለው ድርጊት ጋር በማመዛዘን በአዕምሮው ያውጠነጥን ጀመር። በተለይ ያለፈውን ዘመን በሚያስታውስበት ጊዜ «ይህቺ የጽዮን ተራር እግዚአብሔር የወደዳት ናት» የተባለውንና «ይህች ለዘለዓለም ማረፍያዬ ናት፣ መርጬአታለሁና በዚህች አድራለሁ» ያለው ቃል ትዝ አለው። በዚህ ላይ የተጠቀሰው ቃል እነ ዳዊት፣ ሰለሞን፣ ሕዝቅያስ፣ ዕዝራ፣ ነህምያና የቀሩት ታላላቅ መንፈሳዊ ሰዎች የኖሩበትን ዘመን የሚያስታውስ ነው። ይህ ሀሳብ ኢየሩሳሌም ወደ ፊት ባድማና ወና እንደምትሆን ከተነገረው የትንቢት ቃል ጋር ይመሳሰላል። በመጨረሻም ልክ በዚህ እንደተባለው ኢየሩሳሌም በሮማውያን እጅ ወድቃ ስትደመሰስ የአረቦች መሳለቂያ ትሆናለች። እንግዲህ ኢየሱስ ዓይኖቹ እንባ ያቀረሩት የሕዝቡን መጥፋትና እምነታቸውም

የሕዝብ መሳለቅያ እንደሚሆን በማሰብ ነው። እርሱም ወደ ቤተ መቅደሱ በደረሰ ጊዜ የእርግብ ሻጮችንና የለዋጮችን ገበታ ገልብጦ በጅራፍ አስወጣቸዋል። ከዚያም በዚያ አካባቢ ጥቂት ቀን ቆይቶ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለሕዝቡ ወንጌልን ያስተምር ጀመር። በዚህን በቤተ መቅደስ ውስጥ ያስተምር በነበረበት ቀናት የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያንን ጥያቄዎች በመመለስ፤ ሀሰተኛ መምህራንንና ነቢያት ወደ ፊት ስለሚደርስባቸው በማስታወቅ ወዮላችሁ ይላቸው ነበረ። ከዚህም ጋር ስለ ዓለም ፍጻሜና ስለ መጨረሻው ዘመን አስተምሯል። ምናልባት እንደለመደው በምሽት ጊዜ ወደ ቢታንያ ይመለስ ይሆናል። ከእነዚህ ጊዜያት በአንደኛው ዕለት ምናልባት በምሽት ጊዜ ኢየሱስ ከለምጹ ካዳነው ከስምዖን ቤት እንግድነት ተቀምጦ ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ሽቱ አምጥታ ለመቃብሩ መታሰቢያ እንዲሆን ቀብታው ይሆናል። ይህ ለኢየሱስ ይደረግለት የነበረ ቅዱስ ሥራና አምልኮ ወደ ትግሉ ሜዳ የሚያቀራረበው እንደነበረ ይገመታል።

## የደብረ ዘይት ተራራ

ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን በደብረዘይት ተራራና በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ አብዝቶ ይገኝ እንደነበረ የቃሉ ምስክርነት አለን። የደብረዘይት ተራራ ከፍተኛ ሆኖ ቁልቁል እየወረደ በመሄድ እንደ ሰንሰለት ተያይዞ በመሄድ በከተማው ምስራቃዊ ክፍል ሲደርስ ሦስት ረጃጅም ተራራ ሆኖ ይከፋፈላል። የተራራው ከፍተኛ ቦታ ከኢዮሳፍጥ ሸለቆ ሽቅብ ሲለካ 130 ሜትር ሲሆን ከሜዲትራንያን አካባቢ እስከ ተራራው ጫፍ ግን 900 ሜትር ይረዝማል። ምናልባት ይህ ተራራ ስሙን የወረሰው በላዩ ላይ ካለው የወይራ ዛፍ ሳይሆን አይቀርም። ይኸውም ከአሁን ይልቅ ተራራው በውይራ ዛፎች ተሞልቶ በነበረበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ የወይራ ዛፍ በብዛት የሚታየው በአንደኛው የተራራው ክፍል ብቻ ሲሆን በቀሩትም ላይ እጅግ ሳይበዛ ጥቂት ተራርቆ ይታያል። በጥንት ጊዜ ከእነዚህ የወይራ ዛፎች በስተቀር በተራራው ላይ የዘይት፥ የበረሃ ወይራ፥ የባርስነትና የዘንባባ ዛፍ በብዛት ነበረበት። በአሁኑ ጊዜ ግን እነዚህ ሁሉ ጨርሰው የሉም፤ ነህም. 8፡14-16። ጌታ በምድር በተመላለሰበት ዘመን ተራራዎቹ በለመለሙ ዛፎች የተሸፈኑ ነበሩ። ስለዚህ ጌታ ብዙ ጊዜ ጸጥታና የመንፈስ እረፍት ለማግኘት አዘውትሮ ወደዚህ ቦታ ይመጣ ነበር።

## የጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ

የጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ የሚገኘው ከኢየሩሳሌም ትይዩ ከደብረዘይት ግርጌ ከቄድሮን ወንዝ አጠገብ በኢዮሳፍጥ ሸለቆ ውስጥ ነው። የአትክልቱ ቦታ በጠቅላላው የያዘው ሥፍራ ሃምሳ ሜትር ይሆናል። መቶ አለቃ ሊይንች የተባሉት ሰው «በመጀመሪያ ይህን ቦታ በጐበኘሁበት ጊዜ አቤት፤ የዛፎቹ ሁሉ አበባ ፈንድቶ ሙሉ በሙሉ ታላቅ ፀጋ ይታይበት ነበር። እኔም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ካየኋቸው የአትክልት ቦታዎች ጋር ሳመዛዝነው ከማንኛውም የላቀ ነው። በእርግጥ ሥፍራው መንፈሱ የታወከበትን ሰው ሕይወት እንኳ በፀጥታ ያረጋጋል ብዬ አምናለሁ። ከትክልቱ ሥፍራ ዛፎች ውስጥ ስምንቱ በጣም በዕድሜ የቆዩ ስለሆኑ ልዩ የአከብሮት አመለካከት ይሰጣቸው ነበር። ሌሎች ከእነዚህ ራቅ ብለው በደብረዘይት ተራራ ግርጌ የተተከሉት ዛፎች ደግሞ የጉዳናውን ዳርና ዳር ይዘው በሰልፍ

ሲቆሙ የመንገዱን አቅጣጫ እንደ ገመድ ተዘርግቶ እንዲታይ ያደርጉታል። ከእነርሱ ጥቂት እልፍ ብሎ ደግሞ ለተቀደሰ ነገር ተለይተው የተተከሉ ሌሎች ዛፎች ቆመዋል። ከተራራው ግራና ቀኝ ከፍ ብሎ በቀኝ በኩል የኢዮሳፍጥ ሸለቆ በሰፊው ተሰንጥቆ ሾጣጣ የሆኑ መስመሮች ሸቅብ ሥርቷል። በአንደኛው ሸለቆ አናት ላይ ዘለዓለማዊ የሆነው የኢየሩሳሌም ከተማ ዘውድ መስሎ ጉብ ብሏል። በሌላው ሸለቆ ግርጌ ላይ ደግሞ የመቃብር ቦታ ይታያል። እያንዳንዱ ዛፍ በቆመበት ቦታ ሆኖ የጥንቱን ታሪካዊ ሁኔታ በአቀማመጡና በዕድሜው እርዝማኔ እውን መሆኑን ያረጋግጥ ነበር። አንዳንዱ የወይራ ዛፍ እርጅቶ በሚሞትበት ጊዜ በሞተው ዛፍ ላይ ሌላ አዲስ የውይራ ዛፍ ያቆጠቁጥ ነበረ። ይህ እየሞተ ያለው ዛፍም በግምት ዕድሜው መቶ ዓመት ሊሆነው የሚችል ነው። ጌታም አንዳንድ ጊዜ ወደ አትክልቱ ቦታ ሲመጣ ማረፍ የሚወደው በዚህ አሮጌውን በተካው ቁጥቋጦ ሥር ነበረ። ከእነዚህ ቁጥቋጦች መካከል አንዱ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ተንበርክኮ እያለቀሰ የጸለየበት ቦታ ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ በዚህ ጊዜ የጥርጣሬ መንፈስ ወደዚህ ሥፍራ ለመግባት ቀዳዳ አላገኘም ነበር። ክርስቲያኖችም የጊዜውን ችግር ረስተው ባለፈው በጌታ ሥራ ተመስጦ ውስጥ የሚገቡት በዚሁ ቦታ ሲሆን ነው። ከቁጥቋጦው ሥር የሚበቅሉት ልዩ ቀለማት ያላቸው አበቦችም በቦታቸው ሆነው ያዳኛችንን ሥቃይና ሞት ያበስሩ ነበር።»

## የክርስቶስ ሥራና ትምህርቱ

የሰው ልጅ አሁን በምድር እንዲያደርግ የተሰጠውን ሥራ ሁሉ ፈጽሞ አከናውኗል። እርሱም ነቀፋ የማይገኝበትን አምላካዊ ኑሮ በሥጋው በመኖር ፍጹም የሆነ ምሳሌነቱን በማይታየው አምላክ አምሳል ሆኖ አሳይቷል። እርሱም የብሉይ ኪዳን ትንቢት ፈጻሚ መሢህ እንደሆነ በቃሉ ተናግሮት የነበረውን እውነት በተግባር አረጋግጧል። ከዚህም በቀር ባደረገው ተአምራትና በፈጸመው ቸርነት ጣዕም ከነበረው መለኮታዊ ቃሉ ጋር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አስተማምኗል። በተለይ ረባይ የተባሉት የአይሁድ መምህራን ስለ ሕግና ነቢያት እያዛቡ ያስተምሩት የነበረውን ትምህርት ከእውነት እንዳይርቅ በመጠበቅ ይከላከል ነበር። ከዚህ በቀር እውነትና መልካምነት በቃል የሚተረክ ብቻ ሳይሆን በሕይወት ውስጥ የሚጀምር እንደሆነ ደኅና አድርጐ አስረድቷል። ከዚህ በማያያዝ የታደሰ ፍላጐትና ንፁሕ የሆነ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን መልካም ሕብረት የሚያሳይ ጥሩ መግለጫ ነው ብሏል። በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው አምልኮ በመንፈስ የሚደረግ አምልኮ ብቻ ነው ስለዚህ አማኞች እግዚአብሔርን በዚህ ዓይነት አምልኮ ያመለኩት እንደሆነ ለጠፉት ነፍሳትና ከእርሱ ርቀው ለኮበለሉት ልጆቹ ያለውን ፍቅር መረዳት ሲችሉ ብቻ ነው። አማኞች በዚህ ዓይነት ቅዱስ ሕይወት በሚኖሩበት ጊዜ ኢየሱስን በመለኮታዊ ውበቱና በሰብአዊነቱ መልክ ይመለከቱታል። ነቀፋ የሌለበት የሕይወት እንጀራና የሕይወት ውኃ ስለሆነ እውነተኛ የወይን ግንድ መሆኑን አስተምሯቸዋል። በውስጣዊ ሕይወታቸው እውነተኛ ጥገና ከየት እንደሚገኝ ያውቃሉ ኢየሱስ በጥንት ዘመን ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ንግግር ዛሬ ለወንጌል አገልግሎት አቢይ መከፈቻ ሆኖ እየሠራ ነው። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን ሰው ከአዳም በወረሰው ውስጣዊ ብልሽት በክርስቶስ መስዋዕትነት ነጽቶ ከአብ ጋር ይታረቃል። በአጠቃላይ «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም»፤ «ሙሴ በምድር በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።» ስለዚህ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ በከፈለው

መስዋዕት እስከ ዛሬ ድረስ እንደታሰበ ይኖራል። እርሱም በዚህ መስዋዕትነቱ የሰው ልጅ ጠላት የሆነውን ሞት በሞቱ ድል ሲያደርግ በትንሣኤው ደግሞ ደህንነታችንን አረጋግጧል። ስለዚህ ነው ኢየሱስ «ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ» ሲል የቃል ምስክርነቱን የሰጠን።

የኢየሱስ እልፍ መሰጠትና የጴጥሮስ ክህደት፡- ኢየሱስ ተይዞ ለጠላቶቹ በመሰጠት የመጨረሻዋን ምሽት በሕይወት የሚቆይበት ጊዜ ነው። ከግብፅ ባርነት የወጡበትን ምሽት የሚያሳስበው እራት አብቃ። ይህ እራት በሌላ በኩል በክርስቶስ ከኃጢአትና ከሞት ባርነት አርነት ሊያወጣን ሊያደርገው ያለውን መስዋዕትነት ያሳስባል። የደቀ መዛሙርቱ እግር ታጠበ። አሳልፎ ሊሰጠው ያለውም ደቀ መዝሙር የሊቀ ካህኑን ጭፍሮች ለመገናኘት ወጥቶ ሄደ። በዚህን ጊዜ ብዙ ጭንቀትና ሐዘን በልቡ የወደቀውን ጌታ ለማጽናናት ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ተከትለው ወደ ጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ሄዱ። ሰማያትም በተመስጦ ለጌታ በሚማልዱት ጸሎት ተሞላ ጌታና ሐዋርያት ይህንን ቦታ የመረጡት ከከተማው ጫጫታና ሁካታ በፀጥታ ሆነው ከአብ ጋር በጸሎት የሚገኛኙበትን አካባቢ ስለ ፈለጉ ነው። እነርሱም ወደ አትክልቱ ሥፍራ ደርሰው ሳለ ስምንቱ ደቀ መዝሙርት ከወዲሁ የቄድሮን ወንዝ በሚገኝበት ሸለቆ ውስጥ ለጸሎት ተንበረከኩ። ከእነርሱ መካከል ግን ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ኢየሱስን ተከትለው ጥቂት እልፍ ብለው ከጌታ ጋር ይጸልዩ ጀመር። በዚህ የምሽት ጸሎት ጌታ ኢየሱስ ይሁዳ ሊያደርግ ያለውን አስቀድሞ ያውቅ ስለ ነበር ደጋግሞ በሀሳቡ ይከታተለው ነበት። አሁን ግን አልፎ የሚሰጠው እየቀረበ መምጣቱን አወቀ። የጊዜው የመከራ ደመናና የጨለማው ገዢ ኃይል የሞት ጥላ በላዩ ላይ ወደቀበት። በዚህን ጊዜ ኢየሱስ እጅግ እየቃተተ የደም ላብ እንጥፍጣፊ ከወዙ እየወረደ ነበር። ይህ ብዙ ጊዜ አትፍሩ ይል የነበር ጌታ የሞት ጣር ሰቀቀን፤ ፍርሃትና ድንጋጤ የወደቀበት ይመስላል። በኋላ ግን መንፈሱ ተመልሶ ተረጋጋ። በዚህን ጊዜ ከቄድሮን ወንዝ አካባቢ የችቦ ብርሃን ውጋጋን ይታይ ጀመር። ብርሃኑ እየተቃረበ ሲመጣ ችቦውን የያዙት ሰዎች ድምፅ ያስተገባ ጀመር። ድምፁ እየጐላ በመጣ ቁጥር ችቦውን የያዙት ሰዎች እርምጃቸው ወደ ጌቴሰማኒ እንደሆነ ታወቀ። ምክንያቱም ይሁዳ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የት እንደሆኑ ያውቅ ስለነበረ ነው። አሳልፎ የሚሰጠውም ወደ ኢየሱስ ተጠግቶ ሳመው። ኢየሱስም ያለምንም ቅሬታ ሊይዙት ለመጡት ራሱን አሳልፎ ሰጣቸው። በዚህን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በሞላ ተደናግጠው ሸሽተው ከዚያ አካባቢ ጠፉ። በዚህን ጊዜ ኢየሱስ ብቻውን ያለ ዕረዳት እስረኛ ሆኖ ወደ ከተማ ተወሰደ። ከዚያም ወደ ሐናንያ ቤት መሩት። ሐናንያም ወደ ቀያፋ አሳልፎ ሰደደው። ኢየሱስ የቀረውን ምሽት በሞላ በቀያፋ ቤት መንግሥት ውስጥ አሳለፈ። ዮሐንስና ጴጥሮስ በዚያ ነበሩ። ነገር ግን የጴጥሮስን ልብ አነሳሥቶት የነበረው ድፍረት ቀይቶ ስለሚሸሽ በመጨረሻ ፈጽሞ ጠፋ። ስለዚህ ጴጥሮስ እየማለና እየተገዘተ ጌታን እንደማያውቀው በአደባባይ ካደው። ያ ምሽት የሃዘንና የለቅሶ ምሽት እንደ ሆነ አለፈ። በነጋ ጊዜም ምንም ደስ የሚያሰኛቸው ነገር አልተገኘም።

## ፈተና

በማግሥቱ ጠዋት ሊቀ ከህኑና አማካሪዎቹ የሃይማኖት መሪዎች ጉባዔ ለምክክር ስብሰባ አደረገ። ከእነርሱም መካከል ሊቀ ካህኑ፣ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ኢየሱስ ከባድ ወንጀል እንደ ፈፀመ አድርገው ቆጠሩት። ሆኖም በወቅቱ በኢየሱስ ላይ ይሙት በቃ የማስተላለፍ ሥልጣን

አልነበራቸውም። ስለዚህ ኢየሱስን የሚከሱበትን ምክንያት ይዘው የመጨረሻ ፍርድ ወደሚሰጠው የሮም መንግሥት ተወካይ ወደሆነው ወደ ጲላጦስ የፍርድ ችሎት ቀረቡ። የሮም አገረ ገዢ የሆነው ጲላጦሳም እነርሱ እንደጠበቁት ሳይሆን መርምሮ ወንጀል እንዳላገኘበት በመናገር ሀሳባቸውን ያሰናክልባቸዋል። ቀኑ እየረፈደ በሄደ ቁጥር ጲላጦስ ከውሳኔው ሳይንቀሳቀስ ኢየሱስ የሚፈታበትን ዘዴ በመፈለግ ወንጀል እንደሌለበት ደጋግሞ ያስታውቃቸው ጀመር። ስለዚህ ያለ አበሳው ኢየሱስን ለሞት አሳልፎ መስጠት ይቅርታ የሌለው ግፍ ነው አላቸው። ይህ በዚህ እንዳለ የጲላጦስ ሚስት ስለ ኢየሱስ ያለመችውን ሕልም በማስመልከት እንዳችም ዓይነት ፍርድ እንዳይሰጠው በማስጠንቀቅ ወደ ባለቤትዋ መልዕክተኛ ትልካለች። ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ኢየሱስ የገሊላ ሰው እንደሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ላከው። ሄሮድስም ከመረመረው በኋላ ምንም ወንጀል ስላጣበት መልሶ ወደ ጲላጦስ ይልከዋል። በዚህ ሁኔታ ጲላጦስ በኢየሱስ ላይ ፍርድ ከመስጠት ስለዘገየ የኢየሱስ ጠላቶች የበሩት የሃይማኖት መሪዎች አጉረመረሙ። ጲላጦስም ኢየሱስን መርምሮ ባገኘው ውጤት መሠረት ወንጀል እንደሌለበት አድርጎ ከፈታው የቄሣር ጠላት እንጂ ወዳጅ እንዳልሆነ የሃይማኖት መሪዎቹ አስታወቁት። ጲላጦስም ብዙ ተከራክሮ ስለታከተው እናንተ እንደወደዳችሁ አድርጉበት ብሎ ወንጀል የሌለበትን ኢየሱስን ከገረፈው በኋላ እንዲሰቅሉት አሳልፎ ይሰጣቸዋል። እነርሱም ኢየሱስን ተቀብለው እያንገላቱ ሊሰቅሉት ወደ ጎልጎታ ወሰዱት። በአንዳንድ የጥንት ባህላዊ ታሪክ የጲላጦስ ሚስት ቅላውድያ ጵርስቅላ ክርስቲያን ሆና ነበር ተብሎ ይነገራል።

## ጎልጎታ ሞቱና ቀብሩ

ቀራንዮ ወይም ጎልጎታ እየተባለ በሚጠራበት ቦታ ላይ በሮማውያን የሞት አቀጣጥ ኢየሱስን ብዙ አስቃይተውት ነበር። ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል የተባለው ትንቢት ተፈፀመ። የፋሲካው ጠቦት አጥንቱ እንዳይሰበር እንደተነገረው ከኢየሱስም አንዳች አጥንት አልተሰበረም። የአይሁድ ያቀጣጥ ደንብ ደግሞ አጥንት እስኪሰበር ድረስ በድንጋይ መውገር ነበር። ሆኖም ኢየሱስ የተከሰሰበት ሁኔታ ሕግን በመተላለፍ አልነበረም። ከመስቀሉ ራስጌ የናዝሬቱ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ የሚል ጽሑፍ እስከአሁን ድረስ አይሁዶች በሚነጋገሩባቸው ሦስት ቋንቋዎች ተጽፈው ነበር። የተጻፉባቸው ቋንቋዎችም ዕብራይስጥ፣ ግሪክና ላቲን ነበሩ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለረጅም ሰዓት ከተሰቃየ በኋላ ታላቅ የድል ድምፅ አሰምቶ ፍፁም በሆነው እረፍት ሕይወቱን ሰጥቶ አንቀላፋ። ከዚያም የሕዝብ አለቃ የነበረው የአርማቲያሱ ዮሴፍ ወደ ጲላጦስ መጥቶ የኢየሱስን አካል አስፈቅዶ ከወሰደ በኋላ አስከሬኑን በተልባ እግር ልብስ ጠቀለለው። በኋላም የአይሁድ ሰንበት ሳይገባ ፀሐይ ልትጠልቅ አቅራቢያ ዮሴፍ ለራሱ ባዘጋጀው ከዐለት በተወቀረ መቃብር ውስጥ የኢየሱስን አስከሬን አኖረው። በዚህን ጊዜ ኢየሱስ ታላቁን የመዋጀት ሥራውን አብቅቶ ለሦስት ቀን ያህል በመቃብር ውስጥ ዕረፍት አደረገ።

# ትንሣኤውና ዕርገቱ

የሚቀጥለው ቀን የአይሁድ ሰንበት ነው። እስከአሁን ድረስ እንደ ስካር የሚነገዳገደው የደቀ መዛሙርቱ እምነት አልተረጋጋም። ከዚህ በቀር ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ተሰቅሎ መሞቱን ሲሰሙ የሁሉንም ልብ ብርክ ያዛቸው። በሚከተለው ቀን ግን የኢየሱስ መቃብር ባዶ እንደሆነና ተነስቷል የሚል ዜና ተሰማ። ኢየሱስም በዚያኑ ዕለት ለአንዳንዶቹ ደቀ መዛሙርትና ተከታዮቹ ተገልጾላቸዋል። ከዚያም በተከታዩ ሳምንት በመጀመሪያው ቀን በዚያው በኢየሩሳሌም እንደገና ቶማስ ባለበት ቦታ ደቀ መዛሙርቱ በአንድነት ተሰብስበው ሳለ ተገለጠ። ከዚያም የቶማስን አለማመን ከገሰፀ በኋላ አለማመኑን አስወግዶለታል። ከዚህ በኋላ በገሊላ የሚገኘውን ተራራማ ቦታ እንደ ዋና መገናኛ ሥፍራቸው ካደረጉ በኋላ ሁሉም ወደ ተወለዱበት አካባቢ ተበታተኑ። ከመበታተናቸው በፊት ግን ጴጥሮስ ከቀሩት አሥሩ ደቀ መዛሙርት ጋር ሆኖ በወንዝ ዳር ዓሣ ሲያጠምድ ኢየሱስ በድንገት ተገልጦ ካጠመዱት ዓሣ ከጠበሰላቸው በኋላ አብሯቸው ተቋድሶ ነበር። በዚህን ጊዜ በተለይ ጴጥሮስን ትወደኛለህን? ሲል ደጋግሞ ጠይቆታል። ከዚህ በኋላ በመገኛው ተራራ አካባቢ አምስት መቶ ለሚሆኑ ለገሊላውያን ተከታዮቹ ራሱን ገልጾላቸዋል። በመጨረሻም ለነዚሁ በገሊላ ለሚገኙ ተከታዮቹ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። «ከሁሉ በኋላ ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ የደብረዘይትን ተራራ እቋርጦ በወቅቱ በጣም ወደ ታወቀችው ወደ ቢታንያ ከተማ መጣ። ከዚያም ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርቱ እንደ ገና ለመጨረሻ ከታያቸው በኋላ እየባረካቸው ሳለ በድንገት ተንጥቆ ወደ አብ አረገ።

# የሐዋርያት ታሪክ

# ከ29 ወይም ከ33 እስከ 100 ዓ.ም.

# ክፍል 1

## የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን

### የክርስቶስ ዕርገት

ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የተገናኘው በቢታንያ ነበረ። ምናልባት ኢየሱስ በድንገት ከመካከላቸው ተነጥቆ በሰማይ ዳመና ወደ ሰማይ ያረገው ከአሁን ቀደም ከአልዓዛር ጋር አብሮ በተጋዘበት የወይራ ዛፎች በበዙበት ሥፍራ ወይም ትንሣኤና ሕይወት እርሱ መሆኑን በተናገረበት አካባቢ ሆኖ ሳለ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ በዚያም የሚቀር እስከማይመስላቸው ድርስ ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴና ተአምራት በመካከላቸው ይፈጽም ነበር። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ባረገበት ዕለት ተገልጸውላቸው የነበሩት መላዕክቶች እንደነገሩዋቸው ሐዋርያት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ከመቶ ሃያዎቹ ደቀ መዛሙርት ጋር ሰከቡ። ኢየሱስ በኢየሩሳሌም አካባቢ በሰበከበት ዘመን ሁሉ እርሱን ቆርጠው ለመከተል የወሰኑት ተከታዮቹ 120 ብቻ ነበሩ። እነርሱም በገሊላ አካባቢ ከዳኑት አማኞች ይልቅ እጅግ በጣም የሚያንሱ ነበሩ። በዚህም ላሉ በይሁዳ ፈንታ ማትያስን እንደ አንዳቸው ሐዋርያ እንዲሆን ከመረጡት በኋላ ዓለምን በወንጌል ድል ለማድረግ በአንድነት ሆነው በጸሎት ይተጉ ጀመር። እነርሱም መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ዕለት መጥቶ በሁሉም ላይ እስካረፈባቸው ቀን ድረስ ጸሎታቸውን አላቋረጡም ነበር።

### ሁለት ዘርፍ ያለው የሐዋርያት ታሪክ

በሐዋርያት አገልግሎት ሥር ይካሄድ የነበሩት የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት በሁለት ዘርፍ የሚራመዱ ነበሩ። እነርሱም የአይሁድና የአሕዛብ በመባል በሁለት የተከፈሉ ናቸው። በአይሁድ ቡድን የሚመራው የቤተ ክርስቲያን ክፍል አብዛኛውን ጊዜ በአሥራ ሁለቱ የሐዋርያት ትምህርት የሚመራ ሲሆን በአሕዛብ ቡድን የሚመራው የቤተ ክርስቲያን ክፍል ደግሞ አብዝቶ አትኩረት የሚሰጠው ሐዋርያው ጳውሎስ የሰበከውን መልዕክት ብቻ ነበር። ስለዚህ ቀደም ሲል የተጻፈው የሐዋርያት ሥራ የመጽሐፍ ክፍል አንደኛውን ቡድን የሚደግፍ ሲሆን ዘግየት ብሎ የተጻፈው የመጽሐፉ ክፍል ደግሞ የቀረውን ቡድን እንደሚደግፍ ተደርጐ የተጻፈ ነው። ያም ሆነ ይህ በሁለቱ መካከል ጥቂት የተዛባ አስተሳሰብ ቢኖርም ሁለቱም

«አንድ እምነት፥ አንድ ተስፋና አንድ ጥምቀት ስለተጠመቁ» ሕብረታቸው በእነርሱ አስተሳሰብ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር አሠራር ላይ የተመሠረተ ነበረ። ሃይማኖት በአሁኑ ጊዜ ከቀድሞው ይልቅ የተድበሰበሰ መሆኑ ቀርቶ ግልጽ መሆን ችሏል። አሠራሩም በሰው ትጋት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት የሚፈጸም ነው። ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚሳቡት ከሰማይ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። ከወዲሁ የተነሡት የእግዚአብሔር ነቢያትም ከማንኛቸውም ይልቅ ይህንን ሀሳብ ደግፈው ይናገራሉ። ነገሩም ሊደገፍ የሚገባው በስራ የተፈተነ ኃቅ ነው። በተለይ በአሁኑ ጊዜ በመንፈሳዊ አሠራር ውስጥ ዋነኛውን ተግባር የሚያከናውነው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በግልጽ የታወቀ ነገር ነው። ይልቁንም በሰዎች ሕይወት መለወጥ ተግባር ውስጥ መጀመሪያውን ሥፍራ የያዘው መንፈስ ቅዱስ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል እየተባለ የሚጠራው በዚሁ ምክንያት ነው።

## የበዓለ ሃምሳ ቀን

አይሁዶች ለመጀመሪያ ጊዜ በብዛት ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተለወጡት በበዓለ ሃምሳ ቀን ነበረ። ይህም ቀን የዋለው ክርስቶስ በተሰቀለ በሃምሳኛው ቀን ነው። በዚህን ቀን አይሁዶች ምናልባት ከቀረው ጊዜ ይልቅ ከተበታተኑበት ከዓለም ዳርቻ ሁሉ በዓሉን ለማክበር በብዛት የተሰበሰቡበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። በዚህን ጊዜ አይሁዶች ከተለያዩ የዓለም ክፍላተ ሀገሮች ስለመጡ ሙሴ ያዘዘውን ሥርዓት አምልኮ በትክክል መከታተል አልቻሉም። በበዓሉ ላይ ለመገኘት መቻላቸው ራሱ በጣም አዳጋች የሆነውን ነገር እንደፈጸሙ የሚያስቆጥራቸው ነበረ። ምናልባት በዚህ ጊዜ በብዛት በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ያደረጋቸው ሌላው ምክንያት የመጓጓዣ መስመራቸው ከማንጣውም ጊዜ ይልቅ የተመቻቸ በመሆኑና የተለያዩ መልዕክቶች በቀላሉ ስለሚደርሷቸው ሊሆን ይችላል። ሌላው ሁኔታ ደግሞ ከእስፓኝ እንስቶ ሕንድ ድረስ ያለው መመላለሻ በደንብ ስለተሠራና ነጋዴዎች በየጊዜው ዜና ይዘው ስለሚመላለሱ ነው።

## አይሁዶች በኢየሩሳሌም

አብዛኛዎቹ ከአይሁድ ምድር በየዓለማቱ የተበታተኑት አይሁዶች በተለይም በምርኮ ተወስደው የሄዱቱ በዚህን ጊዜ ዋነኛው የአይሁድ ቋንቋ በሆነው በዕብራይስጥ መነጋገራቸውን አቋርጠዋል። በፋንታውም የተበታተኑበት አገር ነዋሪዎች በሚነጋገሩበት ቋንቋ መጠቀም ጀምረዋል። በበዓሉ ላይ የተገኙት አይሁዶች የቋርቴና የሜድ፥ የኢላሜጤም ሰዎች፥ በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጶዶቅያም፥ በጳንጦስም፥ በእስያም፥ በፍርግያም፥ በጵንፍልያም፥ በግብፅም፥ በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች፥ በሮም የሚቀመጡ የቀርጤስና የዓረብ ሁሉ አይሁዶች ነበሩ። በዚህም ዕለት ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በመቀበል ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ተለውጠው የተጠመቁት አይሁዶች ቁጥር ሦስት ሺህ የሚያክሉ ነበሩ። ከዚያም እነዚህ የተለወጡ ሠራዊቶች በምላ ወደ ኋላ ቅርተው ምክርና ተጨማሪ የክርስትና መመሪያ ከተሰጣቸው በኋላ በሃይማኖት ጸንተው እንዲኖሩ ተነግሯቸዋል። በኋላም በአንድነት መንፈሳዊ ሕብረት አድርገው እንደጨረሱ በያሉበት አገር እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ታላቅ ነገር ለመናገር ተሰነባብተው ተለያዩ።

# ችግርና ምቀኝነት

በሐዋርያት ኃላፊነት ሥር የምትካሄደው የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እያደገችና በመንፈሳዊ ሕይወትዋም እየተዋበች መጣች። ከዚህም በቀር ቤተ ክርስቲያንዋ በትህትና፣ በእውነት፣ በልግስናና በእርስ በርስ ፍቅር በጣም ስላደገች እጅግ የምታስደንቅ ሆነች። እግዚአብሔርም በሚያስደንቅ ሁኔታ በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ከልኋታል። በአንድ ወቅት ሰዱቃውያን ጭፍሮቻቸውን አስከትለው በሐዋርያት ላይ ስደትና መከራ አካሂደውባቸው ነበረ። ከዚያም ጉዳዩን ለፈሪሳውያን አለቃ ለገማልያ አማከሩት። የፈሪሳውያን አለቃ የነበረው ገማልያም ስለ ሁኔታው በዝርዝር እየገለጠ ሳለ ድንገት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንን ስለሚለየው የእምነት ክፍል ጠቅሶ ሲያስረዳ በመካከላቸው መለያየት ተፈጥሮ እርስ በርሳቸው ይቃዋወሙ ጀመር። በዚህን ጊዜ ከአይሁድ ወገን ሆነው በአራም ቋንቋ በሚናገሩት አይሁዶችና ተበትነው በነበሩት ግሪክ ተናጋሪ አይሁዶች መካከል መከፋፋትና መመቀኛኘት ተነሣ። ከዚህ በኋላ በመካከላቸው የተፈጠረውን መለያየትና መከፋፈል መልሶ ለማቃናትና ቤተ ክርስቲያንዋን በግዚያዊ ሁኔታ የሚያሰባስቡ ሰባት ዲያቆናት ተመረጡ። ሰባቱም የግሪክ አገር ተወላጅ ሰው ስም የነበራቸው ነበሩ። ይህ የሚያሳየው ሰዎቹ የተመረጡት ከግሪክ ተናጋሪዎቹ አይሁዶች መካከል እንደ ሆኑ ነው።

# እስጢፋኖስ

ከእነዚህ ከተመረጡት ዲያቆናት መካከል አንዱ «እምነትና መንፈስ ቅዱስ የሞላበት» ሰው እስጢፋኖስም ነበረበት። እርሱም «ፀጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር።» በእርሱም በኃይል መንፈስ ቅዱስ ሲጠቀምበትና አያሌ የሆኑ ታላላቅ ነገሮችን ሲያደርግ አይተው የወንጌል ጠላቶች በጣም ተቃወሙት። በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ውስጥ ተበትነው የነበሩት አይሁዶች ያሠሩዋቸው ምኩራቦች ነበሩ። ምኩራቦቹንም ያሠሩዋቸው ለሁለት ነገሮች ነበረ። አንደኛ ኢየሩሳሌምን ለመጎብኘት ሲመጡ ማረፍያ እንዲሆኑዋቸው ሲሆን ሌላው ምክንያታቸው ደግሞ ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት እንዲሆኑዋቸው ብለው ነው። አንዳንድ ሰዎችም ከእነዚህ ምኩራቦች መጥተው ከእስጢፋኖስ ጋር ይከራከሩ ነበር። እነርሱም እስጢፋኖስ ምናልባት አስቀድሞ ይናገረው የነበረውን የግሪክ ቋንቋ በትክክል መነጋገር የሚችሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነዚህ ምኩራቦች መካከልም አንዳንዶቹ በፊት የሮማውያን ባርያዎች ሆነው ሲገዙ ቆይተው አሁን ነፃነታቸውን ያገኙት አይሁዶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱም በሮም ክፍለ ሀገር በቀሬኔዎስ፣ በግብፅ በምትገኘው እስክንድርያ፣ በኪልቅያና ዋና ከተማ ከነበረችው ከሳዖል አገር ከጠርሴስ የመጡ አይሁዶች ምኩራብ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ ከእስጢፋኖስ ጋር የነበራቸው ክርክር ስለጦፈ እስጢፋኖስ በድፍረት የወንጌልን እውነት ሊቀካህናትና የአይሁድ እምነት መሪዎች ባሉበት ሥፍራ በኃይልና በድፍረት ይናገራል። ከዚህ የተነሣ ይህ አንጋገሩ የሃይማኖት መሪዎቻቸውን እንደመዳፈር ስለተቆጠረበት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ጎትተው ከከተማ ዳር አውጥተው በድንጋይ ወግረው ገደሉት። ምንልባት እስጢፋኖስን ወግረው የገደሉት በኢዮሳፍጥ ሸለቆ ውስጥ ሊሆን ይችላል። እርሱም ኢየሱስን ከፍ ከፍ በማድረግና

መሢህ ነው ብሎ እየመሰከረ በመጨረሻ ለወጋሪዎቹ ደህንነት በመጸለይ ይሞታል። እስጢፋኖስ በዚህ ዓይነት አሟሟት ምድራዊ ሕይወቱን ሲያበቃ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የንጋት ኮከብ እንደሆነ ይመስላል። እርሱም በሙሴ ሕግ ተከታዮችና በክርስቶስ በዳኑት የአሕዛብ ተወላጆች መካከል ምንም ዓይነት መበላለጥ እንደሌለ ቀደም ብሎ ተረድቷል። እስጢፋኖስ የመጀመሪያውን የወንጌል ሥራ አገልግሎት መጨረሻው ግብ እንዲያደርስ ለጳውሎስ ጥሎት ያልፋል።

## ወንጌል በሰማርያ

ከመጀመሪያው ሰማዕት ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ ታላቅ ስደትና ግድያ በክርስቲያኖች ላይ ተካሄደ። እነዚያ በቅድሚያ እስጢፋኖስን የገደሉት ሰዎች የደም ማፍሰሳቸው ሱስ ስለተቀሰቀሰ ይበልጥ ክርስቲያኖችን ለማረድና ለማሳደድ እንደ ቀትር እባብ አስፍስፈው ከወዲያ ወዲህ ይራወጡ ነበር። ይህ ስደት የተነሳው በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ብቻ ተወስነው የተከማቹት ክርስቲያኖች በየስፍራው ተሰራጭተው የወንጌልን ዜና በየቦታው ሁሉ እንዲያደርሱ ነበር። ከዚህ ስደት በኋላ የወንጌሉ ብርሃን ከተዳረሳቸው ከተማዎች አንዱ «የሰማርያ ከተማ» ነበረ። ከዚህ በፊት ኢየሱስ ወደዚህች ከተማ በመጣበት ጊዜ ልዩ ስፍራዋ ሲካር በተባለች ቦታ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አራት ላይ እንደተጠቀሰው ውኃ ልትቀዳ የመጣችውን ሳምራዊት ሴት አነጋግሮ ነበር። ይህች ቦታ ምናልባት የሳምራዊቱ ሴት እንደተናገረችው ስለ ኢየሱስ መምጣትና ሌሎች ሊሆኑ ስላሉት ነገሮች ከጥንት ጀምሮ የተወራበት ጥንታዊት ከተማ ትሆናለች ተብሎ ይገመታል።

ምናልባት በዚህን ጊዜ ሰምዖን የተባለው ጠንቋይ በሰማርያ ከተማ ከእግዚአብሔር የሆነ ኃይል አለኝ እያለ ሕዝቡን እያወናበደ የነበረበት ወቅት ሊሆን ይችላል። በኋላም ከእግዚአብሔር የመገለጥ ስጦታ የነበራቸው ሐዋርያት ወደ ሰማርያ በመጡ ጊዜ እያደረጉ የነበረውን ተአምራት አይቶ የእግዚአብሔርን ሥጦታ በገንዘብ ለመግዛት ይጠይቃቸዋል።

## ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ

ወንጌል ለሳምራውያን መድረሱና እነርሱም በአክብሮት መቀበላቸው በዓለም ፊት ታላቅ ስፍራ የተሰጠው ቢሆንም ይበልጥ ደስ የሚለው ደግሞ ኢየሱስ ለእነርሱ የነበረው ፍቅር ነበረ። የሳምራውያን በክርስቶስ መወደድና ወንጌል በሕይወታቸው የሠራው ለውጥ ሊደነቅ የቻለው እግዚአብሔር አሕዛብንም ለመውደዱ ዓይነተኛ ምሳሌ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር አሕዛብንና የተጣሉትን ሕብረተሰቦች ሁሉ እንደ አይሁዶች የመቀበሉ ተግባር እየቀጠለ በመሄዱ የኢየሩሳሌምን በዓል ለማክበር ለመጣው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የወንጌሉ መልዕክት እንዲነገረው ወደ ጋዛ ምድረ በዳ ፊልጶስ ተልኮለታል። ከዚያን ቀን ጀምሮ ይህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ በመቀበል አማኝ ሊሆን ችሏል። ከረጅም ዘመን በፊት የኤርምያስ ወዳጅ የሆነ አቤሜሌክ የሚባል ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ልክ እንደዚህኛው ጃንደረባ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ካደረገ በኋላ ተመልሶ ወደ አገሩ ሄዶ ነበረ፤ ኤር.36፡16 ተመልከቱ። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር መጻተኞችንና እንግዶች ወደ እኔ ይመጣሉ እኔም እቀበላቸዋለሁ ያለው የትንቢት ቃል

ተፈጸመ፤ ኢሳ. 56፡4-6። ጃንደረባው የብርሃን ምንጭ ከሆነው የኢየሩሳሌም ከተማ ምንም ሳያገኝ ባዶውን ለቆ ወጥቶ ነበር። ቢሆንም የሕይወት ውኃ ምንጭ በጋዛ ምድረ በዳ ውስጥ ፈልቆለታል። በፊልጶስ ምስክርነት ጃንደረባው ክርስቶስን ተቀብሎ አዲስ ፍጥረት ስለሆነ በዚያው በምድረ በዳ ውስጥ የውኃ ጥምቀት አደረገ። ከዚያም በመንፈሳዊ ደስታ ደስ እያለው ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ የደኅንነትን ወንጌል ለተወለደበት ሀገር ሕዝብ መስበክ ጀመረ። ይህ ደግሞ ሌላው ለአሕዛብ የተከፈተውን የደኅንነት በር የሚያሳይ ነው። ሆኖም ሐዋርያት ይህን ለአሕዛብ እየተከፈተላቸው ያለውን የደኅንነት በር ቶሎ ለማስተዋል አልቻሉም ነበር።

## አዲሱ የወንጌል ተልዕኮ

እስጢፋኖስ ከሞተ በኋላ ጥቂት ቆይቶ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ እንደተሳለ ሰይፍ የመሰለውን አገልጋይ አስነሳ። በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን እስጢፋኖስን የመሰለ ሰው ማጣትዋ ታላቅ ክስረት ቢሆንም ምንም የማይሳነው ጌታ የበለጠ አገልጋይ አስነስቶላታል። ይህ ከእስጢፋኖስ በኋላ የተነሳው አገልጋይ ብሩህ የሆነ መንፈስና ጽኑ እምነት የነበረው ሰው ነበረ። እርሱም በቀድሞ ሕይወቱ እጉል ወግ አጥባቂና ሀሳበ ግትር ሰው ነበረ። ሆኖም እግዚአብሔር እስጢፋኖስ አቋርጦ የሄደውን የወንጌል አገልግሎት እንዲቀጥል አድሎት ነበር። የእስጢፋኖስ ጸሎት ከእርሱ የላቀውን መንፈሳዊ አገልጋይ ስላስነሳ መንፈሱ እግዚአብሔርን ያከብር። የዚህ አገልግሎት ዕድለኛ ሆኖ እግዚአብሔር ያስነሣው እስጢፋኖስ ሲሞት የወጋሪዎቹን ልብስ ሰብስቦ ይጠብቅ የነበረ የጠርሴሱ ሳኦል ነበረ። እነሆ እግዚአብሄር የወንጌልን ቃል ለአሕዛብ ሁሉ እንዲያሰማ የተመረጠ ዕቃ አድርጐ ሊጠቀምበት የገማልያል ተማሪ የነበረውን ጳውሎስን መርጧል።

# ክፍል 2

# የሐዋርያው ጳውሎስ የቀድሞ ሕይወት

## ልደቱ በጠርሴስ

ሐዋርያው ጳውሎስ በብላቴናነቱ ዘመን ስለነበረው የሕይወት ታሪክ የምናውቀው በጣም ጥቂት ነው። እርሱም በእስያ አገር የኪልቅያ ዋና ከተማ በነበረችው በጠርሴስ ተወለደ። ምናልባት ሐዋርያው ጳውሎስ የተወለደው ከክርስቶስ ልደት በኋላ ጥቂት ቆይቶ ሳይሆን አይቀርም። ሐዋርያው ጳውሎስ በዕድሜው ቆይቶ እንደሞተ ለመግለጽ «ሽማግሌው ጳውሎስ» ሲል ስለራሱ ተናግሮ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ በሞት ከዚህ ዓለም የተለየው ከ58 እስከ 68 ዓ.ም መካከል ባለው ጊዜያት ውስጥ ነው። አንዳንድ ምሁራን ሐዋርያው ጳውሎስ ከሮም እሥር ቤት ተፈትቶ ኗሮ በክርስቲያኖች ላይ ባመጣው ስደት ውስጥ ነው የሞተው ብለው የራሳቸው የሆነ ማረጋገጫ ይሰጣሉ። ወላጆቹ ከአሕዛብ ጋር ያልተከላለሰ ንጹህ ከሆኑ አይሁዳዊ ቤተ ሰቦች የተወለዱ ናቸው። ትውልዱ ከብንያም የዘር ሐረግ ውስጥ ቢሆን

ሐዋርያው ጳውሎስ ያደገው ከተሰፋይቱ ምድር ራቅ ብሎ በሚገኘው በሮማውያን ግዛት ውስጥ ስለሆነ በሮም ነዋሪነቱ የታወቀ ነበረ። ኪልቂያ የምትገኘው ከሜዲትራንያን ባሕር ዳርቻ ላይ ሲሆን በሮም ግዛት ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የተሰጣት ቦታ ነች። እርስዋም በአንድ ወገን ከጢሮስ ተራራ ጋር ስትዋሰን በሌላው በኩል ደግሞ ከሊባኖስ ጋር ትዋሰናለች። በአካባቢዋም ብዙ የአለት ሰንጣቂዎችና ጥቅጥቅ ያሉ ዱሮች ስለነበሩ ለሌቦችና ለቀማኞች ጥሩ መሸሸጊያ ስፍራ ሆኖላቸው ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ከመወለዱ ከ50 ዓመት በፊት ፓምፔ የተባለው ሰው ስፍራውን ከነፍሰ ገዳዮች ጥርት ከደረገ በኋላ ከሮም ግዛቶች መካከል እንደ አንዱ አድርጐ አቋቁሞታል። በተለይ ይህ ግዛት ሲሲሮ በተባለ አዋቂና ጠቢብ በሆነ አገረ ገዢ ይተዳደር በነበረበት ወቅት በጣም የከበረና የበለፀገ ምድር ሆኖ ነበር። ጳውሎስ በተወለደበት ዘመን ግን በጠርሴስ የግሪክ መጻሕፍት፣ የግሪክ ተናጋሪዎችና ሊቃውንት ይበዙባት ስለነበረ የግሪክ እንጂ የሮም ግዛት ናት ብሎ የሚገምት ሰው አልነበረም። ምናልባት በዚያን ዘመን ጳውሎስ በግሪክ፣ በአራም፣ በዕብራይስጥና በላቲን ቋንቋ መናገር ይችል ይሆናል። ከነዚያም ቋንቋዎች መካከል አንዳንዱን በጠርሴስ ትምህርት ቤት የሚሰማቸው ሲሆኑ የቀሩትን ግን በቤቱ በዕለት ንግግራቸው የሚጠቀሙባቸው ይሆናሉ። እርሱም ከልጅነቱ ጀምሮ ወገኖቹ ታላቅ ሕዝቦች እንደሆኑ እየተነገረው ከማደጉ በቀር የጽዮንንም መዝሙር ገና ከብላቴንነቱ ጀምሮ ያጠና ሳይሆን አይቀርም። ከዚህ የተነሳ ለአገሩና ለሕዝቡ ታላቅነት ያለው ስሜት ከፍተኛ ነበረ። ከዚህም በቀር የዳዊትንና የሙሴን ሕይወት ምሳሌነት ተከተለ፤ መልካምና ቁም ነገረኛ ሰው መሆን እንዳለበት የተማረ ነበረ፤ በሌላ አንጻር ደግሞ ለኢየሩሳሌምና ለይሁዳ ከተሞች ከፍተኛ ግምትና አክብሮት ነበረው።

## ትምህርቱ በኢየሩሳሌም

ሐዋርያው ጳውሎስ በገማልያል ትምህርት ቤት ለመማር የሄደው በስንት ዓመት ዕድሜው እንደሆነ ማወቅ አይቻልም። ሆኖም ከባህላቸው አንጻር አንድ ጐበዝ የአካባቢውን አገሮችና ኢየሩሳሌምን ለመጐብኘት የሚወስደው በስንት ዓመቱ አካባቢ ሊሆን እንደሚችል በግምት መናገር ይቻላል። በተለይም በዘመናት ውስጥ አንዳንድ ታሪካዊ ሁኔታዎች የተፈጸሙባቸውን በታዎች ለማየት እንደሚፈልግ መገመት አያስቸግርም። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ጊብዓን የተባለው ተራራማ በታ፣ ሳሙኤል በእስራኤል የፈረደበት ራማ የተባለው ስፍራ፣ ኢያሱ የተባበሩትን አሞራውያንን የመታበት በታ፣ የፍልስጥኤማዊው የናታን መታሰቢያና የሰርያ ይሁዳ መቀበያ መታሰቢያ በታዎች ናቸው። ሳኦል በገማልያል ትምህርት ቤት ሳለ ይጠራበት የነበረው የላቲን ስሙ ጳውሎስ ነበር። ጳውሎስ ለሃይማኖቱ እጅግ ይቀና ስለነበረ ከአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ትዕዛዝን ተቀብሎ ክርስቲያኖችን ከማሳደዱ በላይ የክርስቶስን ስም እንዲሰድቡ ያስገድዳቸው ነበር። እርሱም ይህን በሚያደርግበት ጊዜ ለእግዚአብሔር እንዳገለገለ አድርጐ ራሱን ይቆጥር ነበር።

## የደማስቆ ጉዞና የሳኦል መለወጥ

ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም አካባቢ ያሉትን ክርስቲያኖች ብቻ በማሳደድ ስላልረካ አዲሱን ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት የሚሰጠውን ትምህርት ለመቃወም እራቅ ወዳሉ

ከተሞች ድረስ ለመሄድ ፈቃደኛ ነበር። የአይሁድ ሊቀ ካህን ሃይማኖትን በሚመለከት ጉዳይ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን አይሁዶች ብቻ ሳይሆን ከኢየሩሳሌም ውጭ በሌላ ምድር የሚኖሩትንም አይሁዶች ጭምር የማዘዝ ስልጣን ነበረው። ስለዚህ ሳኦል ከሊቀ ካህናት የተቀበለው ስልጣን ክርስቲያኖችን እስከ ዳር አገር ድረስ ለማሳደድ በቂው ነበረ። ሳኦል ማናቸውንም የአዲሱን እምነት ተከታዮች በተዘዋወረበት አካባቢ ሁሉ ካገኘ ወደ ኢየሩሳሌም እስሮ እንዲያመጣ ከሊቀ ካህናቱ ደብዳቤ ተቀብሎ ነበር። ወደ ደማስቆ የሚወስደው የሮማውያን አውራ ጐዳና ሳኦልን በገሊላ በሕር አካባቢ ያደርሰው ነበር። ከዚህ በኋላ ሳኦል ክርስቲያኖችን አድኖ ለማጥፋት በዚህ ከልጅነት ጀምሮ በሚያውቀው አካባቢ ለመመልከት አይኖቹን አነሳ። መቼም በወቅቱ በሐዋርያት እጅ ይደረግ የነበረው ድንቅና ተአምራት ዝና እስከ ሩቅ ድረስ ተሰምቶ ስለ ነበር በአካባቢው የሚወራውን ወሬ ለመስማት ጆሮቹን ሳያቆም አልቀረም። በዚህን ጊዜ ሳኦልና አጃቢዎቹ ከገሊላ ባሕር አካባቢ ርቀው ብዙ ሄደው ነበር። ከዚህ በኋላ እድካሚ የሆነውን የሶርያን በረሃማ ምድር አቋርጠው ካለፉ በኋላ የደማስቆን ከተማ በሩቅ ይመለከቱ ጀመር። በዚህን ጊዜ ድንገት እንደ ሰማይ ብልጭታ የሆነ ታላቅ ብርሃን አበራባቸው። ከብርሃኑ ውስጥም ድምፅ ወደ ሳኦል መጣ። በዚህ ድምፅ ኃይልም ሳኦል ከመቅጽበት ተለወጠ። ከዚህ በኋላ አሳዳጁ ሳኦል ከሰማይ ለተገለጠለት ድምፅ በመታዘዝ በድምፁ ኃይል ከወደቀበት ምድር የክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ ሆኖ ተነሣ። በኋላም ያጠፋው የነበረውን የደኅንነት መንገድ መልሶ ማነጽና መደገፍ ጀመረ።

## በወቅቱ የተፈፀመው ሁኔታ ጠቃሚነት

የጳውሎስ የመለወጡ ሁኔታ በማንም አዕምሮ ሲታወስ የሚኖር ነገር ነው። ለአገልግሎት የተደረገለት ጥሪም እንደ ዳግማዊ አብርሃም ጥሪ የሚቆጠር ነው። ሐዋርያው ገና ከመጀመሪያው ዕለት ኢየሱስን በጠየቀው ጥያቄ ነገሮችን በግልጽ ለመረዳት የመሻቱን ሁኔታ አሳይቷል። ስለዚህ «ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?» ሲል ጠይቋል። ይህ ጥያቄ እንደ ጌታ ኢየሱስ ትንሳኤ በራሱ ሙሉ ምስክርነትን የያዘ ነው። ምክንያቱም የጥያቄው መልስ የእውነተኛ ክርስትናን ምንነት በትክክል ስለሚገልጥ ነው። የሐዋርያው ሕይወትና ዓላማ ከመቅጽበት ሊለወጥ ቻለ። ይህ የእግዚአብሔር የማዳኑ ፀጋ እጅግ ሰፊና ሁሉንም የሚያቅፍ በመሆኑ ዜናውን ለማድረስ ራሱ ሳኦል እግዚአብሔር አስነሳው። እርሱም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰጠውን የፀጋ ደኅንነት ለመቀበል ከዐዘኑት ጋር ሲከራከር ለእግዚአብሔር ቸርነት ማረጋገጫ እንዲሆን የኃጢአተኛ ዋና ሳለ ምህረትን እንዳገኘ ያስረዳቸው ነበር። ጳውሎስ እግዚአብሔር ላደረገለት ታላቅ ውለታና ቸርነት ወሮታ ለመመለስ ያደረበት ውስጣዊ ፍቅር ዘወትር ትኩስና የጋለ ፍላጐት እንዲኖረው አድርጐታል። ስለዚህ የጌታ ፍቅር ግድ ይለው ስለነበር በአገልግሎቱ ዘመን በገጠሙት ችግሮችና ፈተናዎች ውስጥ ሳይበገር በድል አድራጊነት አልፎአል።

## የሦስት ዓመት ቆይታ

ሐናንያ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ወይም ሐዋርያ አልነበረም። ሆኖም ታላቁን የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ቆርቋሪ የነበረውን ሐዋርያ ጳውሎስን ያጠመቀው እርሱ ነበረ። ከዚያም

ሐዋርያው ጳውሎስ በደማስቆ ጥቂት ከሰነበተ በኋላ ከቀሩት የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ተሰናብቶ ወደ አረቢያ ሀገር ሄደ። በዚያ በኖረበት ሦስት ዓመት ውስጥ በዋሻ ይኖሩ ከነበሩት መነኩሳት ጋር ይኑር ወይም በገላትያ መልዕክቱ ላይ እንደገለጠው ስለ ሁለቱ ኪዳናት የጥናት ጊዜ ይኑረው በእውነት አልታወቀም። አንዳንድ ምሁራን እንደሚገምቱት ምናልባት በደማስቆ ሰሜናዊ ክፍል በሮማውያን ግዛት በሆነው የአረብ ክፍል በሦርያ በረሃ ውስጥ የጽሞናና በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ላገልግሎት የሚያዘጋጅበት ጊዜ ኖሮት ይሆናል ብለው ያስባሉ። ከዚያ በተመለሰ ጊዜም የእግዚአብሔርን ቃል በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ እየተቃጠለ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለማዳኑ ፀጋ በደማስቆ በግልጽ ያስተምር ጀመር። በዚህን ጊዜ የአይሁድ ወግ አጥባቂዎች ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ተቃውሞ ስላስነሱበት በምሽት በቅርጫት ተደርጐ እንዲያመልጥ ችሏል።

# ወደ ኢየሩሳሌም መመለሱና በሦርያና በቂሊቂያ የሰጠው አገልግሎት

ጳውሎስ በለመደው መንገድ ተመልሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። የሚገርመው ግን ከሦስት ዓመት በፊት በነበረው አመጸኛና ክፉ ልብ ሳይሆን በተለወጠና በሚያስደንቅ ሕይወት መሆኑ ነበር! በዚህን ጊዜ ኢየሩሳሌምን ለመጐብኘት የነበረው ዓላማ ራሱን ለክርስቶስ ሐዋርያት ጋር ለማስተዋወቅ ነበረ። ቢሆንም ሐዋርያት በመጀመሪያ ላይ ተጠራጥረውት ስለነበረ ከመቀበል ገሸሽ አደረጉት። በኋላ ግን በባርናባስ በኩል የጳውሎስን ምስክርነት እንዲሰሙ ከተደረገ በኋላ የቀሩት ደቀ መዛሙርት በሞላ በክርስቶስ ወንድማቸው እንደሆነ አረጋግጠው በፍጹም ደስተኛነት ተቀብለውታል። ከዚያም ከነበረው ጽኑ የሆነ መንፈሳዊ ወኔ ተነሳስቶ በኢየሩሳሌም በሚገኙ ገዳማትና ምኩራቦች እንኳ ሳይቀር ቃሉን በድፍረት ይሰብክና ያስተምር ጀመረ። በዚህ ምክንያት ልክ በደማስቆ የሃይማኖት መሪዎች እንዳሳደሙበት በዚህም ተመሳሳይ ሴራ አድርገውበታል። በዚህ ተመሳሳይ ጊዜ ክርስቶስ በራዕይ ተገልጦ ኢየሩሳሌምን ለቆ እንዲወጣና ለእርሱ ያዘጋጀለት የአገልግሎት ስፍራ በአሕዛብ መካከል እንደሆነ አስረዳው። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን በሥጋ አብሮ ለተወለዳቸው ወገኖቹ ታላቅ ፍቅር ስለነበረው ባለፈው ዘመን ያበላሸውን ነገር መልሶ ለማስተካከልና አሳስቷቸው ለነበሩት ሰዎች የመለወጡን ምስክርነት ለመስጠት በዚያው ለመቆየት ፈቃድ ጠየቀ። ጌታ ግን እሺ አላለውም። ስለዚህ ሐዋርያው ሁለት ሳምንት ያህል በኢየሩሳሌም ከሰነበተ በኋላ የይሁዳን ዋና ከተማ ለቆ ወጣ። ከዚያም በቂሳርያ አድርጐ ወደ ጠርሴስ ተመልሶ በሶርያና በኪልቅያ አካባቢ አገልግሎቱን መስጠት ቀጠለ።

# ክፍል 3

# ቤተ ክርስቲያንን ለማስፋፋት የተደረገ ዝግጅት

## የጴጥሮስ ራዕይ በኢዮጴ

አሁንም በእስራኤል አንዳንድ ሁኔታዎች እየተፈጸሙ እያለ ከአሕዛብ ወገን ብዙዎች ወደ ውሳኔ ደርሰው ጌታን ስለተቀበሉ ቤተ ክርስቲያን በደስታ እየተቀበለች ታስተናግዳቸው ነበር። በተመሳሳይ ጊዜ ማለት ሐዋርያት አገልግሎት በመስጠት ላይ እያሉ ጴጥሮስ በሜዲትራንያን ባሕር አካባቢ ወደምትገኘው ኢዮጴ ወደተባለች ጥንታዊ ወደብ ይወርዳል። ይህም ጥንታዊ ወደብ ያገለግል የነበረው ዘመናዊ የሆኑት የቂሳርያና የአካ ወደቦች እስከተሠሩበት ጊዜ ድረስ ነበረ። ጴጥሮስም ዶርቃ የተባለችውን ክርስቲያን እህት ከሞት በማስነሳት ታላቁን ተአምራት የፈጸመው በዚህኑ ወቅት ነበረ። እርሱም በዚህች ጥንታዊ በሆነች በኢዮጴ ወደብ ላይ ሆኖ ሰማያዊ በሆነ የባሕሩ ገጽታ በሜዲትራንያን በኩል አሻቅቦ ሲያይ የእስራኤልን ከተማ ዙርያ አጠቃሉ መመልከት ችሏል። ምናልባት ሐዋርያው የተመለከተውን አካባቢ ሁሉ በወንጌል ለማዳረስ ልቡ የተነሳሳው በዚህ ስፍራ ሆኖ አካባቢውን ከተመለከተ በኋላ ይሆናል ብለን እንገምታለን። ሆኖም እርግጠኛ ሀሳቡ በእውን አይታወቅም። ሆኖም ጴጥሮስ እግዚአብሔር አሕዛብንም ለደኅንነት እንደተቀበላቸው በራዕይ የገለጸለት በዚሁ በኢዮጴ ሳለ ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሐዋርያት ለአሕዛብ የነበራቸው አስተያየት ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት አስቀድመው መገረዝና አይሁዶች መሆን ይኖርባቸዋል የሚል ነበር። ብዙዎቹ አይሁዳዊ ክርስቲያኖች የሙሴን ሕግ ሳያከሉበት አንድን ሰው ወደ ክርስቲያን ሕብረተ ሰብ ከመቀበል ሞትን ይመርጣሉ። ያም ሆነ ይህ አሕዛብ ያለ ሙሴ ሕግ በክርስቶስ ፀጋ ብቻ ወደ እግዚአብሐር መንግሥት ለመግባት እንዲችሉ የቀሩትን መሰናክሎች ሁሉ ከመንገዳቸው ላይ ማስወገድ ይኖርባቸዋል።

## የቆርኔሌዎስ ራዕይ በቂሣርያ

ጴጥሮስ ያየውን ራዕይ ምን እንደሆነ በሀሳብ ሲያወጣና ሲያወርድ ሦስት ሰዎች ከቂሣርያ ከቆርኔሌዎስ ዘንድ ተልከው ወደ እርሱ ይመጣሉ። ቆርኔሌዎስም በቂሣርያ የሚኖር እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሮማውያን መቶ አለቃ ነበረ። እርሱም በጸሎት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እየጸለየ ሳለ መልአክ ወደ እርሱ ዘንድ ተልኮ መጥቶ የደኅንነትን መንገድ በትክክል የሚነግረው ሰው በቁርበት ፋቂው በሰምዖን ቤት እንግድነት ስለተቀመጠ አስጠርቶ ከቃሉ እንዲሰማ ይነግረዋል። ከዚያም ጴጥሮስና ሊጠሩት የሄዱት መልዕክተኞች ሲጓዙ ውለው በማግስቱ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ይደርሳሉ። ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር ቃል ጠቅሶ የኢየሱስን አዳኝነት እየነገራቸው ሳለ በቆርኔሌዎስና ከቃሉ እንዲሰሙ በሰበሰባቸው በወዳጆቹና በቤተሰቦቹ ላይ ድንገት የእግዚአብሔር መንፈስ ወረደባቸው። በዚህን ጊዜ ጴጥሮስ ጥላቻውን ትቶ ካልተገረዙት ከቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች ጋር በአንድነት ከመሆኑ በላይ የጥምቀትን ሥርዓት እንዲቀበሉ ካደረገ በኋላ አብሮአቸው ከአንድ ማዕድ በልቷል። ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም እንደተመለሰ አይሁዶች ከአሕዛብ ጋር ባደረገው ሕብረት ደስ አላላቸውም!

ምክንያቱን በመከፋት ሁኔታ ይጠይቁታል። እርሱም አሕዛብን ወደፊት እንደ እርኩስ እንዳይቆጥር እግዚአብሔር ስላሳየው ራዕይና በኋላም ለአይሁዶች የሰጠውን መንፈሱን ለእነርሱም እንዳልነፈጋቸው ባስታወቃቸው ጊዜ መከፋታቸውን ትተው ሁሉም በአንድ ሀሳብ በእግዚአብሔር ዓላማ ተስማሙ።

## ፖለቲካዊ ለውጥ

በዚህን ጊዜ ክርስቶስ ወደ አብ ካረገ አሥር ዓመት አልፎታል። ከዚህ በኋላ ባጭሩ ማብራርያ ልንሰጥባቸው ባሉት የፖለቲካዊው ዓለም ክፍል በሆኑት በይሁዳና በቀሩት ቦታዎች ስለተደረጉት ብዙ ለውጦች እንነጋገራለን። ንጉሥ ጢባርዮስ ሞተ። የእርሱ ተከታይ የሆነው ካሊጉላ የተባለው ሰው የሚያደርገውን የማያውቅ ክፉ ወፈፍተኛ፣ ጨካኝና ዘማዊ ነበረ። እርሱም ልቡ እጅግ በትዕቢት ተነፍቶ አይሁዶች እንደ አምላክ እንዲያመልኩት ትዕዛዝ ባስተላለፈበት ወቅት በድንገት ይገደልና በዚህ ሁኔታ ሕይወቱ ያልፋል። ቀላውዲዮስ በዚህን ጊዜ የንጉሡን የሀር መጐናጸፍያ ይለብሳል። ቀያፋም ከሊቀ ካህንነቱ ሥልጣን ተሽሮ በምትኩ ዮናታን ይሾማል። ከዚህም በቀር ጲላጦስ አንድ ሳምራዊ ሰው ጥፋት ሳይኖርበት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ስላስገደለ ከሥልጣኑ ይወገዳል። ከዚህ በኋላ የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ የሚቼ የኤጢሊን ልጅ ሄሮድስ ንጉሥ ሆኖ ተሾመ። ከዚያም ሄሮድስ አንጢጳስ ወደ ጋውል ከተባረረ በኋላ የገሊላና የፕሪያ ያስተዳደር ኃይል ታክሎበት ለንጉሥ አግሪጳ ሥልጣን የበለጠ ክብደት ሰጥቶታል። በቀላውዲዩስ ስምምነት መሠረት ሮማውያን ለንጉሥ አግሪጳ ያያቁ ግዛት የነበረውን ይሁዳንና ሰማርያን አጠቃሎ እንዲይዝና እንዲያስተዳድር አሳልፈው ይሰጡታል።

## የሄሮድስ አግሪጳ ሞት

ንጉሥ አግሪጳም ዝነኛ መሆንን እጅግ አብዝቶ ይጠማ ስለነበረ ሐዋርያው ያዕቆብን በማስገደሉ አይሁዶች ደስ ተሰኝተዋል። እርሱም ይህን ሲያውቅ ይበልጥ በፊታቸው ሞገስን ለማግኘት ሲል ጴጥሮስንም ለማስገደል ትዕዛዝ ሰጥቶ አስይዞ አሳሰረው። ሆኖም ጴጥሮስ ሳይገደል በፊት በተአምር ከእስር ቤት ወጥቶ አመለጠ። ይህም ሊሆን የቻለው በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ አጥብቆ ይጸለይ ስለነበረ ነው።

ከዚያም ንጉሥ አግሪጳ ብዙ ሳይቆይ በቂሣርያ በሚገኘው የትያትር አዳራሽ ውስጥ ለሕዝቡ ንግግር አደረገ። ንጉሡ በዚያ በነበረበት ጊዜ ልብሶቹ በብዙ እንደ ወርቅና አልማዝ የመሰሉ የከበሩ ድንጋዮች በፀሐዩ ውጋጋን ያንጸባርቁ ስለነበር እንደ አማልክት ስለቆጠሩት ወድቀው በመስገድ አመለኩት። እርሱም ያለ አንዳች ቅሬታና ፍርሃት በመኩራራት ስግደታቸውንና አምልኮታቸውን ተቀበለ። ወዲያውም አያቱ በሞተበት ዓይነት የእባጭ በሽታ ተያዘ። ከዚያም ራሱን እንደ አምላክ የቆጠረው ሰው እንደማንኛውም ፍጡር ሞቶ አስከሬኑ ወደ መቃብር ወረደ። ከዚህ በኋላ በንጉሥ አግሪጳ ሥር ይተዳደር የነበረው የይሁዳ መንግሥት ተመልሶ የሮማውያን ግዛት ሆነ። ቢሆንም የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ልጅ በከፊል በሀገሪትዋ ላይ እንዲገዛ ተሰጥቶት ነበር። ጳውሎስ በይሁዳ ታስሮ በነበረበት ጊዜ ሰላምታ ሰጥቶት የነበረው ይህ ንጉሥ ነበረ።

# የቀላውዴዎስ ከብሪታንያ መመለስ

ንጉሥ ቀላውዲዮስ ብሪታንያን ጐብኝቶ ወደ ሮም የተመለሰው ሄሮድስ አግሪጳ በሞተበት ዓመት ነበረ። እርሱም ወደ ብሪታንያ ተሻግሮ የነበረው ከመቶ ዓመት በፊት ጁሊየስ ቄሳር ጀምሮት የነበረውን ሥራ ጨርሶ ለማጠናቀቅ ነበረ። ስለዚህ ልክ እንዳሰበው የተጀመረውን ሥራ ፈጽሞ ተመልሷል።

እግዚአብሔር የወንጌል መልዕክት በጳውሎስ በኩል ወደ ጠርሴስ፤ በጴጥሮስ በኩል ወደ ኢዮጴ እንዲደርስ እንዳደረገ ሁሉ አሁንም በቀላውዲዩስ ጉዞ የደኅንነት ወንጌል ወደ ብሪታንያ እንዲደርስ ሚስጢራዊ በሆነ መንገድ አቅዶ ይሆናል።

የቀጣ ቃል የሚመስለው አስፈሪው የባሕሩ ትመት ከሮም ግርግ ጋር በመነጻጸር በሕዝቡ አፍ ይነገር ነበር። ስለዚህ ሮም በነበራት ወታደራዊ ኃይልና ከባድ መከላከያ ትከበርና ትፈራ ከነበረው በላይ አጠቃላይ ገጽታዋንና ሞገስዋን ለማሳየት ይነገርላት በነበረው ማዕበላዊ መልክ የበለጠ ትከበርና ትታፈር ነበር።

# ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ

አሕዛብን ወደ ደኅንነት ለማምጣት ሐዋርያው ጳውሎስ ራቅ ወዳሉት የአሕዛብ አገሮች ማለትም ወደ ፊንቄ፣ ቆጵሮስና አንጾኪያ ተልኮ ነበር። በዚያኑ ዘመን የፍቅርና የማጽናናት መንፈስ የተሰጠው በርናባስም ሕዝቡን በቃሉ ለማጽናትና ለማበረታታት እስከ አንጾኪያ ድረስ እየሄደ ያገለግል ነበረ። ሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያ ወደ ጌታ በመጣ ጊዜ ሌሎቹ ሐዋርያት ሊቀበሉት ሳይደፍሩ ቀርተው ገሸሽ ሲያደርጉት እጁን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም የወሰደው በርናባስ ነበር። በዚህ ላይ በርናባስ ከቀሩት ደቀ መዛሙርት ይልቅ ምን ያህል ሰውን የመቀበልና የማጽናናት ተሰጥኦ እንዳለው ማስተዋል አያስቸግርም። እርሱም በአሕዛብ መካከል ባገለገለበት ወቅት ጳውሎስን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ ሄደ፤ ባገኘውም ጊዜ ይዞት ወደ አንጾኪያ መጣ። ጳውሎስና በርናባስም በዚያች ከተማ ለአንድ ዓመት አብረው አገለገሉ። ምናልባት አማኞች ለሆኑት ሁሉ ክርስቲያን የተባለው ስም የተሰጣቸው በዚያ ዓመት ውስጥ እንደሆነ ይመስላል። በመጀመሪያ ጊዜ የአንጾኪያ አማኞች ስማቸውን ክርስቲያን በማለት ስለሰየሙት በአካባቢው ሕዝብ መሳገሚና መሳለቂያ ሳይሆኑ አልቀሩም። ሆኖም ይህንን ስም ለመሰየም በወቅቱ ከአንጾኪያ የተሻለ የተመቻቸ ስፍራ አልነበረም። አንጾኪያ ከዓለም ሁሉ ጋር የሚያገናኝ መስመር ነበራት። ስለዚህ ክርስትና በአንጾኪያ መጀመሩ የወንጌል ዜና ዓለምን ሁሉ እንዲያጥለቀልቅ ከማንኛውም ስፍራ አመቺ ነበረ።

# አንጾኪያ የምትገኝበት ሁኔታ

የሶርያዋ አንጾኪያ ከእስክንድር በኋላ ነግሦ በነበረው ሴሉስስ በተባለው ሰው እንደተገኘች ቀደም ሲል ተወስቷል። እርሱም ከጥንታዊዎቹ ታላላቅ የከተማ ሕንፃዎች አናጢ አንጋፋው ነበር። ጳውሎስ አንጾኪያን ለመጀመሪያ ጊዜ ጐብኝቷት በነበረበት ወቅት በጣም በኃጢአት

የተበከለችና ስነ ምግባር የጐደላት ከተማ ነበረች። «እጅግ የተዋበችዋ የሮማውያን ግዛት የሆነችው ክፍል ግን መንፈስን የሚያድስና የሚያረካ የአየር ጠባይ ነበራት፤ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ የግሪክና የሩቅ ምስራቅ ሕዝብ ጥርቅሞች ጭምር የሚኖሩባት ነበረች። ከእነዚህም መካከል አንጾኪያን በሕዝብ ብዛት የሚወዳደራት ሌላ ከተማ ጨርሶ የለም። ስለዚህ በመጀመሪያው መቶ ዓመት የክርስትና ዘመን ውስጥ እውነተኛው እምነት በተለያዩ የአሕዛብ አማልክት ልማዶች ጋር ምን ያህል እንደተወሳሰበ መገመት አያስቸግርም።

# ክፍል 4

## የጳውሎስ የመጀመሪያው ወንጌላዊ ጉዞ

### በቆጵሮስ ስልማናና ጳፋ

ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ጥቂት ካገለገሉ በኋላ ጌታ ወደ ሌላ ስፍራ እንዲሄዱ አዘዛቸው። በዚያም እንደደረሱ በስፍራው የሚገኙት የቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎችና ነቢያት ለተጠሩበት ተግባር አገልግሎታቸውን እንዲሰጡ እጃቸውን ጭነው ከጸለዩላቸው በኋላ አሰናበቱአቸው። ከዚያም ሴሌውቅያ ከተባለው ከአንጾኪያ ወደብ ተነስተው በርናባስ ወደ ተወለደባትና ብዙ አይሁዶች ወደሚኖሩባት ወደ ቆጵሮስ ደሴት ሄዱ። በጥንት ዘመን የዚህች ስፍራ ነዋሪዎች ፊንቄአዊያን ሲሆኑ በኋላ ደግሞ የግሪክ ሰዎች ይኖሩባት ጀመር። ግሪኮች በጣም አጸያፊ የሆኑትን የጣዖት አምልኮ እርኩሰታቸውን ለመፈጸም የሚገኙባት ስፍራ ቆጵሮስ ነበረች።

ከዚህ በኋላ በሁለቱ ከተማዎች ማለት በስልማናና በጳፋ ወንጌል መስበክ ጀመረ። በኋላም የሮማውያን አገረ ገዢ የነበረው ሰርግዮስ ጳውሎስ ጌታን የግል አዳኙ አድርጎ በመቀበል ተለውጧል። ሆኖም አገረ ገዡ ባመነበት ወቅት ከእውነት መንገድ ሊያጣምመውና የሚነግሩትን እንዳይሰማ ይከለክለው የነበረ በርያሱስ ወይም ኤልማስ የተባለ ጠንቋይ ሰው አስቸግሯቸው ነበር። በዚያን ዘመን በዚህ አገር ብዙ ጠንቋዮችና አስማተኞች ስለነበሩ በተለይ ተራው ሕዝብ በማስጠንቀል ነገር ይተባበራቸው ነበር። እነዚህ ጠንቋዮች ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ስለሚገመቱ ተራ ነገሮች አዲስ ነገር የሚመጣ በማስመሰል እያወሩ ስለወደፊት ሁኔታ መረዳት የሚፈልጉትን ሰዎች ያስገርሟቸው ነበር። በጥንቆላ መንፈስ ውስጥ የነበረው ሰው የአገረ ገዢውን እምነት ለመከልከል ሐዋርያትን ተቃውሞ ነበረ። ሐዋርያውም እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በገጠመው ጊዜ ሁሉ አጥብቆ ይቃወም ነበረ። በተለይ በዚህ ወቅት አገረ ገዢውን ከማመን ለመከልከል ይታገል የነበረውን ጠንቋይ በብርቱ በመቃወም ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ሲገስጸው እንዲታወር አድርጎታል። አገረ ገዢውም ይህንን ታልቅ ተአምር ባየ ጊዜ ይበልጥ ልቡ ተነሳስቶ የጸና እምነት ሊኖረው ችሏል።

## የማርቆስ መመለስ - ጴርጌን - የጵንፍልያዋ አንጾኪያ

ሐዋርያትም በመርከብ ሆነው የጵንፍልያን ባሕረ ሰላጤ አቋርጠው በመጀመሪያ የጵንፍልያ ዋና ከተማ ወደምትሆነው ወደ ጴርጌን መጡ። ማርቆስ እስካሁን ድረስ በጴርጌን ነበረ። በርናባስና ጳውሎስ ወደ ጲስድያ አብረውት ለወንጌል አገልግሎት መጥተው በነበሩበት ወቅት በገጠማቸው ችግር አብሮአቸው ሳይቆም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። በዚህን ጊዜ እንደገና ሲያገኙት እፍረትና ቅሬታ ሊሰማው ይችላል። እነርሱም በጴርጌን ብዙ ሳይቆዩ ጵንፍልያንና ጲስድያን በሚያካፍለው ተራራማ ምድር በማቋረጥ ወደ አንጾኪያ ደረሱ። ሐዋርያው ጳውሎስ በኋላ በመልዕክቶቹ ላይ እንደገለጸው በእነዚህ አደገኛና አስፈሪ በሆኑ መንገዶች ላይ አብዝቶ ስለተመላለሰ ሳይለማመደው አልቀረም። በእነዚህ ተራራማ መንገዶች ላይ መጓዝ አብዛኛውን ጊዜ በክፉ የዱር አውሬዎች አፍ ወይም ከተራራ ላይ ድንገት ሞልተው ቁልቁል በድንጋይ ሰንጣቃዎች ውስጥ በሚያልፉ ደራሽ ወንዞች ውስጥ ለመውደቅ ያጋልጣል። ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ የአይሁዶችን መንፈስ የሚቀሰቅስ ታላቅ መልዕክት በአንጾኪያ ምኩራብ ውስጥ ሊሰብክ ችሏል። እርሱም በክርስቶስ የሚገኘውን የጸጋ ስጦታ አይሁድና አህዛብ ሳይለይ በእኩልነት አበረከተው። አይሁዶች እግዚአብሔር አሕዛብንም ከእነርሱ እኩል አመጣጥና ስለወደዳቸውና ይህን ፀጋ ሳያዳላ በመስጠቱ ቁጣቸው ገንፍሎ በጣም ተናደዱ። በዚህ ሳቢያ አንዳንድ አይሁዶች ሴራ ፈጥረው ከተማይቱን እጅግ በመረበሽ ታላቅ ተቃውሞ በሐዋርያት ላይ ስላስነሱ በራሳቸው ሕዝብ ላይ የኢግራቸውን ትቢያ አራግፈው የጵስድያ የሆነችውን አንጾኪያ ለቀው ወጡላቸው።

## ኢቆንዮን - ደርቤ - ልስጥራ - የጳውሎስ መወገር

ሐዋርያቱ በምዕራብ አቅጣጫ 150 ኪሎ ሜትር ጉዞአቸውን እንደቀጠሉ ወደ ኢቆንዮን ደረሱ። ይህችም ከተማ በኋላ ኮኒህ ተብላ የተሰየመች ናት። በጥንት ጊዜ በጦርነት ድል አድራጊ የሆኑ ሕዝብ በኃይል ተነስተው ቁርኮችን ያሸነፉት ከዚህች ቦታ ስለነበረ የድል በአል ማስታወሻ ሆና ተከልላ ነበር። ነዋሪዎችዋም የሚከተሉት ናቸው። «አብዛኛዎቹ ሕዝብ ግሪኮች ሲሆኑ ጥቂቶቹም ከጥንቶቹ መካከል የተረፉት የሸመገሉ ሰዎችም ነበሩባቸው። ሌሎቹ ደግሞ ጥቂት ሮማዊ ሹማምንትና ከጥንት የተረፉ አንዳንድ ቅኝ የነበሩ አይሁዶችም ነበሩባቸው።» ሐዋርያት በአንጾኪያ በነበሩበት ጊዜ ለእነኚህ ቅኝ ሕዝብ ከሚደረግላቸው የተለየ አቀባበል አይደረግላቸውም ነበር። ስለዚህ አስተዳደራቸው በትክክል ይመራ ወደነበሩት ወደ ደርቤና ወደ ልስጥራ ኮብልለው ሄደዋል። በልስጥራ ሳሉም አንድ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ሽባ የነበረ ሰው በመፈወሱ በተለይ በዚያ ይኖሩ የነበሩት ግሪኮች ጁፒተርና ሜርኩሪ እያሉ ያመልኳቸው የነበሩትን አማልክት እንዲያስታውሱ አድርጓቸዋል። ስለዚህ ሐዋርያትንም እንደ አማልክት ሊያመልኳቸው ስለፈለጉ ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚህ ከንቱ ነገር ተመልሰው ሰማይና ምድርን የፈጠረውን አምላክ እንዲያመልኩ ይመክራቸዋል። እነዚህ በመጀመሪያ ሐዋርያትን ለማምለክ ተነሳስተው የነበሩት ሕዝብ በሌላ ጊዜ ከአንጾኪያና ከኢቆኒዮን በመጡ አይሁዶች ተገፋፍተው ሐዋርያ ጳውሎስን እስከ ሞት በድንጋይ ወገሩት። በኋላ ግን ሐዋርያው ነፍስ በመዘራት ተጠናክሮ በሕይወት ሊኖር ችሏል።

# የጢሞቴዎስ መለወጥ

የሐዋርያውን መልዕክት ያዳምጡ ከነበሩት ሕዝብ መካከል ሀሳቡ በምንም ነገር ሳይወሰድ የእግዚአብሔርን ቃል በአንክሮ ይሰሙ ከነበሩት መካከል አንዱ ወጣቱ ጢሞቴዎስ ነበረ። እርግጥ ጢሞቴዎስ ገና ከብላቴንነቱ ጀምሮ በእናቱና በሴት አያቱ በኩል ቃሉን በመስማት ተኮትኩቶ ያደገ ነበር። ሆኖም ቃሉን የመስማቱ እብይ ምክንያት እንደዚህ ጊዜ ልብን ዘልቆ የገባበት ጊዜ አልነበረም። ጳውሎስ ወደዚህ ስፍራ መጥቶ ወንጌልን ከሰበከለት ወዲህ ግን ሕይወቱ በፍፁም ስለተለወጠ ቃሉ ትርጉም እየሰጠው ከሕይወቱ ጋር ይዋሀድ ጀመር። ከዚህ በኋላ ራሱ የወንጌል አገልጋይ ሆኖ በመነሳት ዕድሜውን ሁሉ የኢየሱስን አዳኝነት ሲያውጅ ኖሮ ወደ አባቶቹ ተሰብስቧል።

# ወደ ሶርያዊ አንጾኪያ መመለስ

ጳውሎስና ባርናባስ አስቀድመው ቃሉን በተናገሩበት ስፍራ የሚገኙትን አማኞች ለማጠናከርና ለማጽናናት ተመልሰው ወደ አንጾኪያ ለመሄድ ጉዞአቸውን ይጀምራሉ። እርግጥ በዚያ ስፍራ ታቃውሞና ፈተና እንደሚገጥማቸው ያውቃሉ። ሆኖም መንጋውን የመመገብና የመጠበቅን ኃላፊነት ከእግዚአብሔር ስለተቀበሉ ወደዚያ ስፍራ ተመልሶ መሄድ ግዴታቸው ነው። በዚህን ጉዞአቸው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደጐበኟት የተናገሩት በጵንፍልያ ባሕር ዳር የምትገኘው ኢጣልያ ነበረች። እነርሱም ከዚህ በመርከብ ተነስተው ወንጌል ለአሕዛብም እንዲዳረስ በድጋሚ ወደ ሰሙአቸው ወገኖች በሶርያ ወደምትገኘው አንጾኪያ ሄዱ። እግዚአብሔር ለአሕዛብ የከፈተላቸው የደኅንነት በር ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ ግልጽ ሆኖ የታየው በዚህን ጊዜ ነበር።

# የኢየሩሳሌሙ ጉባዔ

በኢየሩሳሌም በሚገኙት ክርስቲያኖች መካከል ይኸንን የደኅንነት መንገድ የሚቃወሙ ገና የፈሪሳውያንን ትምህርት የሚከተሉ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በዚህን ጊዜ ተደማጭነት ስለነበራቸው ብዙ ተከታዮች ነበሩአቸው። በተለይ የሶርያዋ አንጾኪያ በመጀመሪያ የደኅንነት መንገድ በክርስቶስ ሞት በኩል ብቻ እንደሆነ የተማረችና የምታምን ቢሆንም በኋላ ከእነዚህ ክርስቲያኖች ትምህርት ስለበከለች ደኅንነት የሥጋን ግዝረትንም ያጠቃልላል ስትል ከእውነት መንገድ ልትስት ችላለች። በኋላ ግን አንዳንድ በአንጾኪያ ከሚኖሩ ወንድሞች በርናባስና ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ትምህርት እንዲሰጡበትና የሳቱት ወደ እውነት እንዲመለሱ ሀሳብ አቀረቡ። እነዚህ ወንድሞችም ትምህርት ለመስጠት ወደ አንጾኪያ በመምጣት ላይ ሳሉ እግረ መንገዳቸውን በፊንቄና በሰማርያ አልፈው ታላቅ የወንጌል አገልግሎት ሰጥተው ነበር። በዚያም ብዙ ነፍሳት ባስተላለፉት መልዕክት ልባቸው ተጠግኖ ታላቅ መነቃቃትን አግኝተዋል። በመጨረሻም ላይ ጳውሎስና በርናባስ ኢየሩሳሌም ደረሱ። በዚህን ጊዜ ጳውሎስ ከተለወጠ አስራ ሰባተኛው ዓመቱ ሲሆን ክርስቲያን በመሆኑ በዚህች አገር መከራ ከተቀበለ ደግሞ አሥራ አራት ዓመቱ ነበረ፤ ገላ.2፡1። ጴጥሮስ የተናጋሪዎቹን

አድራሻ ለጉባዔው ያስታውቃል። እነርሱም ጳውሎስ፣ በርናባስና ያዕቆብ ናቸው። ዮሐንስም በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ነበር፤ ሆኖም ምንም አልተናገረም፤ ገላ.2፡9። የአይሁድን ሥርዓት ስለሚመለከተው የግዝረት ጉዳይ ሊከራከሩ የመጡት ሰዎች የስም ዝርዝር አልተነገረም። በመጨረሻ ግን ጳውሎስ እርሱ በዝርዝር ከገለጻቸው ሁኔታዎች በቀር በክርስቶስ ባሉት ላይ ሌላ ሸክም ሊጫንባቸው አይገባም ብሎ በሰጠው ሀሳብ ላይ ጉባዔው ሁሉ ተስማማ። ከአይሁድ ወገን ባመኑት ክርስቲያኖች ምክንያት ሌላ በክርስቲያኖች ማድረግ የማይገባቸው ጥቂት ነገሮች ነበሩ፤ አንደኛው ዝሙት ነው፤ ለጣዖት የተሰዉትን እንዳይበሉና አምልኮታቸውን በሚመለከት ነገርም እንዳይተባበር ተከልክሏል። እነዚህ ነገሮች አብዛኛዎቹ በአንጾኪያና በጲርጊን ይደረጉ ከነበሩ የአምልኮ ሥርዓቶች ጋር የተያያዙ ነበሩ።

## ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ መመለስ

በኢየሩሳሌም ከነበረው ስብሰባ በኋላ ጳውሎስና በርናባስ በርስያ የተባለውን ይሁዳና ሲላስን አስከትለው ወደ አንጾኪያ ተመለሱ። በዚህን ጊዜ ጴጥሮስ ደግሞ አንጾኪያን የጉበኘ ይመስላል፤ ገላ.2፡11። ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ በአንዳንድ በተሳሳቱ ወንድሞች ተታልሎ ካልተገረዙ ከአሕዛብ ወገን ከዳኑት አማኞች ጋር መብላት ተገቢ አይደለም የሚለውን አሳብ ተቀበለው። ከዚህ ሀሳብ መሠረት ጴጥሮስ በአሕዛብ ክርስቲያኖችና በአይሁድ ክርስቲያኖች መካከል አድልዎ ሲያደርግ አይቶ ጳውሎስ ፊት ለፊት ገሠፀው፤ ገላ.2፡14።

## በጳውሎስና በጴጥሮስ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት

በአንጾኪያ የተደረገው ትዕይንት አስደናቂ ነበረ። በክርስትናና በአይሁድነት መካከል የነበረው ልዩነት በሁለቱ ሐዋርያት መካከል ለጥቂት ጊዜ ያህል ከባድ ቅራኔን ፈጥሮ ነበር። እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን፤ ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤ ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንደሚጸድቅ እንጂ በኦሪት ሕግ ሥራ እንዳይሆን አወቅን። ሥጋን የለበሰ ሁሉ በኦሪት ሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንድንጸድቅ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። ይህ ዓረፍተ ነገር በሮሜና በገላትያ የተደረገውን ክርክር አጠር ባለ መልክ ያጠቃለለ ነው።

# ክፍል 5

## ሁለተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ

## ሲላስ - ጢሞቴዎስና ሉቃስ

### የጳውሎስና የበርናባስ መለያየት - ጳውሎስና ሲላስ በእስያ

በአንጾኪያ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ጳውሎስ ቃሉን በሰበኩንባቸው አካባቢ ሁሉ ዞረን ወገኖች እንዴት እንዳሉ እንጐብኛቸው ሲል ባርናባስን አማከረው። በርናባስ በሀሳቡ የተስማማ ቢሆንም በጉዛአቸው ሁሉ የእህቱ ልጅ የነበረውን ማርቆስን ማስከተል ፈለገ። ጳውሎስ ግን በጵንፍልያ በነበሩበት ወቅት ማርቆስ ጥሏቸው ሄዶ ስለነበረ አልተማመነበትም። በዚህ ጊዜ በሁለቱ ሐዋርያት መካከል የሀሳብ ግጭት ስለተፈጠረና መግባባት ስላልቻሉ ተለያይተው በየግላቸው ለማገልገል ተስማሩ። ከዚህ በኋላ በርናባስ ከማርቆስ ጋር ወደ ቆጵሮስ ሲሄድ ጳውሎስ ደግሞ ከሲላስ ጋር ሆኖ ወደ እስያ ለመሄድ ረጅሙን ጉዳና ተያያዘው። ስለዚህ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የሰጠው ማስረጃ በጣም ጥቂት ቢሆንም ባጭሩ የተቀመጠው መግለጫ ለታሪኩ እውነተኛነት ፍፁም ማረጋገጫ ሰጥቶታል።

### ሶርያና ኪልቅያ - ደርቤና ልስጥራ - ጢሞቴዎስ ዮሐንስና ጳውሎስ

ጳውሎስና ሲላስ በመጀመሪያ እስያ እንደደረሱ አገልግሎታቸውን የሰጡት በሶርያና በኪልቅያ ለሚኖሩት ምዕምናን ነበረ። እነዚህ አማኞች ጌታን የተቀበሉት በሐዋርያው ጳውሎስ ሰብከት ሲሆን ጊዜውም ገና ሐዋርያው በተሰወጠበት አካባቢ ነበረ። ሐዋርያው በዚህን ጊዜ በጠርሴስ የሚገኙትን ወገኖቹን ሳይጐበኛቸው እንዳልቀረ አያጠራጥርም። ሆኖም በዚያ ምን እንዳደረገ የሚገልጽ ማብራሪያ የለም። ከዚህ ቀጥሎ ጳውሎስ ከጠርሴስ ደቡባዊ ሰሜን በሚወስደው መንገድ ባለው አካባቢ ጉብኝቱን ካደረሰ በኋላ ዞሮ ወደ ደርቤና ልስጥራ ተመልሷል። ጳውሎስ በዚህ ጉዞው ይበልጥ ያስደሰተው ነገር ወጣቱ ጢሞቴዎስ በጌታ ፀጋ እያደገ መሄዱን ማየቱና ስለ እርሱ ጤናማ መንፈሳዊ ሕይወት ከሁለቱም ማለት ከልስጥራና ከኢቆንዮን ወንድሞች ምስክርነት መስማቱ ነበረ። በዚህን ጊዜ ጢሞቴዎስ ደግሞ በበኩሉ ጌታን ለማገልገል ጳውሎስንና ሲላስን ተከትሎ ይነሳል። ይህ በመሆኑ እናቱና አያቱ በኃዘንና በደስታ ልባቸው እየናወዘ እንባ ይተናነቃቸው ጀመር። ደስታቸው እግዚአብሔር ለዚህ ለተቀደሰ ሥራ ልጃቸውን ስላስነሳው ሲሆን ኃዘናቸው ደግሞ ከቤተሰባቸው ሕብረት ውስጥ

ጢሞቴዎስን የመሰለ የእግዚአብሔር ሰው ተለይቶ ወደ ገላትያና ፍርግያ በረሃ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር መሄዱ ነው።

## ገላትያ

ይህ ገላትያ የተባለው ስም የተወረሰው አባቶቻቸው ከአራት ትውልድ በፊት ጋዋል እየተባለ በሚጠራ የወርካ ዛፍ ሥር እያመለኩ በወቅቱ ይጠሩበት ከነበረ ጋሊክ ከተባለው ስም እንደሆነ ተረጋግጧል። ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ያሉት የገላትያ ሰዎች ጥንታዊ አባቶቻቸው ከምዕራብ አውሮፓ ወደ ምዕራብ እስያ እየተጓዙ በነበረበት ወቅት በመንገድ ላይ የተወለዱ ናቸው። ከዚህም በቀር ሮምና ግሪክም በመጀመሪያ ጊዜ የተገኙት በእነዚሁ ጋውል በተባሉ በገላትያ የጥንት አባቶች እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። የገላትያ ታሪክ የተያያዘው ከጥንቱ ሁኔታ ጋር ብቻ ሳይሆን ከዚያም ወዲህ ከተፈጸሙ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ አፈጻጸም አለው። ሆኖም የጥንት ታሪካቸው ከሚያትተው ሁኔታ እንጻር የገላትያ ሰዎች በግሪክ በመቆየት ፋንታ ወደ ኋላ አፈግፍገው በመመለስ በኤጅያን ባሕር በኩል አቋርጠው መኖሪያቸውን በእስያ አህጉር መካከል መሥርተዋል። ሐዋርያው ጳውሎስም ወደዚህ ስፍራ መጥቶ ሊጎበኛቸው የቻለው ጤንነቱ ተቃውሶ ደህና ባልሆነበት ጊዜ እንደሆነ ይመሰላል፤ ገላ.4፡13። እነርሱም የሥጋውን ሕመም ሳይጸየፉ በፋንታው የራሳቸውን ዓይን እንኳ አውጥተው ሊሰጡት ፈቃደኞች እስከሚሆኑ ድረስ በታላቅ ፍቅር ተቀብለውት እንደነበረ ያሳስባቸዋል፤ ገላ.4፡15። ከዚያም ብዙ ሳይቆዩ በአይሁድ መምህራን ተታለው ትተውት ወደ ነበረ ወደ አይሁድ ሥርዓትና አምልኮ ተመለሱ። የገላትያ ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስ በመካከላቸው በነበረበት ወቅት በክርስቶስ ከነበራቸው የሕይወት ለውጥ የተነሳ ዓይናቸውን ሊሰጡት እስከሚፈልጉ ድረስ ታላቅ መነቃቃት ያላቸው ቢሆኑም በቀላሉ የሚሸነገልና የሚዋልል አቋም ስለነበራቸው ፈጥነው ከእምነታቸው ሊሰናከሉ ችለዋል።

## ጢሮአዳ

ሐዋርያው ጳውሎስ በፍርግያና በገላትያ አድርጐ ካለፈ በኋላ አቅጣጫውን በታላቁ ባሕር ዳር ወደሚገኘው ወደ ኤፌሶን ወደብ መቀየስ የተለመደ ተግባሩ ነበር። ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ጴርጋሞን፥ ሰርዴስ፥ ፊልደልፍያ፥ ሎዶቅያ፥ ሰምርኔስና ትያጥሮን ከተማዎች ለተለየ ዓላማ የሚሄድበት ጊዜ አለ። ቡትለይ በዚህን ጊዜ ሐዋርያውና የሥራ ባልደረቦቹ በእስያ ቃሉን እንዳይሰብኩ መንፈስ ቅዱስ ይከለክላቸዋል። ሆኖም በእስያ ባሕር ወደብ አካባቢ ወደምትገኘው የቅኝ ግዛት ወደሆነችው ምድር ይጠራሉ። ቢታንያም ሊገቡባት እንደማይችሉ ሆና ጀርባዋን አዙራባቸው ተዘግታ ነበር። በዚህን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለመንገዳቸው ክፍት እንድትሆን አድርጐ የሰጣቸው ቦታ ብትኖር ቀድሞ ጢሮአዳ እየተባለች የምትጠራዋ የአሁኒትዋ ጢሮስ ናት።

## መደበኛ ሕብረት - ሉቃስና ዮሐንስ የመቄዶንያው ሰው ራዕይ

በግሪኮች ታሪክ ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደዚህ ወደ መቄዶንያ ሜዳማና ዝነኛ ስፍራ የተመለከተው በታላቅ ፍላጐት እንደሆነ ይነገራል። በዚህ በግሪኮች ዝነኛ ታሪክ መሠረት ጢሮሳውያን አገራቸውን ለመውረር በሚያደርጉት ሙከራ ጋት ያህል እንኳን ላለማስነካት ለአሥር ዓመት ያህል ሽንጣቸውን ገትረው እንደተቋቋሟቸው ይነገራል። በኋላም በሆመር አማካይነት አገሪትዋ ተረጋግታ ሰላምና ፀጥታ ይሰፍንባትና በቀድሞው የሥልጣኔ ጐዳና ትገሰግሳለች። በዚህን ጊዜ ጳውሎስ ካሁን ቀደም አይቶት የማያውቀውን የአውሮፓውያን አገር በተራራማው ምድር አሻግሮ በራዕይ ይመለከታል። ከዚያም አንድ የመቄዶንያ ሰው ወደኛ መጥተህ እርዳን ሲል ይሰማዋል። ይህን በሁለቱ የአውራ በግ ቀንዶች የተመሰለውን ድል አድራጊ የግሪክ መንግሥት በራዕይ ሲመለከት መቼ በገባሁና የክርስቶስን የማዳን ወንጌል በተናገርሁ ብሎ ሳይቋምጥ አልቀረም። በተለይ የመቄዶንያውን ሰው ልመና የመሰለውን ጥሪ ችል ብሎ ማለፍ ስለሚያስቸግር በነጋታው በመጀመሪያው መርከብ ለመሄድ ወሰኑ። በነጋታውም ልክ እንደተናገሩት በመጀመሪያው በጢሮስ መርከብ ተሳፍረው በማዕበሉ ወዲያና ወዲህ እየተንገላቱ ጉዞአቸውን ወደ መቄዶንያ ቀጠሉ። እነርሱም በመርከብ ውስጥ ከተለያዩ ከኤሮፕ አገር የሆኑ ነዋሪዎችን በተመለከቱ ጊዜ ግሪኮችን ብቻ ሳይሆን አውሮፓውያንን በሙሉ ወደ ክርስቶስ ፀጋ ለመማረክ ልባቸው ተቀሰቀሰ።

## በመጀመሪያ ጊዜ በኤሮፓ የተደረገው የወንጌል ስብሰባ - ፊልጵስዩስ

በመጀመሪያ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በኤሮፕ ውስጥ የተሰበከው በመቄዶንያ ሲሆን ከዚያም ወደ ፊልጵስዩስ፥ ተሰሎንቄና ቤርያ ድረስ ተዳርሷል። ፊልጵስዩስ የሮማውያን «ቅኝ» ግዛት ናት። ስለሆነም በቦታዋ ብዙ የንግድ ልውውጥ አይታይባትም። በዚህ ፋንታ ግን በከተማዋ ውስጥ አብዝተው የሚታዩት ወታደሮች ብቻ ነበሩ። በከተማዋ ውስጥ የተሠሩ የፈሪሳውያን ምኩራቦች አልነበሩም፤ ይህ በመሆኑ በከተማዋ የሚገኙት ጥቂት የአይሁድና የአሕዛብ ክርስቲያኖች ያለ አንዳች እንቅፋት በሕብረት ያመልኩ ነበረ። የአምልኮ ስፍራቸውም በወንዝ ዳር አካባቢ በሚገኙ ቦታዎች ላይ ነበረ። ሐዋርያት በመጀመሪያ ጊዜ ወደ ፊልጵስዩስ ሲመጡ አንዲት ነጋዴ ሴት፥ በእርኩስ መናፍስት የምትሰቃይ ልጃገረድና አንድ የእስር ቤት ጠባቂ የሆነ ሰው ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው ተቀብለው ድነዋል። በዚህ ሁኔታ እነዚህ ሦስት ሰዎች በኤሮፕ ለተመሰረተችው አዲስ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ አካል ሆነዋል ማለት እንችላለን። ከዚህ በኋላ ክርስቶስ በእነርሱ የመሆኑ ውጤት በሕይወታቸው ያስከተለውን ለውጥ እናያለን። ሴቲቱ ይህን ደኅንነት እንዳገኘሁ ከፈረዳችሁልኝ ወደ ቤቴ መጥታችሁ ተሰተናገዱ ስትል ግድ ትላቸዋለች። የወህኒ ጠባቂውም ለጠየቀው ጥያቄ ሐዋርያው መልስ ሲሰጥ የወንጌልን አብይ ዓላማ በጥቂት ዓረፍተ ነገር በማጠቃለል ተናግሯል። ጥያቄው «ለመዳን ምን ማድረግ ይገባኛል?» የሚል ነበረ። መልሱ «በኢየሱስ

ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ» የሚል ነበረ። የእግዚአብሔር መንፈስ አብረታቺነትና ደጋፊነት ደግሞ በሐዋርያው ጳውሎስና በሲላስ ውስጥ በደንብ ይታይ ነበር። ምክንያቱም በእስር ቤት ውስጥ ተጥለው በግንድ ሲጠረቁ በኃዘንና ተስፋ በመቁረጥ ፋንታ ይዘምሩና ደስ ይላቸው ስለነበረ ነው። ፊልጵስዩስ ገና ከመጀመሪያው ላገኘችው ደስታና መለወጥ ተቃራኒ የሆነ ነገር ማለት መከራ፣ ስደትና እስራት ካላመኑት ሰዎች ደርሶባታል። የወህኒ ቤት ጠባቂው ከመለወጡ በፊት ራሱን በሰይፍ ሊያጠፋ በቃጣ ጊዜ ሐዋርያው «በራስህ ላይ ክፉ አታድርግ» ብሎ አገደው።

## ተሰሎንቄ

ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ ተነስቶ በጣም በሥራ ወደምትተጋና ተወዳጅ የሆነ ወደብ ወዳላት ወደ ተሰሎንቄ አለፈ። በዚያም በክርስቶስ ፍቅር ሆነው የሚመጣውን ተስፋ በትዕግሥት የሚጠብቁ ክርስቲያኖች ነበሩ። በዚህ ሥራ የሚኖሩ አረማውያን ይሆን አዲስ እምነት ከተቀበሉ በኋላ ዝናውን ይዘው በአንድ ጊዜ በመቄዶንያና በአካይያ አካባቢ ለሚኖሩት ወገኖቻቸው ሁሉ አደረሱት።

## ቤሪያ - የጳውሎስ ወደ አቴና መጓዝ

ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ በስደት እንደወጣ ሁሉ አሁንም ከተሰሎንቄ በስደት ተባሮ ይወጣል። ከዚያም በቤሪያ ከተማ ጥገኝነት ጠይቆ በሚስጥር ሲሠራ ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ደኅንነት አምጥቷል። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ታላላቅ ባለሥልጣኖችና አገረ ገዢዎች ነበሩባቸው። በኋላም ጉባዔው እየበረከተ ሲሄድና ሰፊ ስብሰባ ሊደረግ በተወሰነ ጊዜ ወንድሞች ጳውሎስ በፍጥነት ከቤሪያ እንዲወጣ ሲያደርጉ ሲላስና ጢሞቴዎስ ግን በዚያው እንዲሰነብቱ ሆኗል። ከዚያም ጳውሎስ በመርከብ ሆኖ ወደ አቴን ይሄዳል። በመንገድ ሰላም መርከቡ በባሕር ላይ እየተንሳፈፈ የባሕሩ ማዕበል ከወዲህ ወዲያ ሲወረወርና የፀሐይዋ ውጋጋን ሲያንጸባርቅ ልዩ በሆነ የተፈጥሮ ደስታ ተመስጦ ውስጥ ይገባ ነበር። እርሱም በጉዞው ላይ ሆኖ የብርሃንን አጠላለቅ የንጋትን ነጸብራቅ ከአካባቢው ተራሮችና ዱሮች ጋር ሲያስተያይ የእግዚአብሔር ሥራ እጹብ ድንቅ እንደሆነ ተረድቷል። በመጨረሻም እርሱ ያያቸውን የተፈጥሮ ውበት ከግሪኮች ፍልስፍና ጋር ሲያመዛዝን በዚያ ሁሉ እውቀታቸው የእግዚአብሔርንና የሥራውን እጹብ ድንቅነት ገና እንዳልደረሱበት ይገልጻል።

## አቴና የምትገኝበት ሁኔታ

ጳውሎስ በአቴና ላለ በአካባቢው የሚመለከታቸውን ጥቃቅኑንም ሆነ ግዙፍ ነገሮች ይሰማው ከነበረ ነገር ጋር አጠቃሎ መዘርዘር ሰፊ ቦታ ይይዛል። ሆኖም ጳውሎስ ከብዙ ጉዞ በኋላ የተሳፈረበት መርከብ ከተማውንና ወደቡን በሚያገናኝ ረጅም ግድግዳ አልፎ ፔርያ ከተባለው ወደብ ይደርሳል። ከዚያም ጠንካራና የማይበገር መከላከያ ያለውን የአቴናን ከተማ ፊት ለፊት ይመለከታል። ጳውሎስ ከተመለከታቸው ነገሮች መካከል አንደኛው ሁኔታ ቶሎ ከአዕምሮው አልሄድለት ይላል። ይኸውም በአቴና የሚገኙት ሰዎች ሁሉ ለሥጋዊ ኑሮ

የሚያመች ነገር ብቻ የተገዙ የመሆናቸው ጉዳይ ነው። ስለዚህ አቴናውያን በአዕምሮአቸው መራቀቅ ሁሉ ነገር የተገለጠላቸው ቢሆን፥ በኪነጥበብ የታወቁ መሆናቸው የእግዚአብሔርን አሠራር እንዲረዱ አድርጓቸው ቢሆን፥ እረማዊ አምልኮአቸው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሚስጥር አሳይቷቸው ቢሆን ኖሮ እነርሱን የሚያክል ቅዱስና ፍፁም የሆነ ሕዝብ ባልተገኘም ነበር። ጳውሎስም በከተማው ውስጥ በሚመላለስ ጊዜ ብዙ የሚሰግድላቸውና የሚመለኩ በድንጋይ የተቀረፁ ጣዖቶችን ይመለከት ነበር። በእነዚህ ጣዖታት መካከልም የመሰዋዕት እጣን የሚያጨሱባቸው ዕቃዎች ነበሩ። በአጠገባቸውም «ላልታወቀ አምላክ» የሚል ጽሑፍ በትልቅ ፊደል ተጽፏል። በጠቅላላው አቴና የፍልስፍና ሁሉና የተለያዩ የጣዖት አምልኮዎች መዲና ነበረች ማለት ይቻላል። ከዚያም በከተማው ውስጥ መዘዋወሩን እንደቀጠለ በድንገት ከሁለት የፈላስፋ ቡድኖች ወገን ከሆኑ ከኤፊቆሮስና ከኢስጦኢኮች ጋር ይገናኛል። ኢስጦኢኮች በሥጋዊና በሰላም መካከል ልዩነት የለም የሚል አስተያየት አላቸው። ይህ ፍልስፍናቸው ውሎ አድሮ መሪዎቻቸው የነበሩትን ሁለት ሰዎች እንዲገድሉ አድርጓቸዋል። በፍልስፍናቸው አንጻር ያደረጉት ነገር ትክክል እንደ ሆነ ስላመኑበት ፈፅሞ አልተፀፀቱበትም። ትዕቢትና መንቦጣረር የኢስጦኢኮች ትምህርት ዋና ዓላማ ነው። የኤፊቆሮሶች ዋና ትምህርት ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ትርፉ ባገኘው ነገር ሁሉ መደሰት ነው ይላሉ። ይህ መንደላቀቅ የፈጣሪ በረከት ምልክት ነው ብለው ስላስተማሩ ለሥጋችን ምቾት እስከሰጠ ድረስ በሁሉ ነገር መደሰት አለብን የማለት ፍልስፍና ነበራቸው። ስለዚህ እነዚህ ወገኖች ሰው በሕይወት ሲኖርም ሆነ ሲሞት በምንም ሳይጨነቅ በግድየለሽነት ነገርን በቀላሉ መመልከት እንዳለበት ያስተምራሉ።

## ጳውሎስ በአቴና ሳለ በሕዝቡ ፊት የተገለጠባቸው ሦስት ጊዜያት

ጳውሎስ በተለያዩ ሦስት ጊዜያት ሕዝብ በተሰበሰበበት ጉባዔ ላይ የእውነትን ቃል ምስክርነት ሰጥቶ ነበረ። የመጀመሪያው በአይሁዶች ምኩራብ ውስጥ ነበረ፤ ሁለተኛው ደግሞ በአጉራ ወይም በገበያ ቦታ ላይ ነው፤ ሦስተኛውና የመጨረሻው ቦታ ሕዝብ አንድ አዲስ ነገር ለማየት ወይም ለመስማት በሚሰበሰብበት ሰፊ አደባባይ ላይ ነው። አንዳንዶች በዚህ ስፍራ ላይ የጳውሎስን ንግግር ሰምተው የነበሩ ፈላስፎች ሕዝብ ባልበዛበትና ፀጥታው በተጠበቀ ቦታ ሆነው ዳግመኛ ሊሰሙት ፈለጉ። ስለዚህ በሌላ ጊዜ አርዮስ ፋጉስ ወደተባለ ተራራማ ቦታ ወሰዱት። ይህ ቦታ የአገሩ ዳኞችና ሽንጉዎቹ ተሰብስበው በጥንት እምነታቸው አንጻር በሥጋዊና በመንፈሳዊ አሠራር መካከል ባለው ልዩነት ላይ የሚወያዩበት ስፍራ ነው። ቦታውም በጣም ፀጥታ የሰፈነበት ነው። መንፈሳዊ ሚስጥር በሆነ ነገር ላይ ለመወያየት በአቴና ከተማ ውስጥ ከዚህ የተሻለ ሌላ ቦታ ጨረሶ አልነበረም። በዚህም ቦታ ፓርቴኖን በተባለው ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደተሰበሰቡ ጳውሎስ እግዚአብሔር እጅ በሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደማይኖር ተናገረ። ከዚያም በቤተ መቅደሱ አካባቢ በሚገኘው ጥላማ ስፍራ ላይ ሚኔራ የተባለው ጣዖት ሰይፍና የራስ ቁር አድርጐ ባየበት ጊዜ እግዚአብሔር በሰው እጅ በተሠራ ወርቅና በብር እንዲሁም በተከረፀ ድንጋይ እንደማይመሰል ነገራቸው። በዚህን ጊዜ ዓለምና በውስጥዋ ያሉት ሁሉ አተም ከተባለ ረቂቅ ንጥረ ነገር ተነስቶ እያደገ የሚያምኑት ኤፊቆሮሳውያን ጳውሎስ ዓለምና ሞላዋ በእግዚአብሔር እንደ ተፈጠረች በተናገረ ጊዜ እንደ

ሞኝ ቆጥረውት እየተሳለቁ ሳቁበት። በዚሁ ስፍራ ጳውሎስ ኩራተኛና ትዕቢተኛ ከሆኑት ከኢስጦኢኮች ወገን ለነበረ ሰው የፍርድ ቀን ከመምጣቱ በፊት በኃጢአቱ ተናዞ ንስሐ እንዲገባ ያስጠነቅቀዋል። እርሱም ንግግሩን በመቀጠል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ደኅንነት በልጁ ሞትና ትንሣኤ በደሙ በኩል በሰጠን የኃጢአት ሥርየት ነው ብሎ አስረዳቸው። በተለይ በንግግሩ ውስጥ ሞትና ትንሣኤ በሚለው ቃል ምክንያት ትንሣኤን የማያምኑት ክፍሎች ንግግሩን አቋረጡት። ስለዚህ ጳውሎስ በኋላ በጻፈው በአንደኛው ቆሮንቶስ መልዕክቱ ውስጥ የመስቀሉ ቃል «ለግሪኮች ሞኝነት ነው» ሲል ጻፈ። በዚህ መልዕክቱ ጊዜም የአርዮስ ፋጎስ ፍርድ ቤት ዳኛ የሆነው ዲዮናስዮስ ከቀሩት ጋር ሁሉ በወንጌሉ ኃይል ተለውጦ ወደ ክርስቶስ ደኅንነት መጥቷል።

## ጳውሎስ በቆሮንቶስ

ጳውሎስ አቴናን የጐበኘው ብቻውን ነበረ። ወደ ቆሮንቶስ በመጣ ጊዜ ግን ሲላስንና ጢሞቴዎስን አስከትሏል። ጳውሎስ በመንገድ ላይ ሳለ «ኢየሱስ ክርስቶስንና እርሱም እንደተሰቀለ» ማስተማር ብቻ እንዳለበት ይወስናል። የስብከቱም ዋና ርዕስ ይሄው ነበር። ቆሮንቶስም በዚያን ጊዜ ትክክለኛይቱ የግሪክ ዋና ከተማ ነበረች። እርስዋም ዝነኛ የሆነች በባሕር የተቀበበች ምድር ስትሆን አስተዳደርዋም በእኩልነት አሠራሩ የጥንታዊውን ታሪክ ምዕራፍ የበለጠ አራዝሞታል። ይሄም የተመሠረተው በሮማውያን ነበረ። የቆሮንቶስም ዋና ከተማ የተመሠረተችው ፒሎፓኒየስ በተባለው ድልድይ ላይ ነበረ። ቆሮንቶስ ታላቅ የንግድ መለዋወጥ የሚደረግባት ሥፍራ ነበረች። እርስዋም በምዕራብ በሚገኘው ወደቧ በኩል ከኤሮፓውያን ጋር የንግድ በር ሲኖራት በምስራቅ ደግሞ ከእስያ ጋር ትገበያይ ነበረ። ስለዚህ ከየአገሩ የሚመጡ የንጋዴዎች መናኸሪያ ስለሆነች በዘማዊነትዋና በእርክስናዋ ከፍተኛውን ስፍራ ይዛ ነበር። ቬነስ የተባለው ጣዖቷም በዚህ ዓይነት መንገድ ይከበር ስለ ነበረ ለአደባባይ ፍትወት የሚውሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አመንዝራ ሴቶችን ያሰልፍ ነበር። በጠቅላላው ምድሪቱ በአመጸኞች፣ በሌሰኞች፣ በጣዖት አምላኪዎች፣ በሌቦች፣ በሰካራሞችና በዘራፊዎች ተይዛ ነበር! 1ኛ ቆሮ.6፡9-10።

## የሲላስ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድና ወደ አንጾኪያ መመለስ

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሳለ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር ይኖር ነበር። እነርሱም በእምነታቸው ምክንያት ከቀሩት አይሁዶች ሕብረት ተገልለው በሮሙ ቀላውድዮስ የተባረሩ ነበሩ። በዚያን ዘመን አይሁዶች በሮማውያን ባለሥልጣኖች ድንፋታ ይታረዱ ነበር። በተለይ በክርስቶስ በሚያምኑ ክርስቲያኖች ላይ የሮማን መንግሥት ያስተላለፈው ማስጠንቀቂያ ስለነበረ አይሁዶች ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው ለመቀበል እጅግ ይፈራሉ። ስለዚህ አቂላና ጵርስቅላ ጳውሎስ ወደ ሮም የመሄድ ፍላጐት እንዳደረበት ባወቁ ጊዜ የበለጠ ስለሮም ብዙ ሁኔታዎችን ስላስረዱት ነገሩ በመጠኑ ፍላጐቱን አሸብርበታል። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ስለ አገልግሎቱ ብዙ ሰምሮለታል። በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ ለሥራው ታላቅ እንቅፋት የፈጠረበት ነገር ቢኖር ግዝረትን የሚመለከተው ጉዳይ ነበረ። በዚህ ምክንያት የጳውሎስ

መንፈስ በኃዘንና በድንጋጤ ግራ ተጋብቶ ነበር። ከሁሉ ይበልጥ የጳውሎስ ልብ የከበደው አይሁዶች እግዚአብሔር በሰጣቸው እውነት ላይ ልባቸውን አደንድነው የነቀፉ ቃል መሰንዘራቸው ነበር። ቢሆንም እግዚአብሔር በታላቅ ምህረቱ በራዕይ ስላበረታታው አገልግሎቱን ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል በቆሮንቶስ እንዲቀጥል አድርጉታል። በዚህንም ጊዜ ቀደም ብሎ አዘጋጅቶት የነበረውን ሁለቱን የተሰሎንቄ መልዕክቶች ጽፏል። በመጨረሻም ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ከሚፈፀሙት በዓላት በአንደኛው ለመገኘት እግረ መንገዱን በኤፌሶን አልፎ ለመሄድ ይዘጋጃል። ወደ ኤፌሶንም ተመልሶ ለመምጣት ተስፋ በማድረግ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም ይቀጥላል። ኢየሩሳሌምንም ከጐበኘ በኋላ ወደ አንጾኪያ ይመለሳል። በዚህ ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ ታላቁንና ሁለተኛውን የወንጌል አገልግሎት ጉዞውን ይጨርሳል።

# ክፍል 6

# ሦስተኛው የሐዋርያው ጳውሎስ

## የወንጌል አገልግሎት ጉዞ

ባልደረቦቹ፦ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ፣ ሱሲጳጥሮስ፣ አርስጥሮኮስ፣ ሲኮንዶስ፣ ጋይዮስ፣ ቲኪቆስ፣ ጥሮፊሞስና ሉቃስ ናቸው።

## በኤፌሶን

በሦስተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ ላይ በኤፌሶን ብዙ ቆየ። ካሁን ቀደም ጢሞቴዎስ የሥራ ባልደረባው ሆኖ ለወንጌል አገልግሎት አብሮት ከመጣ ወዲህ በፍርግያና በገላትያ ይህንኑ የመሰለ ጊዜ ቆይቶ ነበር። በእነዚህ ጉዞዎች ውስጥ ሐዋርያው የበለጠ ትኩረት የሰጠውና ዋነኛ ስፍራ ያደረገው ኤፌሶንን ነበር። ወደዚህ ስፍራ ሲመጣ ቀደም ሲል መንገዱ የአሌክሳንደሪያ አይሁድ በነበረው ሰው በአጵሎስ ስብከት ተዘጋጅቶለት ነበር። ይህም ሰው በመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት ወደ ጌታ የተመለሰ ሲሆን በቃሉም በደንብ ተኮትኩቶ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ ሰው ነበር። ኤፌሶን የምትገኘው ካይስተር ከተባለችው ዋነኛዋ ከተማ መግቢያ ላይ ነው። ይህች ካይስተር የተባለችው ከተማ ድሮ እስያ በተባለው ስም ብቻ ተወስና ትኖር ነበረ። የከተማዋም ነዋሪዎች ግማሽ ከግሪክ ግማሽ ከእስያውያን የተከለሱ በመሆናቸው ባሕላቸውና ሃይማኖታቸውም ከምዕራባውያንና ከስሜናውያን የተከላለሰ ነበረ። አስማት ከምስራቃውያን የተወረሰ ልማድ እንደመሆኑ መጠን በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነበረ። ዲያና የተባለችው ጣዖት ቅድመ አማልክትነቷ የእስያውያን ነበረች። እንደዚሁም ሁሉ የባቢሎናውያን አማልክትና የግሪኳ አርጤሚስ ይመለኩ የነበሩ ግዑዝ የሆኑ ቁሶች ብቻ ነበሩ። የአምልኮው ሥርዓት የሩቅ ምስራቅ አገሮችን ባህልና ሥርዓትን የያዘ ነበር። እርሱም ልክ በቆሮንቶስ በሚገኘው በአፍሮዲጡስ ቤተ መቅደስ እንደሚፈጸመው ሥርዓት የአረማውያንን

እምላለክ የሚመስል ነበረ። በኤፌሶን ያለችው የዲያና ወይም የአርጤሚስ ቤተ መቅደስ በዓለም ሁሉ የታወቀ ነበረ። ቤተ መቅደሱ ከተሠራ 220 ዓመቱ ነበረ። የመቅደሱም ጣሪያ በ126 ማዕዘናች የተደገፈ ነበረ። ከፍታውም 20 ሜትር ያህል የሚረዝም ሲሆን በጠቅላላው ቤተ መቅደሱ የተሠራው በብዙ ነገሥታት መዋጮ ነበር። የዲያና ሐውልት ከሰማይ እንደወረደ ሆኖ ይታመንበታል። የሚገርመው ግን ከእንጨት የተቀረፀ መሆኑ ነው። ያም ሆነ ይህ የዲያና ሐውልት በአካባቢው ከሚታየው ውበት ጋር ሲነጻጸር እጅግ አስቀያሚና ማስፈራሪያ የመሰለ ነው። ኤፌሶን ከእንድልቃቂዋና ከዘማዊነትዋ በቀር በጣዖት አምላኪነትዋ በዓለም ዙሪያ የታወቀች ነበረች።

## ሁካታና መለየት

ይህች ዘመናዊ አገር ካጌጠችባቸው ብዙ የከበሩ ነገሮች መካከል በጣም የተከበረውና ታላቅ መታሰቢያነት ያለው ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያናች በውስጧ መታነጻቸው ነው፤ ራዕይ 2፡2-3። ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የጻፈውን መልዕክት የሚያክል እጅግ ብሩህ፥ ደስ የሚያሰኝና የሚያረካ አልነበረም። ብዙ አስማተኞችና ሟርተኞች እንኳን ሳይቀሩ የጥንቆላ መጻሕፍታቸውን እያቃጠሉ በክርስቶስ በማመን ወደ ደኅንነት ይመጡ ነበር። ይህም የሚያሳየው በፍፁም ልባቸው ንስሐ እንደገቡ ነው። የመጽሐፍቱ ዋጋ በገንዘብ ሲተመን 10 000 ብር የሚያወጣ ነበረ። ጣዖቶቻቸውንና አማልክታቸውን እየጣሉ ወደ ክርስትና እምነት የሚመጡ ሰዎች መጠን እጅግ ብዙ በመሆኑ በጊዜው በብር አንጥረኞች በዲያና መልክ የሚሠራው ጣዖት ዋጋ አጣ። ስለዚህ ብር አንጥረኞቹ የዕለት ምግባቸውን የሚያገኙበት ጥቅም ስለቀረባቸው በጳውሎስና በባልደረቦቹ ላይ ሕዝቡን አስተባብረው አመፅ አስነሱባቸው። ጳውሎስና ባልደረቦቹም ሁካታው እስኪበርድ ድረስ ወደ አንድ ስፍራ ተሰውረው በመቀመጥ ከአደጋው ሊተርፉ ችለዋል። ቢሆንም ወደፊት ሥራቸውን እንዳይቀጥሉ የማያመች ሁኔታ ስለ ተፈጠረ በኤፌሶን መቆየት አልቻሉም። ስለዚህ ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ተሰነባብቶ የሚቄዶንያን ቤተ ክርስቲያን ለመጐብኘት ወደ ሜቅዶንያ ሄደ። ሐዋርያው ጳውሎስ የመጀመሪያውን የቆሮንቶስ መልዕክት የላከው ከኤፌሶን እንደሆነ ይመሰላል፤ 1ኛ ቆሮ.16፡8።

## በጢሮአዳ በመቄዶንያና በቆሮንቶስ

ጳውሎስ ኤፌሶንን ከለቀቀ በኋላ በመጀመሪያ ወደ ጢሮአዳ ሄደ። በዚያም በአገልግሎቱ ጥሩ ውጤት ካገኘ በኋላ በሰሜን ግሪክ ወደምትገኘው ወደ መቄዶንያ አለፈ። ከዚያም በፊልጵስዩስ ሳለ ሁለተኛይቱን የቆሮንቶስን መልዕክት ጻፈ። በዚህን ጊዜ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ በክርስቶስ ላሉት ድሃዎች መረጃ ገንዘብ ከአሕዛብ ወንድሞቻቸው በትጋት ይሰበስብ ነበር። ይኸውም አይሁድ ክርስቲያናች ከአሕዛብ የሆኑት ክርስቲያናች ካለመገረዛቸው የተነሳ በእነርሱ ላይ ያላቸውን ጥላቻ እንዲተዉና ልባቸውን ለማለስለስ ሳይሆን አይቀርም። ከዚህም በስተቀር አይሁድ ክርስቲያናች ከአሕዛብ የሆኑት ክርስቲያናች ምን ያህል እንደሚራሩላቸው እንዲገነዘቡም ጭምር ነው። በኋላም ጳውሎስ ቲቶ በዚህ በገንዘብ አሰባሰብ ተግባር ላይ ሰዎቹን እንዲያነቃቃ ወደ ቆሮንቶስ ላከው። ከዚህ በኋላ የአይሁድ አስተማሪዎች በገላትያ የሚገኙትን አማኞች ትምህርት ይገለብጡና አማኞቹን መልሰው በስህተት ትምህርት

ይበክሉአቸዋል። በዚህን ጊዜ ጳውሎስ ኃይለ ቃል በተሞላው መልዕክት የገላትያ አማኞች ከስሕተታቸው እንዲመለሱ ይማጸናቸዋል። ከዚያም ጳውሎስ በቆሮንቶስ ባሳለፈው ሦስት ወር ውስጥ የሮሜ መልዕክቱን ይጽፋል። በሮም የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን በየትኛው ሐዋርያ ወይም መንፈሳዊ ሰው እንደተቆረቆረች አለመነገሩ እጅግ የሚደንቅ ነው። ምናልባት ይህች ቤተ ክርስቲያን የተጀመረችው በአንዳንድ ከሮም ምኩራቦች በወጡ አይሁድ ክርስቲያኖች ወይም ከሌላ አገር ወደ ሮም በመጡ በአንዳንድ አማኞች በስውር ልትሆን ትችላለች። ጳውሎስም ወደ ሜቄዶንያ ተመልሶ ከዚያም ወደ ጢሮአዳ በመርከብ ተሳፍሮ ሄደ።

## የኢየሩሳሌሙ ጉዞና የተደረገላቸው አቀባበል

ሐዋርያው ጳውሎስ ከጢሮአዳ በቀጥታ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለ። ጉዞውም በባሕር ላይ ሲሆን ጉዞው በጣም ደስ የሚል ዓይነት ነበረ።

ከዚህ በፊት ግን በጢሮአዳ የአንድ ሳምንት ምክር ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር አደረገ። ከዚያም ጳውሎስና የሥራ ባልደረቦቹ በመርከብ ሆነው ወደ ጢሮስ ተጉዘዋል። ይህች የጢሮስ ቤተ ክርስቲያን በእስጢፋኖስ ዘመን ከነበረው የመከራ ዘመን አንስታ እስካሁን ድረስ በታማኝነት ትኖር ነበር። በቤተ ክርስቲያኒትዋ ውስጥ ታማኝ የሆኑ አማኞች ብቻ ሳይሆኑ ነቢያትም ነበሩባት። ከዚያም ወንድሞችን ተሰነባብተው ወደ ቂሳርያ ተጓዙ። ከዚያም ከዚህ ስፍራ ትይዩ ወደሚገኘው አካባቢ በደረሱ ጊዜ ወንጌላዊው ፊልጶስና የቀሩት አገልጋዮች ከአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች በደረሰባቸው ተፅዕኖና ፈተና ዝለውና ተክዘው ያገኙአቸዋል። ቢሆንም ጳውሎስ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመሆን በአሕዛብ መካከል ስለሚፈፅመው ድንቅና ተአምራት በመመስከር መንፈሳቸውን አነቃቅቶ እግዚአብሔርን አብረውት እንዲያመሰግኑ አድርጓቸዋል።

# ክፍል 7

# የጳውሎስ ሕይወት ፍጻሜ

## በኢየሩሳሌም ታስሮ ወደ ቂሣርያ ተላከ

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ በዝርዝር ሳይሆን በአጠቃላይ የተፈፀሙትን ነገሮች ብቻ እናትታለን። ጳውሎስ በኢየሩሳሌም በነበረበት ወቅት ወደ አይሁድ ቤተ መቅደስ ገብቶ ስለነበረ ቤተ መቅደሳችንን አርክሷል በማባል በአይሁድ ጉባዔ እንደ ጨርቅ ተበጣጥሶ ከመሞት እግዚአብሔር ታድጉታል። በተለይ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በክርስቲያኖች ላይ ታላቅ ጥላቻ ስለነበራቸው ጳውሎስን ለማስገደል እንደተራበ አንበሳ አሰፍስፈው ነበር። በተለይ ጳውሎስን ከቤተ መቅደሱ ጐትተው ባወጡት ጊዜ በላዩ ላይ እንደ ንብ ተረባርበው ጐሳስመውት ነበር። ሆኖም ለሞት ሳይዳርጉት በፊት የሮማን ወታደሮች ጉባዔውን በመበተን

የሞት ሞታቸውን ከእጃቸው መንጥቀው አትርፈውታል። በኋላም ሮማውያን የሁከቱን መንስኤ አጣርተው የሃይማኖት መሪዎቹን ለማስደሰት ሊገርፉት ሲወስኑ ጳውሎስ የሮሜ ተወላጅ መሆኑን አስታውቆ ከመገረፍ ይድናል። ከዚያም ከእግዚአብሔር ዘንድ በተቀበለው ራዕይ እንደማይሞትና ገና ወደፊት በቂሣርያ ፊት እንደሚመሰክርለት ይነገረዋል። ከዚያም በሌሊት በብዙ የሮም ወታደሮች ታጅቦ ወደ ቂሣርያ ይሸኛል።

## በመንገድ ላይ የተፈፀመው ትዕይንት

ጳውሎስ ያለፈባቸው ሁኔታዎች የአንድን ክርስቲያን እምነትና ድፍረት ለማጠናከርና ለማበረታታት በቂዎች ናቸው። ጳውሎስ በእኩለ ሌሊት ተነስቶ በአጀብ ጉዞውን በጀመረበት ወቅት በቤትሖሮን አቋርጦ ሲያልፍ የአካባቢው ሁኔታ በጨለማው ምክንያት ባይታየውም ቀድሞ ስፍራውን ስለሚያውቀው በአዕምሮው ስዕል በታውን ሳይመለከት አልቀረም። ከዚያም ጥቂት እልፍ እንዳለ በጨረቃ ብርሃን ዕርዳታ ከሺህ አምስት መቶ ዓመት በፊት ኢያሱ ከጠላት ጋር ባደረገው ጦርነት ድል ያደረገበትን የኤሎንን ሸለቆ ሕቅ አመልክቷል። እርሱም በዚህ ሁኔታ ወደተወሰነለት ስፍራ እየገሠገሰ ሳለ ድንገት በስተጀርባው በኩል ከሚገኘው ከበረዶአማው የአርሞንኤም ተራራ የፀሐይ ብርሃን ውጋጋንዋ አሳየች። በዚህን ጊዜ ጳውሎስ በሳሮን ሜዳ አካባቢ ደርሶ ነበር። እርሱም በሳሮን ሸለቆ አካባቢ በግራ ቀኙ በኩል ከሚታዩ የአበባዎች መዓዛና ውበት ሲመለከት ሰለሞን በክብሩ ከእነዚህ እንዳንዱ አለበሰም የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ትዝ አለው። ስለዚህ እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ ታማኝ ስለሆነ አሁንም ከእኔ ጋር ነው በሚል መለኮታዊ ቃል ተጽናና። ከዚያም በቀኑ እኩሌታ ላይ በሰባዎቹ ወታደሮች ታጅቦ በዮሊየስ ቂሣር ሐውልት አካባቢ አልፎ ወደ አማረችው አዲስዋ ዋና ከተማ ደረሱ። ከዚያም ወታደሮቹ በትልቁ ካንፓቸው አጠገብ በድካም ከዛሉት ፈረሶቻቸው ላይ ወርደው አረገፉቸው። እነሆ ጳውሎስ በዚህ ሁኔታ ወደ ቂሣርያ ተመልሷል።

## ፊልክስ፥ ፊስጦስ፥ አግሪጳ - ወደ ቂሣርያ ይግባኝ

በዚህን ጊዜ በቂሣርያ የሮም መንግሥት አገረ ገዢ ሆኖ ያስተዳድር የነበረው ቀላውዲዎስ ፊልክስ ነበረ። እርሱም ለሥጋዊ ጥቅም የሚኖር እንጂ ፍትህ የተሞላ አሠራር አያከናውንም ነበር። ሚስቱም የሄሮድስ አግሪጳ ልጅ ድሩሲላ ትባላለች። በመጀመሪያ ጊዜ ጳውሎስ በፊልክስ ፊት ሲቀርብ ጉዳዩ ተጣርቶ እንደገና እንደሚቀርብ ተነገረው። በሁለተኛው ጊዜ ግን ፊልክስ ጳውሎስን ሲያስጠራው ሚስቱ ድሩሲላ አብራው ነበረች። ጳውሎስም በንግግሩ ውስጥ የዘለዓለም ፍርድንና ኩነኔን በሚመለከት ስለጠቀሰ ፊልክስና ሚስቱ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ። ጳውሎስም ከዚያ ወዲህ ያለ አንዳች ጥያቄ ለሁለት ዓመት በእስር ቤት ታስሮ ቆየ። ከዚህ በኋላ ፊልክስ ወደ ኢየሩሳሌም ተጠርቶ በምትኩ ፊስጦስ አገረ ገዢ ሆኖ ተሾመ። በዚህን ጊዜ ጳውሎስ ታስሮ ወደ ፍርድ ችሎት በቀረበ ጊዜ ወደ ቂሣር ይግባኝ አለ። በዚህ መሀል ንጉሥ አግሪጳና እህቱ በርኒቄ ፊልክስን ሰላም ለማለት ወደ ቂሣርያ መጡ። በዚህን ጊዜ የታሰሩበትን ምክንያትና እግዚአብሔር ስለገለፀለት ነገር እንዲናገር በንጉሥ አግሪጳ ፊት ጳውሎስ ተጠርቶ መጣ። በዚያም እንደቀረበ በተሰጠው በፀጋ ቃል በመንፈስ እየተቃጠለ ይናገር ስለነበረ በጠቅላላው ሁኔታ ንጉሥ አግሪጳን ወደ ክርስትና እምነት ሊያዘነብለው

ይደርሳል። ከዚህ በኋላ በይግባኙ መሠረት ጳውሎስ ጁሊየስ በተባለው መቶ አለቃ ኃላፊነት በመርከብ ሆኖ ጉዞውን ወደ ሮም ይቀጥላል።

## ወደ ሮም የተደረገው ጉዞና የመርከቡ መሰበር

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 27 ላይ የተገለፀው የጳውሎስን ጉዞ የሚመለከተው ታሪክ እጅግ አስደናቂና አስገራሚ ነው። በታሪኩ ውስጥ እንደምንመለከተው በጉዞው ላይ የነበሩት ተሳፋሪዎች ገሚሱ በመርከቡ የሚታመኑ ሲሆኑ ገሚሱ ደግሞ በመርከቡ ነጂና በችሎታው የሚታመኑ ነበሩ። ሆኖም በጉዞአቸው ላይ የሚፈፀመውን ተአምራት የሚመራው እግዚአብሔር ብቻ ነበረ። መርከቡ ወደቡን እስኪለቅ ድረስ ኃላፊነቱን ወስዶ ነገሩን ሁሉ ያቀነባብር የነበረው በቂሣርያ የነበረው ሄሮድስ ነበረ። ከዚያም መርከብዋ ከቂሳርያ ተነስታ በሲዶና ዳርቻ አድርጋ ወደ ሰሜናዊው ቆጵሮስ አለፈች። ከዚያም በኪልቅያና በጵንፍልያ ባሕረ ሰላጤ መካከል አልፋ ሐዋርያው የአባቶቹ አገር ከዓይኖቹ እስኪሰወር ድረስ ይዛው ነጐደች። ከዚያም በሉቅያ ወዳለችው ወደ ሙራ በደረሱ ጊዜ ቀጥታ ወደ ሮም ወደሚጓዘው ሌላ መርከብ እስረኞቹ ሁሉ ተዘዋወሩ። ብዙ ቀንም እያዘገሙ ከሄዱ በኋላ በድንገት ነፋስ ተነስቶ አቅጣጫቸውን ለማስለወጥ ይገፋቸው ጀመር። ሆኖም በቀርጤስ ተተግነው በጭንቅ በሰልሙና አንጻር ጥግ ጥጉን አልፈው መልካም ወደምትባለው ስፍራ መጡ። እነርሱም በዚያ ለረጅም ጊዜ አርፈው ትንፋሻቸው ከተመለሰ በኋላ መርከቡን ለቀው ጉዞአቸውን ጀመሩ። ከዚያ ብዙ አለፍ ሳይሉ በፊት አውራቂስ የሚሉት አውሎ ነፋስ ስለወረደባቸው መርከብዋን ሊገቱ ስላልቻሉና ከቁጥጥራቸው ውጭ ስለሆነች ለቀዋት ተጓዙ። ከዚያም አቅጣጫዋን በመለወጥ በነፋሉ እየተነዳች ወደ ምዕራብ ኸው ብላ ነጐደች። በዚህ ግፊት ውስጥ መርከብዋ እየተሽከረከረች ትበር ነበር። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለሁለት ሳምንት ተሳፋሪዎቹ ብዙ ጭንቅና መከራ ከደረሰባቸው በኋላ አንድ ቀን ምሽት መርከቢቱ መሬት ወዳለበት አካባቢ ደረሰች። መርከቢቱም ወዲያውኑ መልሕቅዋን ወደታች ጥላ እስኪነጋ ድረስ በተጠንቀቅ ቆመች። በኋላም በሩቅ ወደምትታየው ደሴት ለመድረስ ባደረጉት ጉዞ ይበልጥ እየቀረቡ ሲመጡ መርከቢቱ በነፋስ በኃይል ተወርውራ ሁለት ባሕሮች በሚገናኙበት ስፍራ ላይ በአፍንጫዋ ተተከላ ቆመች። በዚህን ጊዜ የባሕሩ ግፊት መርከብዋን ይሰባብራት ስለነበር እስረኞቹ ምግሻቸው በዋና ግማሾቹ ደግሞ በመርከቢቱ ስባሪ ላይ ሆነው በደህና ወደ ምድር ተሻገሩ።

## ጳውሎስ ያሳየው ጠባይ

በዚህ አስፈሪ በሆነ የመርከብ ላይ ጉዞ ጳውሎስ በምንም ሳይናወጥና መንፈሱ ሳይረበሽ በተረጋጋ ሁኔታ ላይ ይገኝ ነበረ። ይህ በመሆኑ አብረውት የነበሩትን መንገደኞች ተስፋ በተሞላ ቃል በእግዚአብሔር ተደግፎ ያጽናናቸውና ያበረታታቸው ነበር። ቀደም ሲል በመጀመሪያ ጊዜ ተነስቶ በነበረው ማዕበል ምክንያት ተሳፋሪዎቹ በተናወጡ ጊዜ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ በህልሙ አብረውት ካሉት መካከል አንዳችም ነፍስ እንደማትጠፋ ስለነገረው ልባቸውን ያጽናናው ነበር። በጉዞአቸው መጨረሻ ላይ ወደተገኘችው ደሴት ከመቃረባቸው አስቀድሞ በነበረው ጭንቀት ውስጥም በሕዝቡ መካከል ተነስቶ እግዚአብሔር የተናገረውን እንደሚፈፅምለት ከተናገረ በኋላ አሁንም ደስ ሊላቸው እንደሚገባ

አፅናንቶ ምግብ እንዲመገቡ ይጋብዛቸዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ካሁን አሁን ሞትን እያሉ ኑፍሳቸው ምንጥቅ ትል ስለነበረ ምግብ ከበሉ አሥራ አራት ቀን ሆኖአቸው ነበር። ስለዚህ የመርከብ ውስጥ ጓደኞቹ በሚናገረው ቃል ከመሳባቸው በቀር እግዚአብሔር ሀሳቡን ሲያሟላለት በመመልከታቸው ልባቸው በተመስጦ ይሞላ ነበር። ከዚህ በቀር ሐዋርያው በዚያ ጭንቀት ውስጥ መንፈሱ የተረጋጋ መሆኑ ከአምላኩ ጋር በነበረው የቅርብ ሕብረት ምክንያት እንደሆነ ሊረዱ ችለዋል።

## መላጥያና ፑቲዩሎስ

መርከብ የወደቀባት ደሴት መላጢያ ትባላለች። መርከቡ የተሰበረበት የባሕሩ አካባቢ እስካሁን ድረስ በቅዱስ ጳውሎስ ስም ተሰይሞ እየተጠራ ነው። የምድሪቱ ነዋሪዎችም ቅድመ ዜግነታቸው ፊንቄአውያን የነበሩ ናቸው። ጳውሎስና የቀሩት ባልደረቦቹ በእነርሱ መካከል ሦስት ወር ከቆዩ በኋላ በሌላ መርከብ ተሳፍረው ሁለተኛ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ከዚያም በስራኩስ ሲያልፉ በዚያ ሦስት ቀን ተቀመጡ። ከዚያም አልፈው እየተዘዋወሩ ወደ ሬጊዩም ደረሱ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ መንገዳቸውን እየተጓዙ ሳለ ከአንድ ቀን በኋላ የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ በነፋሱ እየተገፉ በሁለተኛው ቀን ወደ ፑቲዩሎስ መጡ።

## የሮም ውበትና መልክ

ከዚህ ፑቲዮሉስ ከተባለው የባሕር ወደብ እስከ ሮም ከተማ ድረስ 240 ኪሎ ሜትር ይርቃል። ሐዋርያው ይህን ሁሉ መንገድ ተጉዞ እስከ ሮም ከተማ ድረስ የደረሰው በመሬት ላይ ጉዞ ነበረ። በዚህ የመሬት ላይ ጉዞ ጳውሎስ እግረ መንገዱን ብዙ ታሪካዊ ቦታዎችን ተመልክቷል። በተለይ እከተማው ለመድረስ 80 ኪሎ ሜትር ሲቀረው ፑቲዩሎስ በደረሰ ጊዜ በሮም የሚገኙ ወንድሞች መጥተው በታላቅ አክብሮትና ፍቅር ልባዊ ሰላምታቸውን አቅርበውለታል። ከዚያም ተጉዞ ሮም ከተማ ለመግባት 16 ኪሎ ሜትር ያህል ሲቀረው የንጉሡ ዋና ከተማ በሩቅ መታየት ጀመረች። ከዚህ ቀጥሎ ወደ ሮም ዋና ጐዳና ገባ። ወደ ከተማው እየቀረበ በመጣ ቁጥር በግራና ቀኝ እንዲሁም በፊለፊቱ ቤተ መቅደሶች፥ ቤተ መንግሥት፥ ድልድዮች፥ የቲያትር ቤቶችና ረጃጅም የድንጋይ ሐውልቶች ይታዩ ጀመር። ጳውሎስ በዚህን ጊዜ የልቡ ምኞት ተፈፀመ። በእነዚህ ሰባቱ ተራራማ አገር የኢየሱስን የማዳን ወንጌል እንዲና ለመጨረሻ ለማስተጋባት የጌታ መንፈስ ልቡን ያነሳሳው ጀመር።

## ሮም የምትገኝበት ሁኔታ

እንደዚህች ከተማ የወንጌሉ የመለወጥ መልዕክት አብዝቶ የሚያስፈልግበት ስፍራ አልነበረም። አገሪትዋ በጠቅላላ ስነ ምግባር በጐደለው በፍትወትና በእርከስና ሁሉ የተበከለች በመሆንዋ ብልግናዋ መጨረሻው ከፍታ ላይ ደርሶ ነበር። ሌብነት ውንብድናና የመሳሰሉት ነገሮች በግልጽ ባደባባይ እየተከናወኑ ናቸው። በወቅቱ የአገሪትዋ ንጉሥ የነበረው ኔሮ ገና በሃያ አራት ዓመት ዕድሜው የግፉና የአመፁ መጀመሪያ አድርጐ እጁን የታጠበው በእናቱና በሚስቱ ደም ነበረ። እርሱም በቁባቶቹ አነሳሽነት ዝናና ክብር ያገኙ መስሎት ባልተገራና

በአውሬነት ባሕርዩ ብዙ አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን እያሳደደ ያስጨፈጭፍ ነበረ። ነጻ የከተማ ነዋሪዎቹ ቁጥር ከሚሊዮን በላይ ሲሆን የባሪያዎቻቸውም ቁጥር ከዚህ አያንስም ነበር።

## የወንጌል አገልግሎት

ጳውሎስ በመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን የሰበከው የሮም ነዋሪዎች ለነበሩ አይሁዶች ነበር። ሆኖም አይሁዶቹ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ወጋቸውን ስለመረጡ አላስሙትም። ከዚህ በኋላ ግን ብዙ ፍሬዎች ሊያገኝባቸው ወደቻለው ወደ አሕዛብ ዘወር አለ። ጳውሎስ በሮም በነበረበት ወቅት ሁሉ የሮማውያን እስረኛ ሆኖ በሮም ወታደሮች በሰንሰለት ታስሮ ራሱ በተከራያት በትንሽ ቪጋባ ውስጥ ይኖር ነበር። ይጠብቁት ከነበሩ ወታደሮች መካከልም አንዳንዶቹ ክርስቶስን ተቀብለው ተለውጠዋል። እነርሱም ወደ ክርስቶስ የተመለሱት ከእርሱ ጋር በመነታረክ ሳይሆን እምነተ ፅኑና ካመነው ነገር የማይዛነፍ እውነተኛና አፍቃሪ በሆነ ባህሪይው ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። በሐዋርያው አገልግሎት በዚህ በቅርቡ የነበሩት ወታደሮች ቀርቶ በኔሮ ቤተ መንግሥት የሚገኙት እንኳን ተለውጠው ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ሮም ከገባ ከሁለት ዓመት ወዲህ ብዙ ሰዎች አማኞች እንደሆኑና ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች እንደተመሠረቱ ዋናው ማስረጃ ኔሮ ያስገደላቸው የምዕምናን ብዛት እጅግ ብዙ የመሆኑ ነገር ነው። በእነዚያ ሁለት ዓመቶች ውስጥም ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልሞናን፥ የቆላስይስን፥ የኤፌሶንንና የፊልጵስዩስን መልዕክቶቹን ጽፏል።

## ምርመራና ነፃ መሆን

በመጨረሻም ጳውሎስ ለምርመራ ቀረበ። ምናልባት ይህ ምርመራ የተካሄደው በኔሮ ፊት ይሆን ይሆናል። ሉቃስ የጳውሎስ ጉዳይ ምን እንደደረሰ ሳይናገር በፊት ታሪኩን ይዘጋል። ቢሆንም ከቀሩት ከሐዋርያው መልዕክቶች በምናገኘው ፍንጭ መሠረት ጉዳዩ ተመርምሮ ነፃ የወጣ ይመስላል።

## ወደ እስጳንያ የተደረገ ጉዞ

ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ከሮም ወደ እስያ ከዚያም ወደ ሜቄዶንያ እንደ ሄደ ይታመናል። ሁለት ዓመት በዚያ ለማሳለፍ ወደ እስጳንያ የሄደው ምናልባት ከዚህ በኋላ ይሆናል! ሮሜ 15፡28። ከዚያም ወደ ቀርጤስ ደርሶ ስለነበርና ብዙ ችግር ስለነበረባቸው አሳሳቢ በሆነ ስጋት ላይ ነበሩ። የውንጌልን እውነት በሚገለብጡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እየታመሱ ነበረ። የመጀመሪያውን የጢሞቴዎስን መልዕክትና ቲቶን የጻፈው በዚህን ወቅት እንደሆነ ይመስላል። እርሱም በዚህ መልዕክቱ በኤፌሶንና በቀርጤስ የሚገኙትን አማኞች በመምከርና በማጽናት የሐሰተኞቹን አስተማሪዎች ትምህርት የሚቋቋሙበትን መንገድና ዘዴ ነግሯቸዋል።

## ሁለተኛው እሥራት

ጳውሎስ ክረምቱን በሜቄዶንያ በምትገኘው በኒቆጵልዩን ለመክረም ተስፋ ያደርግ ነበር። ቢሆንም በዚያ እንዲቆይ አልተፈቀደለትም። በዚህ ሳለ ደግሞ እንደገና በአዲስ ክስ ተይዞ ወደ ሮም ከተወሰደ በኋላ ስለራሱ እንዲናገር ወደ ፍርድ ችሎት ቀርቧል። ይህ በሆነበት ወቅት ኔሮ ወራዳ በሆነ ሁኔታ ላይ ይገኝ ነበረ። እርሱም ሲቀናጣ የሮምን ከተማ በእሳት አያይዞ ግማሹ ያህል ከተማ ለስድስት ቀን ያህል ሳያቋርጥ እንዲጋይ አድርጓል። ሆኖም ራሱን ከወንጀሉ ነጻ ለማውጣት በዚህን ጊዜ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ በሆነ ክርስቲያኖች ላይ አሳኮባቸዋል። ከዚህ የተነሳ በጣም አሰቃቂ ስደትና ግድያ በክርስቲያኖች ላይ ተፈጽሞባቸዋል። አንዳንዶቹን ሰቅለዋቸዋል፤ አንዳንዶቹን እርጥብ የእንስሳ ቁርበት እያለበሱ ውሻ ይለቁባቸውና ከቁርበቱ ጋር እስኪሞቱ ድረስ በስቃይ ዘልዝለው ይገድሏቸው ነበር። አንዳንዶቹን ደግሞ በገመድ ጥፍር አድርገው ካሰሩዋቸው በኋላ በጢፍ በተነከረ ጨርቅ ይጠመጥሟቸውና ማታ ማታ ለኔሮ ቤተ መንግሥት ግቢ ብርሃን እንዲሰጡ በሰልፍ አቁመው በእሳት ይለኩሷቸው ነበረ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለቁት የክርስቲያኖች ብዛት እጅግ ብዙ ነበረ።

## ሁለተኛው ምርመራ - ፍርድና ግድያ

ጳውሎስ ሁለተኛ ጊዜ ሲታሰር እንደ በፊቱ ከሌሎች እስረኞች ጋር ሆኖ የመመስከር ዕድል ያገኘ አይመስልም። ቢሆንም ሁለተኛውን የጢሞቴዎስን መልዕክት ጠንቅቆ ለመጻፍ የቻለው በዚህን ጊዜ ነበረ። በዚህ በሁለተኛው እስራቱ ጊዜ ለምርመራ ወደ ፍርድ ሲቀርብ በድፍረት የማዳኑን ወንጌል ተናገረ። በሁለተኛው ጢሞቴዎስ መልዕክቱ ላይ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት መስዋዕት ሊሆን እንዳለ ተናግሯል። በዚህ በመጨረሻ ጊዜ ጳውሎስን ከኔሮ ውሳኔ ሊያድነው የቻለ መከላከያ አልነበረም። ስለዚህ ኔሮ በሰጠው የሞት ፍርድ መሠረት አንገቱ በሰይፍ ተቀንጥሶ ተገድሏል። ጳውሎስ በመልዕክቱ እንደጻፈው ሞት ድል በመንሳት እስከሚዋጥበት ዕለት ድረስ አስከሬኑ ባልታወቁ ውንድሞች በመካነ መቃብር ውስጥ አርፏል።

## የሥራ ባልደረቦቹ

የሐዋርያው ጳውሎስ የሥራ ባልደረቦች የአገልግሎት ሁኔታ ከዚህ በኋላ ብዙ የታወቀ ነገር የለም። ጢሞቴዎስ በሁለተኛው መልዕክቱ ላይ ጳውሎስ ወደ ሮም ተጠርቶ እንደ ነበር ገልጧል። ስለዚህ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ፈጥኖ መጥቶ ይሆናል። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ስለእርሱ ሕይወት ታሪክ በትክክል የምናውቀው ነገር የለም። አንድ ጊዜ ግን የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ እንደነበረ እናውቃለን፤ ዕብ. 13፥23። ባህላዊ በሆነ ታሪክ አንጻር ግን ደሚትየስ በተባለ ንጉሥ መከራ እንደተቀበለና በኋላም በሰይፍ ተሰውቶ እንደተገደለ ይነገራል። ቲቶ ግን በአንድ ቃል ወደ ድልማጥያ ሄዶ እንደነበር በሁለተኛው ጢሞቴዎስ 4፥10 ላይ ተነግሮናል። ቲቶ ወደ ድልማጥያ የሄደው በጳውሎስ ትዕዛዝ ይሆን በራሱ ፍላጐት እንደሆነ የምናውቀው ነገር የለም። ስልዋኖስ ግን በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥12 ላይ የዚያን ሐዋርያ መልዕክት ይዞ በእስያ አካባቢ ለተበተኑ ወገኖች ለማድረስ እንደተላከ ብቻ እናውቃለን።

ማርቆስ ግን እንደገና በጳውሎስ መታመንን ካገኘ በኋላ የሥራው ባልደረባ ሆኖ አብሮት ሲያገለግል ቆይቷል፤ ቆላ.4፡10። በኋላም ጢሞቴዎስ ወደ ሮም እንዲመጣ በላከበት ጊዜ ማርቆስንም አብሮት ይዞ እንዲመጣ ነግሮታል፤ 2ኛ ጢሞ.4፡11። በኋላም ማርቆስ ከጴጥሮስ ጋር በመሆን ጸሐፊውና የቃሉ ተርጓሚ ሆኖ አገልግሎታል። በመጨረሻም ማርቆስ ወደ እስክንድርያ ወርዶ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ካቋቋመ በኋላ በሰማዕትነት ሞቷል። ሉቃስ ጳውሎስ ከመገደሉ በፊት ቀደም ብሎ በሮም ተገኝቶ ነበር። እርሱም በመከራው ሐዋርያውን እያጽናና እያበረታታ የቆየ ታማኝ ወዳጅነቱን አረጋግጧል። ከዚህ በኋላ ሉቃስ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የቀረውን ዘመኑን እንዳሳለፈ የተጻፈ ነገር የለም። ባህላዊ የሆነው ታሪክ ግን እንደሚጠበቀው ሳይሆን የሕይወቱን ፍጻሜ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ይገልጸዋል። በአጠቃላይ አገላለጽ ጳውሎስ ከሞተ በኋላ የሥራ ባልደረቦቹ የሕይወት ፍጻሜ እውን በሆነ መንገድ በትክክል የታወቀ ነገር የለም።

# ክፍል 8

## የቀሩት ሐዋርያት አገልግሎት

### የዘብድዩስ ልጅ ያዕቆብ

ይህ ሐዋርያ ቀደም ሲል እንደተወሳው በመጀመሪያው በቤተ ክርስቲያን ዘመን በንጉሥ ሄሮድስ ተገድሏል፤ የሐዋ.12፡2።

### የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ

ይህ ሐዋርያ ሁሳቡን ባለመቀየርና የማያወላውል በመሆኑ በዓለም ታሪክ የታወቀ ነበረ። ከዚህ የተነሳ «ትክክለኛው ያዕቆብ» በመባል ይጠራ ነበር። የእርሱም የአገልግሎት ስፍራ በኢየሩሳሌምና በውስጧ ባሉት አካባቢዎች ነበረ። ብዙ ጊዜ የጌታ ወንድም ያዕቆብ ይሄኛው ይሆን ሌላኛው የሀሳብ መከፋፈል አለ። የመልዕክቱ መንፈስ የጌታን ፀጋ የሚያከፋፉ ሰዎች ስነ ምግባር የጉደላቸው እንደሆኑ በማስረዳት ላይ የተመረኮዘ ነው። በመጨረሻው የሕይወቱ ዘመን አካባቢ የፈሪሳውያን አስተሳሰብ ካላቸው የክርስቲያን ክፍል አማኞች ጋር የተመሳጠረ ይመስላል። ምክንያቱም ጳውሎስ በገላትያ መልዕክቱ ውስጥ ያወገዘውን ትምህርት መቋቋም አቅቶት ሊሆን ይችላል። ምናልባት ይህ ጥቂት ድክመት የታየበት ወደ መሞቻው ዘመን አካባቢ ላይ ሳይሆን አይቀርም። ያዕቆብ መሢህ ነው ብሎ የሚያስተምረውን ክርስቶስን አይሁዶች የፖለቲካ መሪ እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩት ነበር። ስለዚህ ሊቀ ካህኑ ሐናኒያ የሮም መንግሥት አገረ ገዢ የነበረው ፊስጦስ የአገልግሎቱን ዘመን ጨርሶ በምትኩ ወደ ኢየሩሳሌም በሚመጣው አገረ ገዢ ቅይይር ወቅት ያን ጊዜና ዕድል ተጠቅሞ ያዕቆብን በድንጋይ አስወግሮ አስገድሎታል።

# ጴጥሮስ

በዚሁ መጠን የጴጥሮስንም የመጨረሻ የሕይወት ዘመን አካባቢ ታሪክ መተረክ ያስቸግራል። በባህላዊው ታሪክ አነጋገር መሠረት ሐዋርያው ጴጥሮስ ጳውሎስ በሮም ጠበረበት ወቅት እርሱም ወደዚያም ሄዶ በኔሮ ፍርድ ከጳውሎስ ጋር ሞቷል ተብሎ ይነገራል። በአጠቃላይ ይህ ሀሳብ ጥንታዊ ታሪክነት ስላለው እስካሁን ድረስ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ ነው። ጴጥሮስ ኢየሩሳሌምን ለቆ በወጣበት ወቅት በጳርቴ በተለይም በሜጶፖታምያ አውራጃ ሳለ ወንጌልን በጳርቴኛ ቋንቋ ጽፎ እንደነበረ ብዙ አስተያየት ይሰጣል። በዚህን ስፍራ በዳንኤልና በሕዝቅኤል ዘመን ተወስደው የነበሩ የአይሁድ ዝርያ ቅሪታዎች ይኖሩ ነበረ። ስለዚህ ሐዋርያው ጴጥሮስ ወንጌልን ለማስተማር ጤናማና የተመቻቸ ሁኔታ አጋጥሞት ነበር። ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልዕክቱ ስለ ጥንታዊቱ የባቢሎን ከተማ በውስጧ ወይም በአካባቢዋ እንደ ኖረ ሰው ዓይነት ሆኖ ጽፏል፤ 1ኛ ጴጥ.5፡13። ጴጥሮስ የመጀመሪያይቱን መልዕክቱን በጳንጦስ፥ በገላትያ፥ በቀጳዶቅያ፥በእስያን በቢታንያ ለተበተኑ ወገኖች የጻፈው በዚህ ስፍራ አካባቢ ሆኖ ነው። ጴጥሮስ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት በግሉ ጐብኝቷቸው የማያውቅ ከሆነ ዝናቸውን የሥራ ባልደረባው ከሆነው ከሲልዋኖስ ሳይሰማ አልቀረም። ሲልዋኖስ በሮም በጳውሎስ ላይ ተነስቶ የነበረው የስደት ማዕበል በእስያም ተነስቶ በነበረበት ወቅት ከጴጥሮስ ጐን ሆኖ ይቋቋም የነበረ ሰው ነው። ስለዚህ ጴጥሮስ በእስያ ለሚገኙት ምዕምናን በመከራው ውስጥ ሳይዝሉ እስከ ፍጻሜ እምነታቸውን እንዲጠብቁ የማበረታቻ ቃል ይጽፍላቸዋል። በጥንት ባህላዊ ታሪክ የጴጥሮስ ባለቤት በእምነትዋ ምክንያት ሰማዕት ልትሆን በምትወሰድበት ወቅት ጴጥሮስ ድምፁን ከፍ አድርጐ ከጠራት በኋላ «ጽኚ! ጌታን አስቢ!» ብሏት እንደነበረ ይነገራል። ታዲያ ጴጥሮስ በዚሁ መከራ ውስጥ ሰማዕት እንደሆነ ባይካድም ባህላዊው ታሪክ እንደ ጌታ ሳይሆን ዘቅዝቃችሁ ግደሉኝ ብሎ ለገዳዮቹ ራሱን እንደ ሰጠ ይናገራል። ሐዋርያት እርስ በርሳቸው ሲማማሩም ሆነ ሌሎቹን ሲያስተምሩ በግፍ ፍርድ መከራ በሚቀበሉበት ጊዜ ፀጥ ብለው ችግራቸውን መቀጥ እንጂ ፍዳ የሚያደርሱባቸውን ሰዎች መለማመጥ እንደሌለባቸው ያስተምሩ ነበር።

# ቶማስ

እንደ አንዳንድ መግለጫዎች መሠረት ቶማስ ወንጌልን የሰበከው ከጳርቴ እንደነበረ ታውቋል። ይህ ጳርቴ የተባለው ክፍል ፋርስንና ሜሶጶጣሚያን አጠቃሎ የያዘ ነበረ። ቶማስ በዚህ አካባቢ የሚያገለግለው ጴጥሮስ ከሚያገለግልበት ለየት ባለ ስፍራ ሊሆን ይችላል። እርሱም በየቦታው የተበታተኑትን ወገኖች ወደ አፍጋኒስታየን ያሰባስብ ነበረ። አንዳንድ አፍጋኒስታየኖች ከአይሁድ ወገን የሆነ ዝርያ አለን እያሉ ይናገራሉ። ምናልባት ቶማስ የሕንዶች ሐዋርያ ሊያደርገው የሚያስችለውን አንዳንድ ባህሎች አጥንቶ ይሆናል ብለን እንገምታለን።

# እንድርያስ

ይህ ሐዋርያ አንዳንድ ጊዜ በጥቁር አባይ ዳርቻ በሚገኙ ኮንስታንቲኖፕል በተባሉ አገሮች ሁሉ ወንጌል ለመስበክ ይዘዋወር ነበር። እንድርያስ በዚህ አካባቢ ወንጌልን እንደሰበከ የጥንት ታሪክ ጸሐፊዎች በጽሑፋቸው አረጋግጠዋል። እርሱም በሕይወቱ መጨረሻ የተገደለው በስቅላት ሲሆን የተሰቀለበት እንጨት ቅርፅ ኀ የተባለውን የእንግሊዝኛ ፊደል የሚመስል ነበር ይባላል። ስለዚህ ይህ ዓይነቱ መስቀል እስከ ዛሬ ድረስ የቅዱስ እንድርያስ መስቀል ተብሎ ይጠራል። አሰቃቀሉ ነፍሱ ከመውጣትዋ በፊት በጣም የሚያሰቃየው ነበረ። እርሱም በዚህ ዓይነት አሰቃቀል በጅማት ተወጥሮ ስለታሰረ ነፍሱ ከመውጣትዋ በፊት ለሁለት ቀን ያህል ሳያቋርጥ ተሰቃይቶ ነበር። የጥንት ጸሐፊዎች በመዘገቡት መሠረት ከሐዋርያት መካከል በሰማዕትነት የሞቱት ሁለቱ ያዕቆቦች፣ ጴጥሮስና ጳውሎስ ናቸው።

# በርጠሎሜዎስ

በርጠሎሜዎስ ያገለገለው በሕንድ አካባቢ በሚገኙት አገሮች ነበረ ይባላል። ይኸውም ጥንት ወደ አይሁድነት ተለውጠው ለነበሩ በአረብ አገር ለሚኖሩ ለየመኖች እንደሆነ የጥንት ጸሐፊዎች መዝግበዋል። እነዚህ ወደ አይሁድነት የተለወጡ የመኖች መሐመድ ሊወለድ ጥቂት ዘመን ሊቀረው አካባቢ በስድስተኛው መቶ ዓመት ገደማ ክርስቲያኖችን ያሳድዱ እንደነበረ ጥንታዊ ጸሐፊዎች መዝግበዋል። ነገር ግን ባህላዊው አገላለጽ በርጠሎሜዎስ ወደ ፍርግያና አራራት አገር መጥቶ ከተገደለ በኋላ ሕይወት ዘርቶ እንደ በረረ ያወሳል።

# ፊልጶስ

ፊልጶስ ከመሞቱ በፊት በፍርግያ ያገለግል እንደነበረ ሪፖርት ደርሶናል። ነገር ግን ያሚሚቱ ነገር በጨረፍታ እንጂ በዝርዝር ስላልተገለጸ በዚህ ስፍራ መሞቱን በሪፖርት አቅራቢዎች እምነት በደፈናው ተቀብለነዋል።

# ማቴዎስ

ማቴዎስ በእስያ፣ ኢትዮጵያና በሜቄዶንያ አገልግሎት ይሰጥ እንደነበር ተነግሯል። የማቴዎስ ወንጌል በእስራኤል ለሚገኙት አይሁዶች አገልግሎት እንዲውል ተብሎ ከቀሩት ወንጌላት በፊት ቀደም ሲል የተጻፈ ነው።

# ስምዖን

ስምዖን እንዲያገለግልባቸው የተመደቡለት ስፍራዎች ግብፅ፣ ሦርያና ሞሪታኒያ እንዲሁም እንግሊዝ ነበሩ። እርሱም እንደቀሩት ሁሉ በዘመኑ መጨረሻ ላይ በእንግሊዝ

ተወላጆች ሰማዕት ሆኖ በመገደል ያልፋል። የአብዛኛዎቹ ሐዋርያት የሰማዕትነት ሞት ታሪክ የተገኘው እነርሱ ሞተው ብዙ ዘመናት ካለፉ በኋላ ነው። በዚያን ዘመን በነበሩ አንዳንድ ሰዎች አስተሳሰብና ግምት ከሐዋርያት መካከል በሰማዕትነት ያልሞተ ሰው ከተገኘ እንደ ቅዱስ አይቆጠርም ነበር።

## ይሁዳ

የይሁዳ ወይም የታዴዎስ የሕይወት ታሪክ በሜሶጶጣሚያ ውስጥ የምትገኘው የኢዴሲያ ገዢ ከሆነው አጉረስ ከተባለው ሰው ታሪክ ጋር የተጣመረ ነበር። የዚህ የኢዴሲያ አገር አስተዳዳሪ ሰው ስም በግሪክ አርፋ ወይም ዮርፋ ይባላል። በኋላም አርፋ ውሎ አድሮ በይሁዳ ምስክርነት ክርስቶስን ተቀብሎ ድኗል። ይህ ንጉሥ በዳዊት ዘር በኩል ከክርስቶስ ጋር ይዛመድ ስለነበረ ይህ በክርስቶስ በኩል ያለ የገዢነት መደብ አንድ ቀን አቆጥቁጦ ይነሳል የሚል ጉምጉምታ በአካባቢው ይሰማ ጀመር። በዚሁ አሳብ መሠረት የክርስቶስ ወንድም የይሁዳ ሁለት የልጅ ልጆች ለአስተዳዳሪነት ታጭተው ነበር። ነገር ግን ለዚህ ኃላፊነት የማይበቁ አልባሌ ሰዎች በመሆናቸው እንደታሰበው የገዢነቱን መደብ ሳይዙ ቀርተዋል።

## ማቲያስ

አንዳንድ ጸሐፊዎች በገለጹት መሠረት ለዚህ ሐዋርያ የተመደበለት የሥራ ቦታ ኢትዮጵያ ነበረ ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ቀጳዶቅያ ነበረ ይላሉ። አንድ ጥንታዊ ጸሐፊ ግን ማቲያስ ሴባስቶፓል በተባለበት አገር እንደሞተና መቃብሩም በፀሐይ ቤተ መቅደስ አጠገብ እንደነበረ ገልጿል።

## ዮሐንስ

በዚህን ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ የሐዋርያውን የዮሐንስን የሕይወት ታሪክ ብቻ ነው። ከቀሩት የሐዋርያት የሕይወት ታሪክ ይልቅ የዮሐንስ የሕይወት ታሪክ ከታመነ ምንጭ የተገኘ ስለሆነ የበለጠ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል። ሐዋርያው ዮሐንስ ኢየሩሳሌምን ለቆ የወጣው ጳውሎስ ኢየሩሳሌምን ከመጐብኘቱ ቀደም ሲል ነበረ። ሆኖም በዚያን ወቅት አገልግሎት ይሰጥ የነበረበትን ስፍራ በትክክል አናውቀውም። ሆኖም ጴጥሮስ የመጀመሪያውን መልዕክቱን የጻፈው በእስያ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን መከራን እየተቀበለች ስለነበረ ማጽናኛና ማበረታቻ እንዲሆናት ሲል ነበር። ዮሐንስም ይኸንኑ የማጽናናት ተግባር ለመፈጸም በመካከላቸው ሆኖ ያገለግል ነበረ። እርሱም እውነትን በሥልጣን እያሳወቀ በተለይ በኤፌሶን ለረጅም ዘመን ተቀምጦ እንደነበረ ታውቋል። በመጨረሻም ደሚትያን በተባለ ንጉሥ በፍጥሞ ደሴት ላይ ታስሮ ከቆየ በኋላ እንደገና ወደ ኤፌሶን ተመልሶ ዕድሜውን ጠግቦ በእርጅና ዘመኑ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

# ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት

ስለ ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት በተጻፈው ታሪክ ውስጥ የዮሐንስም ስም ተደጋግሞ ተጠቅሷል። ጌታ ኢየሱስም ከሰሙ ጋር የተያያዙ አጫጭር መልዕክቶችን እንዲጽፍ ዮሐንስን ለዚህ ተግባር ለይቶት ነበረ። ስለ እያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለመስጠት አንችልም። ቢሆንም አጫጭር መግለጫ ለመስጠት እንበዝንም።

1. ኤፌሶን፡- ይህች አብያተ ክርስቲያን በምን ሁኔታ ላይ ትገኝ እንደነበረና በመጀመሪያም የክርስትና ትምህርትን ያስተዋወቃት ጳውሎስ እንደነበረ ቀደም ሲል በተነጋገርነው ትምህርት ውስጥ ገልጸነዋል። በዚያን ዘመን የኤፌሶን ዋና ከተማ አይአኒያ ትባል ነበረ። ኤፌሶንም ዝነኛ የነበረችው በውስጥዋ ከነበረው ከዲያና ቤተ መቅደስ ውበት የተነሳ ሲሆን በፍልስፍናዋ፥ በአስማትዋና በጥንቆላዋም የታወቀች ነበረች። ይህች ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ላይ መልካምና ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ላይ ብትገኝም ውላ አድራ ግን ከነበረችበት ሁኔታ ወደ ኋላ ተንሸራትታለች። ስለዚህ ከዚህ ውድቀትዋ ተመልሳ ንስሐ ካልገባች መቅረዝዋ እንደሚወገድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷት ነበር። እርስዋም በማስጠንቀቂያው መሠረት ንስሐ ገብታ ሳልተመለሰች ልክ እንደተባለው ተፈጽሞባታል። አሁን በኤፌሶን ከተማ ከሚገኙት መንደሮች መካከል ከትንሽዋ የቁርኮች መንደር በስተቀር በጠቅላላው ምድረ በዳና ወና ሆኖ ፈራርሷል።
2. ሰምርኔስ፡- ሰምርኔስ የምትገኘው ከኤፌሶን ሰሜናዊ ክፍል 65 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝበት ስፍራ ላይ ነው። ይህች ቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት የነቀፋ ቃል አልደረሰባትም፤ ሆኖም ወደፊት የመከራ ቀን እንደሚደርስባት ተነግሯታል። እርስዋም የተነገራትን የመከራ ዘመን በትዕግሥት አሳልፋዋለች። በሰምርኔስ ከሚገኙት ምዕምናን መካከል ፓሊካርፕ የተባለው ሰው ስለ እምነቱ የሰጠው ምስክርነት ምን ጊዜም የማይረሳ ቁም ነገር ነው። እርሱም እስከ ሞት ድረስ በክርስቶስ የታመነ በመሆኑ የሕይወትን አክሊል ተቀብሏል። አምላኩና ጌታው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲሳደብ በጠላቶቹ በተጠየቀ ጊዜ «ሰማንያ ስድስት ዓመት አገልግዬዋለሁ፤ በዚህ ዘመን ውስጥ ሁሉ አንድ ጊዜ እንኳ በድሎኝ አያውቅም፤ ስለዚህ ይህንን አምላኬንና ንጉሤን እንዴት እሰድበዋለሁ?» ብሏል። ሰምርኔስ እስካሁን ድረስ 130000 ሕዝብ የሚኖርባት ሰፊ ከተማ ናት።
3. ጴርጋሞን፡- ጴርጋሞን ከሰምርኔስ ሰሜናዊ ክፍል 96 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝበት ስፍራ ላይ ናት። እርስዋም የጥንታዊው መንግሥት ዋና ከተማ ስትሆን በዘመኑ ስለነበሩ ንጉሣዊ ቤተሰቦች የሚተርኩ ከ200000 በላይ የሚሆኑ መጻሕፍትን የያዘ ዝነኛ ቤተ መጻሕፍት ነበራት። በዚሁ ስፍራ መለኮታዊ አምልኮ ይደረግለት የነበረ በእባብ መልክ የተሠራ ጣዖት ነበረ። ይህ ምስል በውስጣዊ መልኩ በዚህ ቦታ የሚፈጸመውን ርካሽ የሰይጣን አምልኮ በአንጻሩ ይገልጻል። ይኸውም «የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን ቦታ አውቃለሁ» የሚለውን ሀሳብ ይገልጻል። ይህ ቦታ በዚህ ዘመን የፍርስራሽ ክምር ቢሆንም በውስጡ 14000 ያላነሱ ሕዝቦች ይኖሩበታል።

4. ትያጥሮን፡- ትያጥሮን የምትገኘው በሊድያ ሰሜናዊ ድንበር ላይ ነው። በአሁኑ ጊዜ የሕዝብዋ ቁጥር በ6000ና በ7000 መካከል ይገኛል። የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን በፍቅርዋ፣በእምነቷ፣በአገልግሎቷና በትዕግሥቷ ዝናን ያተረፈች ብትሆንም በአሁኑ ጊዜ ይህንን ሁሉ ፀጋዋን ስላጣች ምሳሌነትዋን ለመቅሰም ወደ እርስዋ የሚሄድ ሁሉ በከንቱ ይደክማሉ። በጠቅላላው ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ጋር የጠቀስናቸውን የአራቱን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በሚገባ ተመልክተን እንደሆነ ለመንጋዎቹ እንቅፋት የሆኑት ሾልከው የገቡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ወይም ተከተሎች ናቸው። በተለይ በትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን መድረክ ተለቀላቸው የስሕተት ትምህርታቸውን ያስተምሩ ስለነበሩ በምዕምናኑ ላይ ብዙ መሰናክል አድርሰዋል። ምዕምናኑም ከእምነታቸው ጨርሰው ስለተናጉ ኤልዛቤል በምትከተለው በአረማውያን ልማድ ተማርከው ከእግዚአብሔር እውነት ጨርሰው ርቀዋል።

5. ሰርዴስ፡- ሰርዴስ የጥንታዊው የሊድያ መንግሥት ዋና ከተማ ነበረች። ንጉሥዋም በሀብቱ የታወቀ እጅግ ባለ ፀጋ ሰው እንደ ነበረ ይነገርለታል። እርሱም በዳርዮስ መንግሥት ሀብቱ በተዘረፈበት ወቅት የገንዘቡ ክምችት ከስድስት መቶ ሚልዮን ብር በላይ የሚገመት እንደነበረ ታውቋል። ከዚህ በኋላ በሰርዴስ የፍርስራሽ ክምር በስተቀር ምንም የቀረ ነገር አልነበረም። ስለዚህ ይህ ወናና ምድረ በዳ ሆኖ የቀረው መንደርዋ የጥንታዊትዋን የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ባህርይ በተዘዋዋሪ መንገድ ይገልጻል። ይኸውም «ስም አለህ ሞተህማል» የተባለው ነው።

6. ፊልደልፍያ፡- ሁለተኛይቱ የሊድያ ከተማ ነበረች። ይህች ቤተ ክርስቲያን በተጻፈላት መልዕክት ውስጥ ሕዝብዋ «በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እንደሚጠበቅ» ተነግሮላታል። ይህ የተስፋ ቃል ጊዜውን ጠብቆ ተፈጽሟል። የሮማውያንን መንግሥት መግነንና ውድቀት እንዲሁ እንደነበረ ዜና አቅራቢ የነበረው ጋቦን በገለጸው ዘገባ መሠረት ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያኖች አትዋ የተባለው ሰው ባስነሳው ወረራ ምክንያት በ131 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንዳልነበሩ ሆነው እንደተደመሰሱ ተነግሯል። ያም ሆነ ይህ በጠላት ከተደመሰሱት የጥንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ደብዛቸው ሳይጠፋ ለምልክት ያህል የቀሩ ብልድያና በኒቆኒዮም ጥቂት ማስታወሻዎች እስከ ዛሬም አሉ። ከሰባቱ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያይቱ የሆነችው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በተደመሰሰች ጊዜ በሰባቱ መቅረዞች ከሚመሰሉት የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ መልአክ የመጀመሪያው እንደ ወደቀ ተደርጐ ይገመት ነበረ። ከዚህ በኋላ በዚህ ቦታ የእንስሳት ቲያትር ትዕይንት የሚታይበት አደባባይና ሌላ ሦስት መደበኛ የትያትር ቦታዎች ተቋቋሙ። ስለዚህ የሰርዴስ ከተማ የዱር እንስሳዎች መፈንጫ በመሆን ከቀድሞ ክብርዋ እጅግ ተዋርዳለች። ከዚህም በቀር የትያጥሮንና የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን በነበረችበት ስፍራ የመሐመድ አምላክ የሚመለክበት ስፍራ ሆኖ ተለውጧል። በተነገረላት ትንቢት መሠረት ይህን የመሰለ ውርደት ሳይደርስባት ተጠብቃ የቆየች የፊልድልፍያ ቤተ ክርስቲያን ብቻናት። ስለሆነም ጨርሶ ከመፍረስና ከመደምሰስ ባትድንም ለማስታወሻ ያህል ጥቂት ቅሬታ የሚታይባት እርስዋ ብቻ ናት። በዚህ አንጻር እግዚአብሔር ያከበረውና ተስፋ የገባለት ሕዝብ መከራ ቢቀበልም ደብዛው ከምድር እስከሚጠፋ ድረስ ጨርሶ የማይደመሰስ መሆኑን ያስተምረናል። በዚህ መሠረት በፊልደልፍያ ከሚገኙት ፍርስራሾች መካከል አንዱ

የድንጋይ ማዕዘን ለፊልደልፍያ የተገባላትን የቃል ኪዳን ቃል የያዘ ነበረ። ይኸውም «ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፤ ወደፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም።»

7. ሎዶቅያ፡- የታላቁ የፍርግያ ዋና ከተማ ስትሆን ሰፊና እጅግ የተንሰራፋ አካባቢን የያዘች ቦታ ነበረች። ፍርስራሹ እስካሁን ድረስ ጨርሶ ያልጠፋ ከ20 እስከ 30 ሺህ ተመልካቾችን የሚይዝ ታላቅ የቲያትር አዳራሽ ነበራት። ተራራዎችዋም ቀደም ሲል በተነሳው እሳተ ገሞራ ምክንያት አቧራና ድንጋይ የለበሱ ዓይነቶች ናቸው። እስካሁን ድረስ በሕብረተሰቡ መካከል የተለያየ የሙቀት ደረጃ ያላቸው የፍል ውኃ ምንጮች አሏት።

ይህችም ቤተ ክርስቲያን በነበራት አቋም በአንድ አፓጋቢ በሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ስላልነበረች በውስጥዋ ከነበሩ ምንጮች ጋር የተያያዘ መልዕክት ደርሰዋታል። ይኸውም ትኩስ ወይም በራድ ስላልሆነች ለብ በማለትዋ ልትተፋ መቃረብዋን የሚያስረዳ ነበረ። ሎዶቅያ በአሁኑ ጊዜ ለምንም የማትውል ጭው ያለች ምድረ በዳ ሆናለች። እርስዋም ለብዙ መቶ ዓመታት ያህል የፍርስራሽ ክምር ሆና ከመኖርዋ በላይ ከነገር ሁሉ ተነጥላ ብቻዋን በመቅረት ከኤፌሶን አልቃ ትብሳለች። በላይዋም ትቢያና ጉድፍ ተከምሮባት ኩሲና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በመሆንዋ ሙጃ አልብሷታል። ከዚህ የተነሳ እርስዋ ብቻ ሳትሆን የቀድሞ ስሟ ጭምር ተረስቶ ጨርሶ ጠፍቷል። ስለዚህ አካባቢዋ ሁሉ ጤናማ ስላይደለ የሚያስተጋባው ሁሉ ምድረ በዳነትንና ባዶነትን ብቻ ነው።

## ፍጥሞ

የፍጥሞ ደሴት ልምላሜ የማይታይበት ደረቅና ድንጋያማ የሆነ ምድረ በዳ ስፍራ የሚገኘውም በእስያ ባሕር አቅራቢያ ነበረ። ዮሐንስም ከኅብረተሰቡ ተለይቶ ዶሚተስ በተባለው ሰው የተጣለው ይህን በመሰለ ስፍራ ነበረ። ለዚያውም ደግሞ ደሴቲቱ በዙሪያዋ ባሉ ውኃዎች ዙሪያዋን እየተሸረሸረች ነበረ። የአካባቢዋ ግዛት ዋና ከተማም የደሴቲቱንና የባሕሩን አቀማመጥ ቁልጭ አድርጎ ለማየት በሚቻልበት ሁኔታ በከፍተኛ ተራራ ላይ ተመስርታ ነበር። በሀገሪትዋ ባህላዊ ታሪክ አንጻር ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የተገለጠለትን ራዕይ የተመለከተው በተራራው ከፍታ መካከለኛ ስፍራ ላይ በሚገኝ ታላቅ ቋጥኝ ላይ እንደነበረ ነው ተብሎ ይታመናል።

## ስለ ዮሐንስ የተነገረ ባሕላዊ አገላለጽ

ብዙ የጥንት ባህል ጸሐፊዎች ስለ ዮሐንስ ባቀረቡት ዘገባ ላይ ዮሐንስ ታላቅ መንፈሳዊ ቅናት የነበረው ሰው እንደሆነ ተናግረዋል። እርሱ በሚሰብክበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በተለየ ሁኔታ ይጠቀምበት ስለነበረ በተለያየ ውንብድና ውስጥ ያሉ ኃጢአተኞች ሁሉ እንባቸውን እያዘሩ ንስሐ በመግባት ከእግሩ በታች ወድቀው ይጸልዩ ነበር። በተለይ አንድ ጊዜ ከብዙ ሰዎች ጋር በአንድ መጠመቂያ ውስጥ ሆኖ ገላውን እየታጠበ ሳለ በመካከላቸው ሐሰተኛ መምህራን ስለ ነበሩ ከእነዚህ የእውነት ጠላቶች የተነሳ ይህ መጠመቂያ ይዘን እንዳይሰጥም

«ፈጥነን ከዚህ ቦታ እንሽሽ» ብሎ እንደነበረ ይነገርለታል። ዮሐንስ በዕድሜው ብዙ እስከ ገፋ ድረስ መንፈሳዊ ቅንአቱ ጨርሶ ያልበረደ በመሆኑ ብዙ ጊዜ በአልጋ ተሸክመው ወደ ቤተ ክርስቲያን እየወሰዱት ይሰብክ ነበር። በተለይ በአንድ ወቅት ከተኛበት አልጋ ውስጥ እጁን ወደ ውጭ ዘርግቶ «እናንተ ታናናሽ ብላቴናዎች ኑ እርስ በርሳችን እንዋደድ» ሲል ተናግሮ ነበር ይባላል። ወደ ጉባዔው መምጣት እስካልቻለ ድረስ እጅግ ዕድሜን ጠግቦ በመጨረሻ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

# ክፍል 9

# የኢየሩሳሌም መፍረስና በተመሳሳይ ወቅት የተፈጸሙ ሁኔታዎች

## በይሁዳ የተፈጸሙ ሁኔታዎች

ከፊስጦስና ከፊልክስ በኋላ የሮም አገረ ገዢ ሆኖ በይሁዳ የተሾመው ሰው በሕዝቡ ላይ ታላቅ ተጽዕኖና ጫና ስላሳደረ አይሁዶች በጣም ታውከው ነበረ። ከዚህ የተነሳ ሕዝቡ ብሶቱን ለመግለጽ በየአደባባዩ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርግ ነበረ። በተለይ በአንድ ወቅት በቂሣርያ አውራ ጐዳና ላይ ብዙ ሺህ አይሁዶች በሕብረት ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው ነበረ። ይህ ሰላማዊ ሰልፍ ውሎ አድሮ አጠቃላይ የሆነ አድማ ለማስነሳት ምክንያት ሆኗል። ጳውሎስ በሮም መከራና የሞት ስቃይ እየተቀበለ በነበረበት ወቅት ኔሮ ሺስፓሲያን የተባለውን የጦር ጀነራሉን ይሁዳ ልኮ አይሁዶችን ያስመታ ነበረ። ሺስፓሲያን ከአይሁዶች ጋር ባደረገው ጦር በብዙ መንገድ ድል አድርጐ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ በቁጥጥሩ ሥር ካደረገ በኋላ የሚቀረውን ሥራ ሁሉ በልጁ በቲቶ ኃላፊነት ሥር ሰጥቶ ወደ ሮም ተመልሷል።

## ቲቶ ኢየሩሳሌምን እንደያዘ

ቲቶ ወደ ኢየሩሳሌም እየቀረበ በመጣ ጊዜ አስፈሪ የሆነ ሁከትና ሽብር ተነሳበት። ይኸውም ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ አናስቀርብህም የሚል ነበረ። ሆኖም የቲቶ ወታደሮች ከተማዋን ወዲያውኑ እንደመጡ ሊይዟት ባይቻላቸውም ቀስ በቀስ እያሉ ውለው አድረው ከተማዋን ከቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ችለዋል። ቢሆንም በጦርነቱ ጊዜ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ እንዲቃጠል የቲቶ ፈቃድ አልነበረም። ሆኖም በሽብሩ መካከል ድንገት ነሐሴ 9 ቀን ቤተ መቅደሱ በእሳት ተለኩሶ ፈጽሞ እስኪወድቅ ድረስ ጋይቷል። ኢየሩሳሌም ከተደመሰሰች በኋላ አይሁዶች ወደ ጐረቤት አገሮች ሁሉ ተበታትነው በጥገኝነት ለመኖር ተግደዋቸው። ዳሩ ግን የሮም ወታደሮች ተከታትለው በመሄድ መልሰው ሊያመጡዋቸው በሞከሩ ጊዜ ለጠላት አንገዛም ሲሉ በራሳቸው ላይ አሳዛኝ የሆኑ ድርጊቶችን ፈጽመዋል። ያም ሆነ ይህ ይሁዳ በሮማውያን ጨርሶ ከመያዝ አልዳነችም። አባቶች ለዘመናት እግዚአብሔርን

ሲያመልኩባት የቆየችው ውቢ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተቃጠለች። ረጅሙ የወናንትና የምድረ በዳነት ዘመን ጀመረ። ይኸውም የአሕዛብ ዘመን እስኪፈፀም ድረስ ነው። እስከዚያም ድረስ ኢየሩሳሌም እንድ ቅርጫ ሥጋ በአሕዛብ እጅ ተቆራርሳለች። ዮሐንስ ይህን ሁኔታ ቀደም ሲል ተመልክቶ ስለነበረ ተመሳሳይ ውድቀት እንዳይደርስባቸው ለማስጠንቀቅ በእስያና በኤፌሶን ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት መቅረዛቸው እንዳይወሰድ አሳስቦአቸዋል።

## የቲቶና የዶሚቲያን ግዛቶች

በመጨረሻው መቶ ዓመት አጋማሽ ላይ አስደናቂ የሆነ አጠቃላይና ታላቅ የዓለም ታሪክ ተፈጽሞ ነበር። ቬስፓሲያን በቲቶ እስከተተካበት ዘመን ድረስ ይሁዳን ለአሥር ዓመታት ያህል በታላቅ ክብርና ብልጽግና አስተዳድሯታል። በኋላም ቲቶ የአስተዳደሩን ሥልጣን ተረክቦ አገሪቱዋን እየመራ በነበረበት ወቅት «የሰው ልጅ የደስታ ቁንጮ» የሚያሰኘውን ስም አትርፎ ነበር። ሆኖም አጭርና መጠነኛ በሆነችው ያስተዳደሩ ዓመታት መካከለኛ ዘመን ላይ ቬሲለስ ከተባለው ተራራ ውስጥ በተነሳው እጅግ አስፈሪ በሆነ እሳተ ገሞራ የፓምፒና የሄርኩለኔዩም ከተማዎች ነደውና ታቃጥለው ሊሰጥሙ ችለዋል። ከዚህ በኋላ ቲቶ በጣም አመጸኛና አንባ ገነን በሆነ ደሚቲያን በተባለ ወንድሙ ተተካ። ይህን ሰው የመሰለ ግፈኛ ንጉሥ በዘመን ሁሉ በዙፋን ላይ ተቀምጦ አያውቅም ነበረ። በአጠቃላይ እንደሚታመነው ታላቁ የክርስቲያን ስደትና ግድያ የተፈጸመው በዚህ ግፈኛ ንጉሥ ያስተዳደር ዘመን ነበረ። ዮሐንስም ፍጥሞ ወደምትባለው ደሴት የተጣለው በዚሁ ወቅት ነበረ። ከዚያም ደሚቲያን ነርቫ በተባለ ሽማግሌ ሰው ተተክቶ የመንግሥቱ ዘመን ያበቃል። ይህም ሰው ጠቢብና አስተዋይ ስለነበረ ባለፉት ነገሥታት ዘመን የተበላሹትንና የተዛቡትን ነገሮች መልሶ በመጠገን ታላቅ የእድሳት ተግባርን የፈጸመ ንጉሥ ነበር።

ከጌታችን ልደት ቀደም ሲል አጉስቶስ የጳኑስን ቤተ መቅደስ በዘጋበት ዘመን አንዳንድ ጥቃቅን የባዕድ አገር ጦርነቶች ተካሂደው ነበር። ስለዚህ በሮም ግዛት ዳር አገር ላይ የተከማቹ የጳርቴ፣ የጀርመን፣ የብሪታንያና እንዲሁም የተለያዩ ጉሳዎች ሕዝብ በሮም ጭፍራዎች ላይ ተጨማሪ ኃይል ሆነው ለጦርነት የሚያገለግሉ ቅጥረኛ ሠራዊቶች ነበሩ። የኔሮ ግዛት በሆነው በብሪታንያ ምድር ላይ ብዙ ደም የተጠሙ ጨካኝ የጦር ሠራዊቶች ማሰልጠኛ ቦታ ነበረ። ይህ ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም በምትገኘው ትንሽ የኪራይ ቤት ውስጥ እየኖረ የፊልጵስዩስን፣ የኤፌሶንንና የቆላስይስ መልዕክቱን የጻፈበት ዘመን ነበረ። ሐዋርያው ዮሐንስ የኤፌሶንን ምዕምናን እርስ በርሳቸው ይዋደዱ ዘንድ እያበረታታቸው በነበረበት ወቅት አግሪኮላ ብሪታንያን ድል የማድረጉን ጦርነት ጨርሶ ምሽጉን ጦርነት ወዳዶች በሆኑት ከለዳውያኖች በደሴቱ እቋራጭ ላይ እንዲታነጽ አድርጓል። በዚህን ጊዜ ለጦርነት መጥተው ከነበሩት የሮም ወታደሮች መካከል ክርስቲያኖች የሆኑ ስለነበሩባቸው ለእነዚህ ድብልቅ የአሕዛብ ወገኖች የክርስቶስን የደኅንነት ወንጌል ሊያስተዋውቁአቸው ይገፋፉ ነበር። ምናልባት በመጀመሪያው መቶ ዓመት መዝጊያ ላይ የክርስቶስ ኢየሱስን ስም መባረክና መውደድ የለመዱ ሰሜናዊና ደቡባዊ ብሪቲሾች ይኖሩ ይሆናል።

## የክርስቶስና የሐዋርያቶቹ ሥራ

አንድ ሰው በክርስቶስ በመሆን ምክንያት በሕይወቱና በኑሮው ላይ ስለሚታየው ታላቅ ለውጥ ማብራሪያ ለመስጠት በአንድ ምዕራፍ መግለጫ የሚያበቃ ሳይሆን አንድ ትልቅ መጽሐፍ ሊወጣው የሚችል ነው። በዚያን ጊዜ በድንግዝግዝ ይለፈፍ የነበረው እውነት አሁን ግልጽ በሆነ በመለኮታዊ ብርሃን ተገልጿል። በተስፋ ይጠበቅ የነበረውም አዳኝ መጥቷል። እርሱም ምድራዊ አገልግሎቱን አጠናቅቆ ከፈፀመ በኋላ ተመልሶ ወደ አባቱ ዘንድ ሄዷል። በምድር በሰዎች ልጆች መካከል በኖረበትም ጊዜ ብዙ ጊዜ ለነፍስና ለሥጋ በሚጠቅሙ ነገሮች ሲረዳና ሲያገለግላቸው ቆይቷል። እርሱም አብረውት ለነበሩ ሰዎች ሁሉ የኃጢአት ይቅርታ፥ የሰላምና የደስታ፥ የፍቅርና የቅድስና፥ የነፃነትና የዕድገት፥ እንዲሁም የቀሩት በረከቶች ሁሉ ምንጭ ሆኖላቸው ነበረ። ስለዚህ በአጠቃላይ ከእርሱ ጋር በመቀራረብ የሚደረግ ኑሮ ሁሉ በውስጥ ካለ ማንኛውም መንፈሳዊ በሽታ በሞላ የሚፈውስ ነው። ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር በሚኖራቸው ሕብረት በኩል ወደ እግዚአብሔር አብ መምጣት ይኖርባቸዋል። እርሱም ከማንም ሰው ይልቅ ስለ መስዋዕትነቱ ሚስጥር ለሐዋርያቶቹ አስረድቷቸው ነበረ። ይህም መስዋዕትነት ሰዎች ሁሉ የኃጢአታቸውን ሥርየት የሚያገኙበት ቀጥተኛ የእግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ ነበረ። በብሉይ ኪዳን ዘመንም ቢሆን የተለያዩት ምሳሌአዊ ስርዓቶች ሁሉ ያሳዩ የነበሩት ይህንኑ በክርስቶስ የሚገኘውን የደኅንነት መንገድ ነበር።

## የታሪኩ መደምደሚያ ክፍል

እስካሁን ድረስ የተነገረው የወንጌል አገልግሎትና የተአምራቱ አሠራር ታሪክ በዚህ ሲያበቃ ፀጋውን ለሰዎች ልጆች ለመስጠት የሚያደርገውን የደኅንነት ውጊያ ግን እስካሁንም ሆነ ወደፊት እስከመጨረሻ ድረስ አያቋርጥም። አሁን የወንጌሉ ትርጉም ራዕይ እየተገለጠ ነው። የክርስቶስም ቤተ ክርስቲያን የእርሱ ምስክርነት የመሆንዋን አገልግሎት እየሰጠች ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሀሳቡን ይደመድማል።

*********////////*********